# ውዳሴ መስቀል

ዘ

# አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ትርጉም

በዲያቆን ዳንኤል ክብረት

አሳታሚና አከፋፋይ

አማዮስ ኅትመትና ጠቅላላ ንግድ

# አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ታላቅ ቦታ የያዘ ኢትዮጵያዊ ሊቅ:: ዐፄ ዳዊት ደግሞ "ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ" ብለውታል:: አባቱ ሕዝበ ጽዮን እናቱ አምኃ ጽዮን ይባላሉ:: እንደ ድርሳነ ዑራኤል አባቱ በመጀመሪያ የትግራይ በኋላ ደግሞ የሰግላ /ጋሥጫ/ገዥ ነበር:: እንደ ገድሉ ደግሞ ጠቢብና የመጻሕፍት ዐዋቂ፣ የእግዚአብሔር ወዳጅና በቤተ መንግሥት በነበረችው ድንኳን/ሥዕል ቤት/ ከሚያገለግሉ ካህናት ወገን ነበር:: የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ የመረመርን እንደሆነ ሁለቱም ምንጮች ስለ አንድ ጉዳይ የተለያዩ መረጃዎች የሚሰጡ ሳይሆኑ አይቀርም ::

ለምሳሌ በንጉሥ ላሊበላ ዘመን የአራቱ የኢትዮጵያ ግዛቶች ገዥዎች የታላላቅ አድባ ራትና አስተዳዳሪዎች ነበሩ:: ከዚህም በላይ የአንዳንድ ገዳማት አበምኔቶችና በቤተ መንግሥት የሚያገለግሉ ካህናት አንድ አንድ አውራጃ ወይም ወረዳ ይሾሙ ነበር:: በመሆኑም የአባ ጊዮርጊስን እናት ገድሉ "ወእሙኒ እም ሰዩማነ ወለቃ" ይላታል:: ይህም በወለቃ/የዛሬ ደቡብ፣ ወሎ፣ ቦረና/ ከነበሩ መኳንንት ወገን መሆኗን ያመለክታል::

አባ ጊዮርጊስ የተወለደው በ1357 ዓ.ም ነው[1]:: ወላጆቹ ልጅ ስለሌላቸው ዘወትር እያዘኑ ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር:: አባ ጊዮርጊስ የተወለደው በቅዱስ ዑራኤል አብሳሪነት መሆኑን ድርሳነ ዑራኤል ይተርከልናል ::

አባ ጊዮርጊስ የመጀመርያውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተማረው ከአባቱ ሳይሆን አይቀርም:: ምክንያቱም አባቱ የመጻሕፍት ሊቅ መሆኑን ስንመለ ከትና ገድሉም አባ ጊዮርጊስን በተመለከተ "ወሰበ ልህቀ ሕቀ ወሰዶ ኀበ ጳጳስ ወሴሞ ዲያቆን" የሚለውን ስናጤነው አባቱ የመጀመሪያውን ደረጃ ትምህርት ካስተማረው በኋላ ከጳጳሱ ዘንድ ወስዶ ዲቁና አሹሞታል ማለት ነው:: ገድሉ ዲቁና የሰጡትን ጳጳስ ስም አይነግረንም:: ነገር ግን በ1341 ዓ.ም ወደ

[1] ገድሉ ያረፈበትን ዘመንና ያረፈው በተወለደ በ60 ዓመቱ መሆኑን ስለሚገልጥ ከዚያ በመነሣት የሚገኝ ነው::





ኢትዮጵያ የመጡትና እስከ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ የነበሩት አቡነ ሰላማ መተርጉም ሳይሆኑ አይቀሩም::

ዲቁና ከተቀበለ በኋላ ለትምህርት ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ተላከ:: ወደ ሐይቅ የገባው በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት /1374 -1306 ዓ.ም/ መሆኑን ገድሉ ይገልጣል:: ሐይቅ እስጢፋኖስ የተለያዩ ሊቃውንት የሚገኙባት፣ በብዙ መጻሕፍት የተሞላችና ዙሪያዋም በሐይቅ በመከበቧ የተማሪን ሐሳብ ለመሰብሰብ አመቺ የሆነች ቦታ ናት:: አባ ጊዮርጊስ በሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርት አልገባው ብሎ ለሰባት ዓመታት ተቀምጦ ነበር:: አብረውት የሚማሩት ተማሪዎች ይህ ትምህርት የማይገባው ስለ ምንድን ነው? በእርሱ ኃጢአት ነው ወይስ በወላጆቹ? ይሉት ነበር:: በዚያ ጊዜ የሐይቁ መምህር የነበረው ዐቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ለአባቱ "ልጅህ ትምህርት አይገባውማና የቤተ መንግሥት ነገር አስተምረው" ብሎ መለሰው:: አባቱ ሕዝበ ጽዮን ግን "አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ፤ እዚያው ገዳሙን ያገልግል" ብሎ እንደ ገና ላከው::

አባ ጊዮርጊስ ዕውቀት ስለ ተሠወረው ሁል ጊዜ በሥዕለ ማርያም ሥር እየተንበረከከ ይጸልይ ነበር:: የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምንም እህል በመፍጨት ያገለግል ነበር[2]:: አንድ ቀን እመቤታችን ተገለጠችለትና «አይዞህ ዕውቀት የተሠወረብህ ትምህርት ስለማይገባህ ሳይሆን የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንዲገለጥ ነውና ታገሥ» አለችው:: ከዚያም ጽዋዕ ልቦና አጠጣችው::

ከዚህ በኋላ በሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርቱን በሚገባ ተምሮ አጠናቀቀ:: በዕውቀቱ ቀድሞ የሚያውቁት ሁሉ ይደነቁበት ነበር::

[2] በ1988 ዓ.ም የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምን የመጽሐፉ አዘጋጅ በጎበኘበት ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ይፈጭበት የነበረውን የድንጋይ ወፍጮ ገዳማውያኑ አሳይተውታል::

አባ ጊዮርጊስ በዜማ[3]፣ በትርጓሜ መጻሕፍትና በቅኔ የጠለቀ ዕውቀት እንዳለው ድርሰቶቹ ይመሰክራሉ።

የማስተማር ሥራውን የጀመረው በዚያው በሐይቅ እስጢፋኖስ መሆኑን ገድሉ በሚከተለው መልኩ ይገልጠዋል "ወአብርሃ ለቤተ ክርስቲያን እንተ ተሐንፀት በሐይቅ ባሕር፣ ወእም አሜሃ አሐዘ ይሰአሉ እም ኀቤሁ ኵሎሙ ሰብአ ሀገር ቃለ መጻሕፍት ወትርጓሜሆሙ፣ ወኵሎ ቃለ ማኅሌት።"[4]

ከሐይቅ በኋላ በዚያ ዘመን ሸግላ በመባል ትጠራ ወደ ነበረችው ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ጋሥጫ ተጓዘ። በዚያ ጊዜ የነገሥታቱ መቀመጫ በዚያ የነበረ ይመስላል። ለዚህ ሦስት ምልክቶች አሉ። የመጀመሪያው በነገሥታቱ መቀመጫ አካባቢ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚበዙት ሁሉ /አኩስምን፣ ላስታን፣ ጎንደርን፣ አንኮበርንና አዲስ አበባን በምሳሌነት ማንሣት ይቻላል።/ በጋሥጫም በዚያም ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። ሁለተኛው ደግሞ በገድሉ ላይ አባ ጊዮርጊስ ወደ ሸግላ በመጣ ጊዜም ወደ ቤተ መንግሥት እንዳስገቡት የሚገልጠው ነው። ሦስተኛው መረጃ ጋሥጫ የዐፄ ይስሐቅ የክረምት ጊዜ ማረፊያ እንደነበረች ገድሉ መግለጡ ነው።

አባ ጊዮርጊስ ወደ ሸግላ ሲመጣ አባቱ በጣም አርጅቶና መንኩሶ ነበር። ስለዚህም በአባቱ እግር ተተክቶ በቤተ መንግሥቱ ያለችውን ሥዕል ቤት እንዲያገለግል ወደ ዚያው አስገቡት። በቤተ መንግሥቱ የንጉሡን ልጆች ከማስተማሩም በላይ በቤተ መንግሥቱም ዙሪያ ከነበሩት ሊቃውንት መካከል አባ ጊዮርጊስ አንዱ ነበር። በአንድ ወቅት ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ በርተሎሜዎስ ሥላሴን አንድ ገፅ ብለው ያምናሉ ተብለው በተከሰሱ ጊዜ ነገሩን እንዲያጣሩ ከተመረጡት ከቄስ ዐፄ ተከሥተ ብርሃንና ከሐይቁ መምህር ዐቃቤ ሰዓት ዮሴፍ ጋር አብሮ ተልኮ ነበር። እንዚህ ሦስት አበው ጳጳሱን

[3] የያሬድን ዜማ ከአባ ሳሙኤል ዘጋርማ እንደተማረው ገድሉ ይገልጣል። በዐፄ ዳዊት ዘመን የድጓ ዋና ማዕከል በነበረው በደብረ ነጎድጓድ ተሾሞ ሳያስተምር አይቀርም። ምክንያቱም አባ ጊዮርጊስ በኢትዮጵያ የድጓ መምህራን ዝርዝር ውስጥ ስሙ ይጠቀሳልና።

[4] ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣2004 ዓም፣ ገጽ 47 (በዚህ መጽሐፍ የተጠቀምኩት ማኅበረ ቅዱሳን ለገዳሙ ያሳተመውን ገድል ነው።)





ካነጋገሩ በኋላ ክሱ ውሸት መሆኑን በማረጋገጥ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ የሚገልጠውን የጳጳሱን እምነት በጽሑፍ ይዘው መጡ።

በቤተ መንግሥቱ በነበረ ጊዜ የንጉሡን ልጆች ይስሐቅን፣ ቴዎፍሎስን፣ እንድርያስን፣ ሀብተ ኢየሱስን፣ ሕዝቅያስን፣ ኢዮስያስን፣ ዘርዐ ያዕቆብንና ሴት ልጁን እሌኒን በምግባርና በሃይማኖት ቀርጿቸዋል። ከእነዚህም መካከል ዘርዐ ያዕቆብ በድርሰቱ ሲመስለው ቴዎድሮስ ደግሞ በሕይወት መስሎታል። ዐፄ ዳዊት የአባ ጊዮርጊስን ሊቅነትና መልካም ሥነ ምግባር በሚገባ ስላወቀ በጋብቻ ሊዛመደው ወዶ ስለነበር ልጁን እንዲያገባ ዘወትር ይጠይቀው ነበር። አባ ጊዮርጊስ ግን በድንግልና ጸንቶ ለመኖር እንደሚፈልግ ከመግለጽ አልተቆጠበም። የዐፄ ዳዊት ጥያቄ ስለበዛበት ወደ አቡነ በርተሎሜዎስ ሔዶ ቅስናን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው መነኮሰ። ገድሉ የት እንደ መነኮሰ አይገልጥልንም። ነገር ግን አንድም በሐይቅ እስጢፋኖስ ያለበለዚያም በደብረ ጎል ሊሆን እንደሚችል ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ግምታቸውን አስቀምጠዋል።

ከመነኮሰ በኋላ ወደ ሸግላ በመምጣት "ወእምድኅረዝ ኮነ አቡነ ጊዮርጊስ መምህር ለነገሥት ወለካህናት ዘደብተራ፣ ወለኵሉ ዐበይተ ቤተ መንግሥት፣ ለንቡራነ እድ ወለመኳንንት፣ ለመሳፍንት ወለኵሉ ተዐይነ ቤተ መንግሥት» ይላል ገድሉ። ከዚህ በኋላ ለነገሥታትና በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ካህናት እንዲሁም በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ታላላቆች፣ ለንቡራነ እድና ለመኳንንት፣ ለመሳፍንትና በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ባለሟሎች ሁሉ መምህር ሆነ።"

አባ ጊዮርጊስ በሸግላ በነበረ ጊዜ በወባ በሽታ ታምሞ ሊሞት ደርሶ እንደ ነበር ገድሉ ይናገራል። ታምሞ በነበረ ጊዜ አንድ ሌሊት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ተገልጠውለት ከእኛ ጋር ትኖር ዘንድ ልንወስድህ መጣን አሉት። እርሱም «የድርሰት ሥራዬን ሳልሠራና እግዚአብሔርንም አብዝቼ ሳላመሰግነው አሁን አትውሰዱኝ» ሲል ለመነ። እነርሱም ልመናውን ተቀብለውት ከሕመሙ ፈውሰውት ሔዱ። ለዚህም ይመስላል ከበሽታው እንደ ተፈወሰ ወዲያው የድርሰት ሥራውን የጀመረው።

የመጀመሪያ መጽሐፉን ጽፎ እንደ ጨረሰ ጠፍቶበት እንደ ነበረ ገድሉ ይተርካል። ከቤቱ ውስጥ የነበሩትን መጻሕፍት ሁሉ እያገላበጠ ቢፈልገውም

ሊያገኘው አልቻለም:: አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ሌሊት በአገልግሎት ላይ እያለ እመቤታችን ተገልጣ "ለምን አስቀድመህ ሳትነግረኝ ጻፍከ?" ስትል ጠየቀችው:: እርሱም "አንቺን ደስ ያሰኘሁ መስሎኝ ነውና ይቅር በይኝ?» ሲል መለሰላት:: ከዚህ በኋላ የድርሰት ሥራውን ፈቅዳለት ተሠወረችው:: "ወሶቤሃ በርሃ ልቡ ከመ ፀሐይ፤ ወሐተወ ውስተ ኀሊናሁ ባሕርየ መለኮት፤ ወነጸረ ኩሎ ኅቡአት -ከዚህ በኋላ ልቡ በራለት፣ ኅሊናውም ነገረ መለኮትን ዐወቀ:: የተሠወረውንም ሁሉ ተመለከተ" ይላል ገድሉ[5]::

የመጀመሪያው ድርሰቱ አርጋኖን የተሰኘውና በቅኔ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚያመሰግነው መጽሐፉ ነው:: ስለ አርጋኖን ድርሰቱ ገድሉ በሚከተለው መንገድ ይገልጠዋል "ወሰመዮ በሠለስቱ አስማት ዘውእቶሙ አርጋኖን ውዳሴ፣ ወመ ሰንቆ መዝሙር ወእንዚራ ስብሐት - በሦስት ስሞችም ሰየማቸው፤ እነርሱም አርጋኖን ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙርና እንዚራ ስብሐት ናቸው::"[6] ይላል:: ይህ አገላለጥ አንድ ነገር እንድናስተውል ያደርገናል:: ይሄውም ስለ አርጋኖን መጽሐፍ ይዘት ነው:: በገድሉ ላይ አርጋኖን መጽሐፍ አንድ ሆኖ ሦስት ክፍሎች ያሉት ይመስላል:: እስካሁን የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ አርጋኖንንና እንዚራ ስብሐትን ለየብቻ አግኝቷቸዋል:: አርጋኖን ከሰኞ እስከ ዓርብ ላሉት ዕለታት ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን እንዚራ ስብሐት ግን ከ/ሀ/ እስከ /ፖ/ ያሉትን ፊደላት በመከፈያነት በመጠቀም የተዘጋጀ ነው:: ይህም አርጋኖንን አባ ጊዮርጊስ ሲያዘጋጀው አንድ ሆኖ በኋላ ግን በየክፍሉ እየተጻፈ የተባዛ ይመስላል::

እመቤታችን አርጋኖንን ስለ ወደደችለት ዚማት/ምናልባት ዤማ ይሆን?/ በሚባለው ሀገር በነበረ ጊዜ «ከድርሰቶችህ ሁሉ እንደ አርጋኖን የምወደው የለም» ብላዋለች:: ዐፄ ዳዊትም ድርሰቱን በጣም ከመውደዱ የተነሣ በወርቅ ቀለም እንዳጻፈው ገድሉ ይገልጣል::

[5] ገድለ አባ ጊዮርጊስ፣ ገጽ 54፡55

[6] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 56





ከዚህ በኋላ የደረሰው ድርሰት ይህ አሁን ተተርጉሞ የቀረበው ውዳሴ መስቀል ነው:: ቀጥሎም መጽሐፈ ስብሐት ዘመዓልት ወዘሌሊት የተባለውን (ወይም እርሱ ራሱ መጽሐፈ ብርሃን ብሎ የሰየመውን) መጽሐፍ አዘጋጀ:: መጽሐፈ ብርሃን ብሎ የሰየመበትን ምክንያት ገድሉ ሲያብራራ "እስመ ውእቱ ያበርህ ወያስተርኢ ፍናወ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር፣ ወፍናወ ስብሐቲሆሙ ለትጉሃን፣ ወለኩሎሙ ማኅበረ ቅዱሳን ልዑላነ ብርሃን ወዓዲ ይነግር እንዘ ያስተሐውዝ ውዳሴሃ ለድንግል ንጽሕት - የእግዚአብሔርን የምስጋናውን መንገድ ያበራል /አብርቶ ያመለክታልና፣ ልዑላነ ብርሃን የሆኑትን የማኅበረ ቅዱሳንንና የትጉሃንን የምስጋናቸው መንገድ ያመለክታልና፣ የእመቤታችንንም የምስጋናዋን ጣዕም ይገልጣልና "ይላል::[7]

በዚያ ጊዜ በነበረው ልማድ ካህናቱ ቁርባን በሚያቀብሉ ጊዜ ሕዝቡ ወደ ካህናት መጥተው ሲቀበሉ ንግሥቲቱ ግን ካለችበት ቦታ ካህናቱ ሔደው ነበር የሚያቆርቧት:: አባ ጊዮርጊስ ግን "ይህ ቁርባን ንጉሠ ነገሥት ነውና ንግሥቲቱ ወደዚህ መጥታ ልትቀበል ይገባታል እንጂ እኛ መሔድ የለብንም" ሲል ተቃወመ:: ይህን ነገር ንግሥቲቱንና አባ ጊዮርጊስን ስላጋጫቸው ዐፄ ዳዊት ችግሩን ለመፍታት አባ ጊዮርጊስን ወደ ሀገረ ዳሞት ንቡረ እድነት ሾሞ ላከው::

አባ ጊዮርጊስና አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ የተገናኙት አባ ጊዮርጊስ ወደ ዳሞት በሚ ጓዝ ጊዜ ነበር:: አባ ጊዮርጊስ አለባበሱ እንደ ተርታ ሰው በመሆኑ አቡነ ሳሙኤል በመጀመሪያ አላወቁትም ነበር:: በዚህም የተነሣ አባ ጊዮርጊስ ቅር ብሎት ወደ ዳሞት ተመለሰ:: እንደ ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ግምት ሁለቱን ያላግባባው ሥርዓተ ጸሎት ሳይሆን አይቀርም:: በዚያ ጊዜ በዋልድባ የሚጸለየው በቀን ሰባት ጊዜ ነበር:: አባ ጊዮርጊስ ደግሞ ሰባት ጊዜ በቀን መጸለዩ ለእግዚአብሔር ያንሰዋል ብሎ ያምን ነበር:: ምናልባትም በዚያን ጊዜ 22 ሰዓት የሚፈጀውን ሰዓታት ሳያዘጋጅ አልቀረም::

[7] ገድለ አባ ጊዮርጊስ፣ ገጽ 57

ከዚህ በኋላ የአባ ጊዮርጊስ ዋናው ትኩረቱ በድርሰቱ ላይ ሆነ፡፡ ወደ ጳጳሱ ወደ አቡነ በርተሎሜዎስ ዘንድ በመሔድ የቅዳሴ ድርሰት ለመድረስ እንዲ ፈቀድለት ከጠየቀ በኋላ የቅዳሴ ድርሰት ማዘጋጀቱን ገድሉ ይገልጣል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ቅዳሴያት ደራሲያቸው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ፍንጭ የሚሰጠን ይሆናል፡፡ ገድሉ እንደሚተርከው አንዳንድ ካህናት የአባ ጊዮርጊስን ቅዳሴ ተቃውመው ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አርዮስን በቀጣ በት መንገድ ቀጥቷቸዋል፡፡ አባ ጊዮርጊስ የቅዳሴዎቹን ስሞች በታወቁት የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስሞች የሰየማቸው ይህንን ተቃውሞ ለማለፍ ይሆናል፡፡

አባ ጊዮርጊስ ነገረ ሃይማኖት ጠንቅቆ የተረዳና የሚያስረዳ ስለነበር በዘመኑ የተነሡ የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ እርሱ ከሌለ አይሳኩም ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ በሸዋ በይፋት ራሳቸውን ቤተ እስራኤል እያሉ የሚጠሩ አይሁድ ነበሩ፡፡ ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጀምሮ ብዙ መምህራን ወደነዚህ ሕዝቦች እየተሠማሩ ወንጌልን አስተምረዋል፡፡ አቡነ ዜና ማርቆስ ወደ ክርስትና ለተመለሱት ቤተ እስራኤላውያን በእመቤታችን፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በአባ ኖብና በሰማዕቱ በጊጋር ስም አራት አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተው ነበር፡፡ ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ አሁንም አሉ፡፡ ይህ ሁሉ ቢሆንም ቤተ እስራኤላውያን ሙሉ በሙሉ ወደ ክርስትና አልተመለሱም ነበር፡፡

ከእነዚህ አይሁድ መካከል አንዱ ከክርስቲያኖች ጋር በነገረ ሃይማኖት ለመከራከር ጥሪ አቀረበ፡፡ "ክርስቲያኖች ከረቱኝ ወደነርሱ ሃይማኖት እገባለሁ፤ እኔ ከረታኋቸውም ወደኔ ሃይማኖት ይገባሉ፡፡" ሲል ነገሩን ጥብቅ አደረገው፡፡ ዐፄ ዳዊት ይህን ጉዳይ ሲሰማ በጣም ስለ ተናደደ ሊቃነ ካህናቱን፣ ንቡራነ እዱንና የመጻሕፍት ዐዋቂዎችን ሁሉ ከየሀገሩ እንዲሰባሰቡ አዘዘ፡፡ አይሁዳዊው በአንድ ወገን እነርሱም በሌላ ወገን ሆነው ክርክሩን ጀመሩ፡፡ የመጀመሪያው እድል የተሰጠው ለአይሁዳዊው በመሆኑ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ አቀረበ፡- "እናንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የምትሉት ይሄ ክርስቶስ እውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ፣ ወደ ቢታንያ በመጣ ጊዜ አልዓዛር የተቀበረበትን ቦታ ሳያውቅ ቀርቶ "አልዓዛርን የት ቀበራችሁት?" ብሎ እንደ ጠየቀ በወን





ጌላችሁ ተጽፏል፡፡ ለዚህ መልስ ስጡኝ፣ እኔንም ከመጽሐፈ ኦሪቴ ጠቅሳችሁ ጠይቁኝ?" ሲል የመከራከርያ ነጥቡን አቀረበ ፡፡

በዚህ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ታሞ አልጋ ላይ ነበር፡፡ ሊቃውንቱም እንዲህ ያለው ነገር ያለ እርሱ አይሆንምና አባ ጊዮርጊስ ይምጣ ሲሉ ለዐፄ ዳዊት ጥያቄ አቀረቡ፡፡ አባ ጊዮርጊስም በአልጋ ላይ እያለ እንዲመጣ ተደረገ ፡፡ በአልጋ ላይ ሆኖም በጉባኤው ላይ ተገኘ፡፡ ጉባኤተኞቹ የቀረበውን ጥያቄ ነገሩት፡፡ አባ ጊዮርጊስ የሰጠውን መልስ ገድሉ በሚከተለው መንገድ ይገልጥልናል "እኔ ግን በወንጌል ሳይሆን በኦሪት እከራከርሃለሁ፡፡ የምኩራብ መጻሕፍት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን የታወቁ ናቸውና፡፡ ምኩራብ ዘራች፣ ቤተ ክርስቲያንም አጨደችው፤ ምኩራብ ፈተለችው ቤተ ክርስቲያን ለበሰችው፤ አዳምን በገነት ሳለ "አዳም ሆይ ወዴት ነህ" ብሎ የጠየቀው ማነው? አብርሃምንስ "ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት" ብሎ የጠየቀው ማነው? እስቲ መልስልኝ፡፡ ሰይጣንንስ "ከወዴት መጣህ?" ብሎ የጠየቀው ማነው? እግዚአብሔር አብ አይደ ለምን?"» በዚህ ጊዜ አይሁዳዊው መልስ አጥቶ ዝም አለ፡፡ ንጉሡ፣ ሊቃውንቱና መኳንንቱም እጅግ ተደሰቱ፡፡

አባ ጊዮርጊስ ሌላው ያጋጠመው ተግዳሮት ‹ቢቱ› ከተባለው ሰው ጋር ያደረገው ክርክር ነበር፡፡ ቢቱ "በምጽአት ጊዜ የሚመጣው ወልድ ብቻውን እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ አይመጡም" የሚል ኑፋቄ ማስተማር ጀምሮ ነበር፡፡ «ቢቱ» ከዚህ ኑፋቄው በተጨማሪ የጥንቆላ ሥራም ይሠራ ነበር፡፡ ቢቱ በጥንቆላ ሥራው የተነሣ በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት የነበረው ሰው እንደ ነበር ገድሉ ይናገራል፡፡

ቢቱና አባ ጊዮርጊስ ወደ ንጉሥ ዳዊት ቀርበው በጉዳዩ ላይ መነጋገር እንደ ሚፈልጉ ገለጡ፡፡ ዐፄ ዳዊትም ጳጳሱ እንዲመጡ አዘዘ፡፡ በዚህ ጊዜ ተንኮለኛው ቢቱ ከአባ ጊዮርጊስ ጋር ከተከራከረ እንደሚረታ ስላወቀ «ንጉሡ የአባቶቻችንን ሃይማኖት ክዷልና አትምጣ» የሚል ደብዳቤ በአባ ጊዮርጊስ ስም ጽፎ ጳጳሱን ሊጠሩ በሄዱት መልእክተኞች እጅ ላከ፡፡ ወዲያውም ለዐፄ ዳዊት ይህንን ነገር አሳበቀ፡፡ ዐፄ ዳዊትም ፈጣን መልክተኞች ልኮ የፊተኞቹ መልእክተኞች እንዲመለሱ አደረገና ደብዳቤው ተነበበ፡፡ የቢቱ ተንኮል

ያልገባው ንጉሥ ዳዊት ይህን ደብዳቤ ሲመለከት አባ ጊዮርጊስ በደም አበላ እስኪነከር ድረስ እንዲደበደብ አድርጎ ወደ እስር ቤት አስገባው:: ዐፄ ዳዊት እስኪሞትና ልጁ ቴዎድሮስ እስኪነግሥ ድረስም አባ ጊዮርጊስ በዚያ ቆየ:: ቢቱ ግን በመልአክ ተቀሰፎ ሞተ::

አባ ጊዮርጊስ በወኅኒ ቤት እያለ ጴጥሮስና ጳውሎስ እየመጡ ያጽናኑት ነበር:: ውዳሴ ሐዋርያት የተሰኘውንና የሐዋርያትን ምስጋና የያዘውን መጽሐፍ ያዘጋጀው በወኅኒ በነበረ ጊዜ ነው:: አብዛኞቹ ድርሰቶቹን በዚህ ጊዜ ሳያዘጋጃቸው እንደ ማይቀር ይገመታል:: ዐፄ ዳዊት በሞተ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ እጅግ አድርጎ አዘነ:: እንዲያውም አንዳንዶቹ "በመሞቱ ደስ ልትሰኝ ይገባሃል እንጂ እንዴት ታለቅሳለህ?" ብለው ሲጠይቁት፣ አባ ጊዮርጊስ ግን "ጥቂት ቢኖር እወዳለሁ፤እመቤታችንን የሚወድ ሰው ነውና" ብሎ ነበር የመለሰው::

ዐፄ ቴዎድሮስ አባ ጊዮርጊስን ከወኅኒ ቤት አውጥቶ በጥንቱ ቦታ አስቀመጠው:: አባ ጊዮርጊስ ግን የቤተ መንግሥትን ነገር ለመሸሸ ስለ ፈለገ ቢጋስጫ ከመቀመጥ ይልቅ ርቆ ጥንት ወደ ነበረበት ወደ ዳሞት በመሄድ ማስተማር ጀመረ:: ወደ ዳሞት ሲሄድ እግረ መንገዱን ወደ ደብረ ሊባኖስ ገብቶ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን መቃብር ተሳልሟል:: በዚህ ጊዜ የደብረ ሊባኖሱ አበ ምኔት እጨጌ ዮሐንስ ከማ /ሰባተኛው የደብረ ሊባኖስ እጨጌ/ እንደነበረ ገድሉ ይናገራል::

ነገር ግን በዕውቀቱ የሚቀኑበት፣ በችሎታው የሚመቀኙት ሰዎች ነገር ሠርተው ከንጉሥ ቴዎድሮስ ጋር ስላጣሉት እልም ካለ በረሐ እንዲጋዝ ተደረገ:: አባ ጊዮርጊስ ከግዞት የወጣው ዐፄ ቴዎድሮስ ቀዳማዊ ሲሞት ነበር::

የአባ ጊዮርጊስ ሌላው ተማሪ የነበረው ዐፄ ይስሐቅ በ1399 ዓ.ም መንግሥቱን ሲይዝ አባ ጊዮርጊስን ከግዞት አውጥቶ ወደ ጋስጫ መለሰው:: በዚያ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ዕድሜው 42 ዓመት ሲሆን በስደትና በጤንነት መታወክ የተነሣ ከባድ ጉዳት ደርሶበት ነበር:: ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜውን በጾም፣ በጸሎትና በድርሰት ያውለው ነበር::





"ወበአሐቲ መዋዕል ተሰዕሎ አሐዱ መስፍን ዘስሙ ቴዎድሮስ ዘይሰመይ ካዕበ ሊቀ ሐራ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ወደረሰ ሎቱ መጽሐፍ ዘይሰመይ ፍካሬ ሃይማኖት:: ወሶበ ርእዮዎ ወአንበብዎ ለውእቱ መጽሐፍ ንጉሥ ወኩሎሙ ካህናተ ምሥጢር ይቤሉ አማንኪ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ወቄርሎስ አፈ በረከት ተንሥኡ በመዋዕሊነ:: ኢትዮጵያ ተመሰለት በቁስጥንጥንያ፣ ወተአረየታ ላዕለ እስክንድርያ - አንድ ቀን ቴዎድሮስ የተባለ መስፍን፣ ሁለተኛው የጦር አዛዥ፣ አባ ጊዮርጊስን ስለ ርትዕት ሃይማኖት ጠየቀው:: አባ ጊዮርጊስም ፍካሬ ሃይማኖት የተባለውን መጽሐፍ ደርሶ ሰጠው:: ንጉሡና የምሥጢር ሊቃውንት የሆኑ ካህናት ይህንን በተመለከቱና ባነበቡ ጊዜ «በእውነት ዮሐንስ አፈ ወርቅና አፈ በረከት የሆነው ቄርሎስ በዘመናችን ተነሥተዋል:: ኢትዮጵያም ቁስጥንጥንያን መስላለች፣ ከእስክንድርያም በላይ ከፍ ከፍ ብላለች ብለው» አደነቁ "ይላል ገድሉ አባ ጊዮርጊስ ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘውንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውንና የምታወግዘውን በግልጥና በዝርዝር የጻፈበትን መጽሐፍ እንዴት እንደ ደረሰው ሲገልጥ:: የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ፍካሬ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ታሪክ የመጀመሪያ ዓይነተኛ ሥራ ነው የሚል እምነት አለው::

አባ ጊዮርጊስ መከራ ያልተለየው አባት ነበር:: ገድሉ እንደሚተርከው በቤተ መንግ ሥቱ የነበሩ ሰዎች የርሱን መከበርና መወደድ አይፈልጉትም ነበር:: በተለይም ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘውን መጽሐፍ በመጻፉ የተነሣ መከበሩ አልተዋጠላቸውም:: ስለዚህም ነገር ሠርተው ከዐፄ ይስሐቅ ጋር አሁንም አጣሉት::

ዐፄ ይስሐቅ አባ ጊዮርጊስን አሣስሮ ውኃ ወደማይገኝበት ዐለታማ ቦታ አጋዘው:: በዚያም በመከራ ለብዙ ጊዜ ኖረ:: በዚያ እያለ ዘወትር በጸሎት አብዝቶ ይተጋ ነበር:: እግዚአ ብሔር ዐፄ ይስሐቅ ወደ ልቡናው እንዲመለስ አደረገ:: ንጉሡ በአባ ጊዮርጊስ ላይ የፈጸመው ነገር ሁሉ ፀፀተው:: አገልጋዮቹንም ጠርቶ አባ ጊዮርጊስን እንዲያመጡት አዘዘ:: ነገር ግን እነዚያ ተንኮል ሠሪዎች የአባ ጊዮርጊስ መምጣት ተንኮላቸውን ስለሚያጋልጠው አባ ጊዮርጊስ ሞቷል ብለው አስወሩ:: ይህንን ሲሰማ ዐፄ ይስሐቅ ፈጽሞ አዘነ::

አባ ጊዮርጊስ ሞቷል እየተባለ መወራቱን ከደቀ መዝሙሩ ስለ ሰማ በሕይወት የመኖሩን ዜና ጽፎ ለዐፄ ይስሐቅ እንዲያደርስለት አውሎ ንፋስን ላከው:: አውሎ ንፋሱ ደብዳቤውን ተሸክሞ በመሄድ ዐፄ ይስሐቅ በድንኳን ተቀምጦ በነበረ ጊዜ ጉልበቱ ላይ አስቀመጠው:: ንጉሡ ምትሐት የተሠራበት ስለ መሰለው ደንግጦና መኳንንቱንና ሕዝቡን ሰብስቦ ጉዳዩን ገለጠ:: ወዲያውም እሳት አስነድዶ ቢጥለው ሊቃጠል አልቻለም:: ወደ ውኃም ቢጨምረው አልጠፋም:: በዚህ ተደንቆ ወረቀቱን ከፍቶ አነበበው:: ደብዳቤው ከአባ ጊዮርጊስ የተላከ መሆኑን ሲያውቅ ዐፄ ይስሐቅ ደነገጠ:: እነዚያን መልክተኞች ይዞ ወደ ወኅኒ ጨመራቸው:: አባ ጊዮርጊስንም ከግዞት ያወጡት ዘንድ ላከ::

አባ ጊዮርጊስ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመጣ ንጉሡ በደስታ ተቀበለው:: ደብ ዳቤውን በማን እጅ እንደላከውም ጠየቀው:: አባ ጊዮርጊስም ደብዳቤውን በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ በነፋስ እንደ ላከው አስረዳ::

ከግዞት ከተመለሰ በኋላ እመቤታችን ተገልጣለት መከራው ሁሉ እንደ ሐዋ ርያት መሆኑን ገለጠችለት:: አእምሮውን ብሩህ፣ ልቡናውን ትጉህ የሚያደ ርግ እጅግ ብዙ ምሥጢር ነገረችው:: ተሰናብታው ከሄደች በኋላ «እጅግ ብዙ መብራት አቅርቡ፤ አምስት ፈጣን ጸሐፊዎችንም አምጡ» ብሎ አዘዘ:: እርሱ እየነገራቸው እነርሱ እየጻፉ እረፍት ሳያደርጉ ሦስት ቀን ሙሉ አስጽፎ መጽሐፈ ምሥጢር የተሰኘውን መጽሐፍ ፈጸመ:: አባ ጊዮርጊስ ይህንን ያደረ ገው ምናልባት በስደትና በመከራ ስለ ደከመ ሳይሆን አይቀርም:: አምስቱ ጸሐፍት የየድርሻቸውን አጠናቅቀው በአንድ አደረጉት:: አባ ጊዮርጊስም ይህን ተመልክቶ በእጅጉ አደነቀ:: "እኔ የዚህን መጽሐፍ ቃል አልተናገ ርኩም፤ መንፈስ ቅዱስ በእኔ አፍ ተናገረ እንጂ "ሲል በወቅቱ መመስከሩን ገድሉ ይናገራል::

ይህንም መጽሐፍ መጽሐፈ ምሥጢር ሲል ሰየመው:: የጻፈው በ1409 ዓ.ም ዕድሜው 52 በደረሰ ጊዜ ሲሆን የዚህ መጽሐፍ ቅጅ በነጋድያን እጅ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ በወቅቱ ሄዶ እንደ ነበር ገድሉ ያስረዳል::





መጽሐፈ ምሥጢር የተጻፈበትን ዘመንና ምክንያት የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ከዚህ በተለየ ነው የሚያስቀምጠው:: "በመዋዕሊሁ ለዝንቱ ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ኮነ ተቃሕዎ በእንተ ሃይማኖት ወተዋሥአ አባ ጊዮርጊስ ምስለ አሐዱ አፍርንጅ ወሞዓ እስከ ከሠተ ወጸሐፈ መጽሐፈ ምሥጢር - በዚህ በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት ክርክር ሆነ:: አባ ጊዮር ጊስ ከአንድ ፈረንጅ ጋር ተከራክሮ ረታው:: መጽሐፈ ምሥጢር የተባለውን መጽሐፍም ደረሰ"[8] ይላል:: ይህ ግን የሚያስኬድ አይመስልም:: ምክንያቱም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ዐርፎ ነበርና::

ዐፄ ይስሐቅ ለአባ ጊዮርጊስ ምድረ ሰዎን የተባለው የጳጳሳት መቀመጫ የነበ ረውን ሀገር በርስትነት ሰጥቶት ነበር:: አባ ጊዮርጊስ በምድረ ሰወን ንጉሥ ይስሐቅ ክረምቱን ያሳለፍበት በነበረው ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ሠራ:: በዚያም በማስተማርና በጾም በጸሎት ይተጋ ነበር:: በሥጋጫ እያለ ዐፄ ይስሐቅ አስጠራው:: በዚያ ጊዜ ንጉሡ የመናገሻ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ ስለ ነበር እንዲባርክለት ፈልጎ ነበር:: አባ ጊዮርጊስ ምንም እንኳን በዚያ ጊዜ ታምሞ የተኛም ቢሆን ወደ ንጉሡ ተጓዘ:: እዚያ ሲደርስ በጣም ተዳክሞ ነበር:: ሥርዓቱን ለመፈጸምም ዐቅም አልነበረውም:: ስለዚህም ንጉሥ ይስሐቅ በአልጋ ተሸክመውት እንዲያዞሩትና ቤተ ክርስቲያኗን እንዲ ባርካት አደረገ::

ቡራኬውን ከፈጸመ በኋላ ደቀ መዝሙሮቹን ሰብስቦ "ከሞትኩ አባቴ በጸሎት ሚካኤል መከራ ወደ ተቀበለባትና እኔም ቤተ ክርስቲያን ወዳነጽኩባት ቦታ ወስዳችሁ ቅበሩኝ" ሲል አዘዛቸው:: ለደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻ የስንብት ትምህርቱን እያስተማራቸው እርሱም በአልጋ ተሸክመውት ወደ ጋሥጫ እያመሩ ሳለ በመንገድ ላይ ሐምሌ ሰባት ቀን 1417 ዓ.ም በ60 ዓመቱ ዐረፈ:: ከመናገሻ ወደ ጋሥጫ የሚወስደው መንገድ በአዲስ አበባ በኩል አድርጎ፣ በደብረ ጽጌ በኩል ወጥቶ፣ በመርሐ ቤቴና በጉንደ መስቀል በኩል በማለፍ በሚዳና በወረም በኩል ወደ ቦረና የሚሻገር ይመስላል::

[8] J. Perruchon, Les Chroniques de Zar'a Ya'eqob et de Be'eda maryam, 1893, p 63

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በ1986 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሚዳ ጉንደ መስቀል ቤተ ክርስቲያን በተገኘ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ በመንገድ ላይ በማለፉ ለጊዜው ዐፅሙ ያረፈበትን ቦታ ካህናቱ በክብር ጠብቀው አሳይተውታል:: በገድሉም ላይ በዘመዶቹና በደቀ መዝሙሮቹ መካከል የት ይቀበር? በሚለው ጉዳይ ላይ ክርክር በመነሣቱና ንጉሡ በገዳሙ እንዲቀበር መወሰኑን ይገልጣል:: ከዚህም በላይ ደግሞ ክርክሩ አልቆ ዐፅሙ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እስኪገባ ድረስ በሌላ ቦታ ዐፅሙ ዐርፎ መቆየቱን ገድሉ ጨምሮ ይገልጣል:: በመ ሆኑም ያረፈበት ቦታ ጉንደ መስቀል ሳይሆን አይቀርም::

እስካሁን ድረስ ያሉት ምንጮች የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ቁጥራቸው ከዐርባ በላይ እንደ ሆነ ይገልጣሉ:: በስም የምናውቃቸው ግን የሚከተሉትን ብቻ ነው:: ምናልባት ብዙ ጥናት ማድረግ ሳያስፈልገን አይቀርም።

1 ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት

2.ኆኅተ ብርሃን/ከመጽሐፈ አርጋኖን ጋር አብሮ ታትሟል /

3. ውዳሴ መስቀል

4. ቅዳሴ

5. ውዳሴ ሐዋርያት

6. አርጋኖን ውዳሴ

7. ፍካሬ ሃይማኖት

8. መጽሐፈ ምሥጢር

9. ውዳሴ ስብሐት

10. እንዚራ ስብሐት

11. ሕይወተ ማርያም

12. ተአምኖ ቅዱሳን

13. መጽሐፈ ብርሃን

14. ጸሎት ዘቤት ቤት





# ስለ ‹ውዳሴ መስቀል›

ኢትዮጵያ ውስጥ ከተነሡት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በድርሰቱ ጣዕምና ብዛት ተወዳዳሪ የሌለው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ «ውዳሴ መስቀል» የተሰኘ መስቀልን የሚያከብር ድርሰት መድረሱን ገድሉ እንዲህ ይነግረናል:: «ዳግመ ኛም ከዕለታት በአንድ ቀን ጴጥሮስና ጳውሎስ ወደ እርሱ መጡ፤ መስቀ ሉንም አምጥተው በፊቱ አስቀመጡ:: የመስቀሉም ቁመት እስከ ራሱ ደረሰ:: የመስቀሉም ሁለት ክንፎች በሁለቱ ትከሻዎቹ ልክ ሆኑ::

ያን ጊዜም ከሰማይ ‹እንደበትህ እንደ ጴጥሮስና ጳውሎስ እንደበት፣ ሥልጣን ህም እንደ ሥልጣናቸው ይሁን::› የሚል ቃል ሰማ:: ያን ጊዜም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በልቡ በራ:: ውዳሴ መስቀል የሚባል መጽሐፉንም ደረሰ[9]::» ይለናል::

አባ ጊዮርጊስ ይህንን ደርሰት እንዲደርስ ያደረጉት ሁለት ምክንያቶች ሳይኖሩ አይቀሩም:: የመጀመርያው ከዐፄ ንዋየ ማርያም ዘመን ጀምሮ በአንዳንድ አካላት ዘንድ የተፈጠረው ‹ለመስቀል ክብርና ስግደት አይገባውም› የሚለው አስተሳሰብ ነው:: አባ ጊዮርጊስ ይህንን ሐሳብ የሚቃወምና ለመስቀሉ ሊሰጥ የሚገባውን ክብርና ምስጋና የሚገልጥ ድርሰት በመድረስ የቤተ ክርስቲያ ኒቱን አቋም ገልጧል::

ሁለተኛው ደግሞ መስቀልንና ድንግል ማርያምን በተመለከተ የማን ክብር ይበልጣል? የሚል ክርክር በእርሱ ዘመን ተነሥቶ ስለ ነበር ነው:: በመጽሐፈ ምሥጢር ድርሰቱ ላይ «ደግሞም ሰዎች ስለ ማርያምና ስለ መስቀል እንደ ተሳሳቱ በጆሮዎቻችን የሚሮጥ ዜና አለ:: ከፊሎቹ የወለደችው ማርያም ከመ ስቀሉ ትበልጣለች ይላሉ፤ ከፊሎቹ ደግሞ በሕማመ መስቀሉ የተጠመቀው መስቀል ይበልጣል ይላሉ:: እኛ ግን ማርያምን ወላዲተ አምላክ እንደሆነች፣ መስቀሉንም በመለኮት ትስብእት በደሙ የተዋጀ የተቀደሰ የብርሃን ምልክት

[9] ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ(፳፻፱ ዓም)፣ ገጽ ፶፮ና ፶፯

መሆኑን እናምናለን[10]» በማለት የነበረውን ክርክርና የአባ ጊዮርጊ ስንም አቋም ይገልጥልናል።

አባ ጊዮርጊስ እመቤታችንን በተመለከተ አርጋኖን ድንግል፣ ሕይወተ ማርያም፣ ኆኅተ ብርሃን፣ እንዚራ ስብሐት የተሰኙ መጻሕፍትን ደርሷል። በዚህ ‹ውዳሴ መስቀል› በተሰኘው ድርሰቱ ደግሞ ቅዱስ መስቀልን በተመለከተ ያለውን አክብሮትና አስተምህሮ ገልጧል።

በዘመነ ዐፄ ዳዊትና በዘመነ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋር በተያዘ መስቀልንና እመቤታችን ለማክበር ይበልጥ ትኩረት ያገኘበት ጊዜ ነበር። ከአባ ጊዮርጊስ ውዳሴ መስቀል በተጨማሪ ‹መስተበቊዕ ዘመስቀል› በዚያን ጊዜ የተደረሰ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ትእዛዝ በልብስ፣ በቤትና በመሣርያ ላይ የመስቀል ምልክት ማድረግ ተዘውትሮ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ያ ዘመን ግማደ መስቀሉ በዐፄ ዳዊት ዘመን መጥቶ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ወደ ግሼን አምባ የገባበት ጊዜም ነው።

ይህ ***ውዳሴ መስቀል*** የተሰኘው ድርሰት የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት መሆኑን ከገድሉና ከመጽሐፈ ምሥጢር በተጨማሪ በድርሰቱ ውስጥ ፍንጭ የሚሰጡ ነገሮችም አሉ።

አባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ አርጋኖንና ውዳሴ መስቀልን የዘጋበት መንገድ ተመሳሳይ ነው። በሁለቱም ድርሰቶች ላይ ከአዳም አንሥቶ እስከ ዘመኑ ያሉትን ቅዱሳን በማመስገን ነው የሚዘጋው። በአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ውስጥ በስፋት ለበጎ ነገር ምሳሌነት የሚውሉት ‹መሰንቆና እንዚራ› በውዳሴ መስቀልም ላይ በስፋት ጥቅም ላይ ውለዋል።

‹አባ ጊዮርጊስ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ሊቅ ብቻ ሳይሆን ሐሳቡን ለመግለጥ አዳዲስ የግእዝ ቃላትን የሚፈጥርም ሊቅ ነው› ይላሉ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ። ለምሳሌ «መጻእርት» የሚለውን ቃል የምናገኘው በአባ ጊዮርጊስ

[10] ኅሩይ ኤርምያስ፣ መጽሐፈ ምሥጢር፣ 2001 ዓም፣ ገጽ 5





ድርሰቶች በመጽሐፈ ምሥጢርና በውዳሴ መስቀል ላይ ነው። ይህ ጉዳይ የሁለቱም ድርሰቶች ደራሲ አንድ ሰው መሆኑን ያመለክተናል።

የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ከአርጋኖን፣ ከመጽሐፈ ምሥጢርና ከመጽሐፈ ሰዓታት በቀር ሌሎቹ በሰፊው አልታወቁለትም። መጽሐፈ ምሥጢርም ቢሆን በውጭው ዓለም የታወቀውን ያህል በሀገር ውስጥ አልታወቀም ነበር። አሁን ግን ማኅበረ ቅዱሳንና ገዳሙ መጽሐፉን ወደ አማርኛ በመተርጎም ስላቀረቡት ዛሬ ዛሬ በየትምህርቱና ድርሰቱ የሚጠቀስ መጽሐፍ ሆኗል። ውዳሴ መስቀል በአባ ጊዮርጊስ መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ካልሆነ በቀር በስፋት አይታወቅም።

ይህ አሁን በአማርኛና በግእዝ የቀረበው መጽሐፍም አንዱ ዓላማው ሊቃውንቱና ምእመናኑ በቀላሉ ለማግኘትና ለማንበብ እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

ለዚህ ሥራ የተጠቀምኩት ጌታቸው ኃይሌ በግእዝና በእንግሊዝኛ ከመግቢያና ከግርጌ ማስተዋሻ ጋር ያዘጋጁትን ነው[11]። እርሳቸው የተጠቀሙት በEMML 5041 የሚገኘውንና በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት[12] ፍሥሐ ክርስቶስ ለተባለ ሰው የተገለበጠውን ቅጅ ነው። ይህንን ቅጅ እኔ በ1988 ዓም ካገኘሁት ሌላ ቅጅ ጋር ለማስተያየትም ሞክሬያለሁ። ካስጻፉት ሰዎች ስም በቀር ሌላው ተመሳሳይ ነው። እኔ ያገኘሁት ቅጅ ምናልባት የ18ኛው መክዘ ሳይሆን አይቀርም። በዋነኛነት በትርጉም ሥራው EMML 5041ን የተጠቀምኩት ለታሪካዊነቱ ስል ነው። በዚሁ አጋጣሚ ጥንታዊ የግእዝ መዛግብትን ለዓለም ለማሳወቅ ለሚደክሙት ለፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ዕድሜ ከጤና እለምንላቸዋለሁ።

በመጽሐፉ ውስጥ ለአንቀጾቹ እኔ ቁጥር ሰጥቻቸዋለሁ፤ ይኼውም አንባቢ ግእዙን ከአማርኛው ለማነጻጸር፣ ብሎም እግረ መንገዱን የግእዙን ትርጉም

[11] Praises of the Cross, wədase mäsqäl, by Abba Giyorgis of Gasečča ውዳሴ መስቀል፣International Journal of Ethiopian and Eritrean studies (Æthiopica14 (2011))

[12] 1500-1533 ዓም

ለማጥናት እንዲመቸው ነው። እንዳይቸግር ብዬ ነው። ምዕራፎቹን በተመለከተ እኔ ያገኘሁትን ቅጅ ተከትያለሁ። የግእዙ ጽሑፍ በብራናው ያለውን የፊደል አጠቃቀም እንዳለ እንዲከተል ትቼዋለሁ። የአማርኛውን ትርጉም ግን በኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሥርዓት አስቀምጬዋለሁ።





# ክፍል አንድ - ግእዝ

## ፩

(፩)በስመ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ዘእንበለ ትማልም፤

ወማእከላዊ ዘእንበለ ዮም፤

ወደኃራዊ ዘእንበለ ጌሰም፤

ብሉየ መዋዕል ዘእንበለ ዓም፤

ገባሬ ኵሉ ዘእንበለ ድካም፤

ባሕረ ምሕረት ዘእንበለ አቅም፤

(፪)ንጽሕፍ እንከ ውዳሴ መስቀል ዘከመ እፎ ውእቱ ዕበያቲሁ፤

ወናየድዕ እንከ ስብሐቲሁ፤

ዘከመ እፎ ተነግረ እምቅድም ዜናሁ።

መስቀል ዕፀ ሕይወት፤

መስቀል ዕፀ መድኃኒት፤

መስቀል ዕፀ ተነብዮ፤

መስቀል ዕፀ አንሕዮ፤

(፫)መስቀል ጒድበ ሙስና ዲበ ሰይጣን፤ ወሰይፈ ሙቃየ አርእስቲሆሙ ለአጋንንት፤

መስቀል ረምኃ እሳት ዘይረግዘሙ ለመናፍስት ርኩሳን፤ ወሐፀ መብረቅ ዘይደጕዮሙ ለሠራዊተ መስቴማ።

መስቀል ፀወን ዘኢይክል በጺሐ ኀቤሁ ዘኢነሥአ ማኅተመ ሥላሴ።

መስቀል ወልታ ጽድቅ ዘእምየማን ወእም ጺጋም።

መስቀል ንዋየ ሐቅል ለፀብዕ በከመ ይቤ ጳውሎስ ሐዋርያ እስመ ቀትልክሙ ኢኮነ ምስለ ዘሥጋ ወደም።

መስቀል ጽርዐ ሃይማኖት ዘኢይክል ሰጢጦቶ ሥጽረተ ሐፅ ወኢደርብዮቶ ኵያንው ወአርማን።

መስቀል ዘተገብረ በአምሳሊሁ ለእደ ሙሴ በገዳመ ራፊድ በእንተ ፀብዐ አማሌቅ።

መስቀል ዘአጥዐሞ ለማይ መሪር በገዳመ ሱር ሶበ ተወድየ ውስቴቱ በእደ ሙሴ።

መስቀል ማኅተመ ቅድስና ወንጽሕ።

መስቀል አክሊለ መዊዕ ዘመስተጋድላን ወሠርጐ ትርሲት ለእለ ተዓሥሩ ውስተ መርዐ በግዑ።

መስቀል ነቅዕ ዘኢይነጽፍ ወአዘቅተ ክብር ዘምሉዕ ረባሐ።

(፬) መስቀል ዕፀ ገነት ዘይሰቅይዎ ፬ አፍላግ፤ ስሙ ለ፩ ፈለግ ኤፌሶን ዘእምኔሁ ይውኅዝ ወይነ ምስጢር አስተዳለወ እግዚአብሔር ለቅዱሳኒሁ። ወፈለግ ካልዕ ግዮን ዘእምኔሁ ይውኅዝ ጺቃውዐ መዓር ከፍለ ንጹሓን። ስሙ ለሣልስ ፈለግ ጤሮስ ዘእምኔሁ ይውኅዝ ቅብዐ ዘይት ለአጽሕዶ ሥጋሆሙ ለመስተጋድላን። ስሙ ለራብዕ ፈለግ ኤፍራጥስ ዘእምኔሁ ይውኅዝ ሐሊበ ልቡና ዘውእቱ ሰቴ ፍሥሐ ወሐሤት።

መኑ ውእቱ ፈለገ ወይን ወመኑ ውእቱ ፈለገ መዓር፤ ወመኑ ውእቱ ፈለገ ቅብዕ፤ ወመኑ ውእቱ ፈለገ ሐሊብ፤ ዘእንበለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰምየ እንከ





ፈለገ ወይን። እስመ ወይነ ትፍሥሕት ዘውኅዘ እምገቦሁ፤ በከመ ይቤ ዳዊት ወወደይከ ትፍሥሕተ ውስተ ልብነ እምፍሬ ስርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኅ። ወቅብዕ ለአብርሆ ገጽ።

(፭)አርአየ እንከ ነቢይ ፫ ጽምረተ ውስተ ፩ ቃል። እምፍሬ ስርናይ ወወይን ዘይቤ በእንተ ቍርባነ ሥጋሁ ወደሙ ለወልደ እግዚአብሔር። ወቅብዕ ለአብርሆ ገጽ ዘይቤ በእንተ ቅብዐ በለሳን ዘተውኅበ ለማኅተመ ጥምቀት። ዝውእቱ አርውአያ ጽሕደቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ። ወኵሉ ዘሀሎ በአሚነ ዚአሁ ኢስሕከ ውእቱ ወይጽሕድ እም ሜላት። ወበእንተዝ እንከ ይትሐተም ዘቦአ ውስተ ዐቢይ ክርስቲያን በቅብዐ በለሳን በከመ ይለብስ ጽሕደቶ ኢየሱስ ክርስቶስ በከመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር ወሠራዕከ ማዕደ በቅድሜየ በአንጻ ሪሆሙ ለእለ ይሣቅዩኒ፤ ወአጽሐድከ በቅብዕ ርእስየ፤ ጽዋዕከኒ ጽኑዕ ወያረዊ። ይብል እንከ ጥንተ መዝሙር እግዚአብሔር ይሬእየኒ ወአልቦ ዘየኃጥአኒ። እስመ ዘየአምን በክርስቶስ መርዔተ ክርስቶስ ውእቱ። እግዚአብሔር ይሬእዮ ወአልቦ ዘየኃጥእ ምንተሂ እምፍኖተ መንፈስ ቅዱስ። ይደግም እንከ ወይብል ውስተ ብሔር ስዑር ህየ የኃድረኒ ወኀበ ማየ ዕረፍት ሐፀነኒ። ወሜጣ ለነ ፍስየ ወመርሐኒ ፍኖተ ጽድቅ፤ በእንተ ስመ ዚአሁ። ብሔር ስዑር ቤተ ክርስቲያን ይእቲ ጺአተ መራዕየ ክርስቶስ። ኀበ ማየ ዕረፍት ኀፀነኒ ብሂል ማየ ጥምቀት ውእቱ። ወሜጣ ለነፍስየ ወመርሐኒ ፍኖተ ጽድቅ ብሂል ሜጠኒ እም ኢያእምሮ ውስተ አእምሮ።

(፮)አማን በእንተ ስመ ዚአከ እመኒ ሖርኩ ማዕከለ ጽላሎተ ሞት ኢይፈርሆ ለእኩይ፤ እስመ አንተ ምስሌየ። ወኵሉኬ ዘየአምን በክርስቶስ ኢይፈርህ መዊተ በእንተ ስመ ዚአሁ፤ በከመ ይቤ በወንጌል ኵሉ እንከ ዘየአምን ብየ በቅድመ ሰብእ አአምኖ አነሂ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት። ወዘሰ ክህደኒ በቅድመ ገጸ ሰብእ ወአነሂ እክህዶ በቅድመ ገጸ አቡየ ዘበሰማያት። ይብል እንከ ነቢይ በትርከ ወቀስታምከ እማንቱ ገሠጻኒ። በትርከ ብሂል በትረ ሃይማኖት፤ በዘባቲ ንትመረጐዝ ከመ ኢንደቅ ውስተ ስሕጸተ ዕልዋን፤ ወቀስታምከኒ ዘይቤ ቀስታመ መስቀል፤ በዘይትጌሠጹ መሃይምናን ከመ ኢይሳተፎሙ ለንፉቃን።

(፯)ወሠራዕከ ማዕደ በቅድሜየ፤ ዘንተ እንከ ይነግር በእንተ ሥርዓተ ቍርባን። ወእምዝ ይብል ወአጽሐድከ በቅብዕ ርእስየ። ዘንተ ይነግር በእንተ ቅብዐ በለሳን። ትምህርተ ሐዋርያቲነ ይብል ወቅብዐ በለሳንሰ ኃይለ ሃይማኖት ውእቱ። ወበእንተዝ ተሰምየ መድኃኒነ ፈለገ ወይን ወፈለገ ቅብዕ። ወካዕበ ተሰምየ ፈለገ መዓር ወፈለገ ሐሊብ፤ እስመ አሰፈዎሙ ለአበዊነ ከመ የሀቦሙ ምድረ እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ። ወዝኒ ሥርዓተ ሐዲስ ውእቱ ዘውኅዘ እምገቦሁ ለመድኃኒነ፤ በከመ ይቤ ዳዊት ጥዑም ለጕርዔየ ነቢብከ። እመዓር መዓርዒር ወከሉ ፍትው። ወካዕበ ትብል በላዕኩ መዓርየ ምስለ ኅብስትየ፤ ሰተይኩ ወይንየ ምስለ ሐሊብየ በእንተ መሥዋዕተ ወንጌል ዘተሠርዐ እም ድኅረ በሊዐ ፍሥሐ አሪት። ያዕቆብኒ ይቤ ፍሡሓት እም ወይን አዕይንቲሁ፤ ወጸዓዳ ከመ ሐሊብ ሰነኒሁ። ወበዝ እንከ ተሰምየ አማኑኤል አምላክነ ፈለገ መዓር ወፈለገ ሐሊብ።

(፰)ንግባዕኬ ኀበ ዘቀዳሚ ነገር በእንተ ዕፀ ሕይወት ዘተተክለ ማዕከለ ዕፀወ ገነት። ዕፀ ሕይወትሰ መስቀል ውእቱ። ወዕፀወ ገነትኒ መሃይምናን እሙንቱ። ወህየንተ ሔዋን ዘአምጽአት መርገመ ላዕለ ርእሳ፣ ኢድምአት ድንግል በረከተ እምኀበ መልአክ። ወይቤላ ቡርክት አንቲ እም አንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ወህየንተ አዳም ዘበልዓ እምፍሬ ዕፀ በዓሊ ወትእዛዘ አምላክ ውእቱ፣ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰፍሐ እደዊሁ ዲበ ዕፀ መስቀል ተአዛዚ ከዊኖ ለቃለ አቡሁ። ወህየንተ ፬ አፍላግ ዘይወፅኡ እም ውስተ ገነት ወይትፈለጡ ለ፬ መዓዝነ ዓለም፣ ፬ወንጌላት ቅዱሳት ዘተሰብኩ ውስተ ፬ መዓዝነ ዓለም።

(፱)ኦ አመቂሁ ለብዕለ ጥበቢሁ ለእግዚአብሔር፤ እም ቅድመ ይፍጥሮ ለአቡነ አዳም አስተዳለወ ሎቱ ዘይሴሰይ ወኵሎ መፍቅደ ዘይደሉ ለአጓለ እመ ሕያው። እምቅድመ ይትወለዱ ጻድቃን አስተዳለወ ገነተ ትፍሥሕት። ወዘእንበለ ይትወለዱ ኃጥአን አስተዳለወ ገሃነመ በዘይጼአሩ፤ እም ቅድመ ይፍጥሮሙ አእመረ ምግባሮሙ። ወዘእንበለ ይፃኡ እምከርሠ እሞሙ አስተዳለወ ማኅደሮሙ በከመ ይቤ ለሊሁ በኪዳን እም ቅድመ ሕሊና ኵሎ የአምር። ወእም ቅድመ ሕሊና ይፈትን። ዳዊትኒ ይቤ እንዘ ይዜኑ ከመ የአምር ምግባሮሙ ለኃጥአን እምቅድመ ይግበሩ ተነከሩ ኃጥአን እማኅፀን፤ እምከርሥ





ስሕቱ ወነበቡ ሐሰተ። ዘንተ እንከ ይብል ነቢይ በእንተ እማሬ ኃጢአቶሙ ለሐሳውያን እምቅድመ ይፃኡ እምከርሠ እሞሙ።

(፲)በውስተ ከርሥ እንከ ምስለ መኑ ተናገሩ። ወምስለ መኑ ነበቡ ሐሰተ። ወበእንተ እማሬ ጽድቆሙ ለቅዱሳን በኀበ እግዚአብሔር ንንግር እስመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለኤርምያስ ዘእንበለ ትፃእ እምከርሠ እምከ አእመርኩከ ወዘእንበለ እፍጥርከ ቀደስኩከ። ወበነቢይኒ ይቤ ያዕቆብሃ አፍቀርኩ ወዔሳውሃ ጸላእኩ ዘእንበለ ይትፈለጥ ምግባሮሙ ለክልኤሆሙ ወዘእንበለ ይሢጥ ዔሳው ብኵርናሁ ለያዕቆብ። ይቤላ እግዚአብሔር ለርብቃ ፪ቱ ሕዝብ ሀለዉ ውስተ ከርሥኪ ወ፪ቱ ሕዝብ ይወፅኡ እም ውስተ ከርሥኪ ወሕዝብ እምነ ሕዝብ ይኄይስ። ወዘይልሕቅ ይትቀነይ ለዘይንእስ።

(፲፩)ወለሔዋን ሰመያ ሕይወተ በእንተ ቅድስት ድንግል ማርያም፤ እስመ አእመረ ፈጣሪ ከመ እምኔሃ ይወፅእ ሕይወተ ኵሉ ዓለም። ወለዕፀኒ ዘሀሎ ውስተ ዕፀወ ገነት ሰመዮ ዕፀ ሕይወት፤ እስመ አእመረ ከመ በመስቀሉ የሐዩ ኵሉ ዓለም። ወዕፀ ሕይወትሰ ቀዲሙኒ ተተክለ ማዕከለ ዕፀወ ገነት በእደ አምላክ። ወበቀራንዮኒ ተተክለ በእደ አይሁድ መስቀለ አምላክ። መስቀለ አምላክ አቅረቡ አይሁድ እም ዘእሁ ለዚእሁ። በዘለሊሁ ፈቀደ አሕመምዎ፤ እስመ ውእቱ ሠምረ ከመ ይቅትልዎ። ሎሙሰ መሰሎሙ ከመ ይደምሰስ ዝክሮ እምገጸ ምድር። ወኢያእመሩ ከመ በመስቀሉ ይሰደዱ፤ ወበትንሣኤሁ ይትፈለጡ።

(፲፪)ኦ ጥቀ ዕፁብ ዘተሰቅለ ይመውዕ ወእለሰ ሰቀሉ ይትመውኡ። ኦ ጥቀ መንክር ዘሞተ ያስተኃፍር ወእለ ቀተሉ ይትኀፈሩ። ኦ ጥቀ መድምም ዘሐመ ያኀስር። ወእለ አሕመምዎ ለብሱ ኃሣረ። ለዕፀ ዘተከሉ ተሰዱ። ወለብእሲ ዘሰቀሉ ተዘርዉ። ፈትሑ ላዕሌሁ ሊቀ ካህናት እንዘ ይብሉ ሕገ ብነ፤ ወበሕግነ ርቱዕ ይሙት፤ እስመ ወልደ እግዚአብሔር ረሰየ ርእሶ። ሎሙሰ መሰሎሙ ዘይቀንኡ ለእግዚአብሔር ወለኦሪተ ሙሴ። መኑኬ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእንበለ ዘሰቀልዎ። ወመኑ ውእቱ መጣዌ ኦሪት ዘእንበለ ዘሰቀልዎ። አፍቀርዎ በአፉሆሙ ወሐሰውዎ በልሳኖሙ። ወእንዘ ይፈቅዱ ይንበቡ ህሰወ ወነበቡ ህልወ። አማንኬ ዘይቤሉ ሕገ ብነ፤ ወበሕግነ ርቱዕ ይሙት፤ እስመ ይቤ ሙሴ

በውስተ ሕግ ትሬእይዎ ለመድኃኒትከሙ ስቁለ ዲበ ዕፀ። ሕገ በሙ ከመ ይርከቡ ፀሐየ ከመ ኢያንሶስዉ በብርሃኑ። ሕገ በሙ ከመ ይደይዎ ለሕይወት ውስተ ሞት ወኢይገብሩ በዘየሐይዉ። ሕገ በሙ ከመ ይጥብሕዎ ለበግዕ ወኢይጥዕሙ እምጥቢሑ። ሕገ በሙ ከመ ይቅድሑ ወይነ ምሥጢር ወኢይሰትይዎ። ይቤ ቀያፋ ይኄይሰነ ፩ደ ብእሲ ንቅትል እምይትኃጐሉ ሕዝብ ወኵሉ ዓለም።

(፲፫)አማንከ ይደሉ ከመ ይቅትልዎ ለወልደ እግዚአብሔር፤ እስመ ቦቱ የሐይዎሙ ለሙታን። አማንከ ይደሉ ከመ ይሰቅልዎ ለወልደ እግዚአብሔር፤ እስመ በመስቀሉ ይቄድሶ ለዓለም። ወለእመ ኢተሰቅለ እመ ኢድኅነ። ወለእመ ኢሞተ እመ ኢሐየውነ። ወስኂተ ዚአሆሙ ብዕለ ኮነ ለአሕዛብ። አዕረቅዎ ሥጋሁ ለሰቂል፤ እስመ ኢይደልዎ ለማኅቶት ተከድኖ ልብስ። አላ ይደሉ ነቢረ ዲበ ተቅዋሙ ከመ ያስተርኢ ብርሃኑ ለእለይፈቅድዎ። አዕረግዎ ዲበ ዕፀ መስቀል፤ እስመ ኢይደልዎ ካዕበ ለማኅቶት ነቢረ ውስተ ምድር። ዳዕሙ ይደሉ ከመ ይትሌዓል ውስተ መራን ከመ ያብርህ ሎሙ ለእለ ያንሶስዉ በብርሃኑ በከመ ይቤ ለሊሁ በወንጌል ወኢየሐቱ ማኅቶተ ከመ ይሢምዋ ታሕተ ከመ ይክድንዋ ታሕተ ከፈር ዘእንበለ ከመ ያንብርዋ ዲበ ተቅዋማ ወታበርህ ለኵሉ ሰብእ።

(፲፬)ተቅዋምሰ መስቀል ውእቱ። ማኅቶትኒ አማኑኤል ውእቱ። ናንሶሱ እንከ በብርሃኑ ለወልደ እግዚአብሔር። ወኵሉ ዘየአምን ኪያሁ ውስተ ብርሃን የሐውር። ወጽልመትኒ ኢይረከቦ። ወበእንተዝ እጸርኅ እንከ ኀቤሁ ምስለ ዳዊት ነቢይ እንዘ እብል በብርሃንከ ንርአይ ብርሃነ ወበጽድቅከ ንርዓይ ገጸከ። ወካዕበ ዕብል ኖን ማኅቶት ለእገርየ ሕግከ። ብርሃን ለፍኖትየ። ወዓዲ እጸርኅ ምስለ ኢሳይያስ ነቢይ እንዘ ዕብል ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር።

(፲፭)ወይእዜኒ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አርኢ ብርሃነ ገጽከ ላዕሌየ። ወከሥት አፉየ ለስብሐተ መስቀልከ ቅዱስ። በስመ መስቀልከ ሐፀር ጥቅማ ለነፍስየ። ወአጽንዖ ሥጋየ ውስተ ሥጋከ ቅዱስ መለኮታዊ። ኦ ዘከረ ልዕልና፤ ይእዜሰ እከሥትከ፤ መኑ አንተ ዘደመርከ መለኮተከ በፍጥረተ ትስብእትነ መዋቲ፤ ወረሰይከ ፩ደ ምስለ መለኮትከ ዘኢይመውት ወዘኢይማስን።





(፲፮)በስመ መስቀል ምሥጢር ኅቡዕ ዘኢይትነገር ባቲ ልሳነ እጓለ እመሕያው።

በስመ መስቀል ምሥጢር ኅቡዕ ዘይዘርዎሙ ለማኅበረ ሰቃልያን።

በስመ መስቀል ምሥጢር ኅቡዕ ዘይቀጠቅጥ ርእሰ ከይሲ። ቀጥቅጥ ወአጽብብ ኃይሎሙ ለእለ ይትቃወምዋ ለነፍስየ። ወረስየኒ እትፌሣሕ በድቀተ ጸላእትየ ሊተ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ። ለዓለመ ዓለም አሜን።

## ፯

(፲፯)ኦ ዘበመስቀልከ አሕሰርኮ ለዕቡይ ከመ ቅቱል፣ ቅትሎ ኃጢአተ እንተ ኃደረት ላዕሌየ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።

ኦ ዘበመስቀልከ ሰረውካሁ ለጽልመት፣ ስርዎሙ ለጸርየ ወጥስዮሙ እምዓለም ከመ ኢይትረከብ ዝክሮሙ ከመ በህዱእ ወበጽምው ይኩን ንብረትየ ሊተ ለገብርከ።

ኦ ዘበመስቀል ነጸሕኮ ለተኵላ ወአንገፍከ በግዐ እምአፉሁ፣ ወአንግፈኒ እምእደ ጸላእትየ ሊተ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።

ኦ ዘበመስቀልከ አረቆ ለሰብእ ምስለ አቡከ ሰማያዊ፣ ኢታርኅቅ እምኔየ ሰላመ እንተ እምኀቤከ ሊተ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።

ኦ ዘበመስቀልከ ወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቀስት፣ ግበር ምስሌየ ትእምርተ ለሠናይ ወይርአዩ ጸላእትየ ወይትኃፈሩ ከመ አንተ እግዚኦ ረዳእከነ ወአስተፍሣሕከነ።

ኦ ዘበመስቀልከ ነአውኮ ለአርዌ ዘይትኄየል ወሰሐውኮ በሐፃውንተ ቅንዋቲከ፣ ሰሐጦሙ ለእለ ይፈቅዱ አሕስሞ ላዕሌየ ሊተ ለገብርከ።

ኦ ዘበመስቀልከ ፀባዕኮ ለቤልሆር ወሞኦከ ላዕሌሁ ኃፍረተ፣ ወአልብሶሙ ኃሣረ ለጸላእትየ ሊተ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።

አ ዘበመስቀልከ ሥዓርከ ፅንዐ ዕቡያን ወአዕበይከ ጸሎተ ቅዱሳን፣ ጸግወኒ ዕበየ እምነቤከ።

አ ዘበመስቀልከ አተብካ ለቤተ ክርስቲያንከ ወቀደስካ በስምከ ወሀፀብካ በማይ ዘውኅዘ እም ገቦከ፣ ሕፅበኒ ወአንጽሐኒ እም ኃጢአትየ፤ ወእም አበሳየኒ አንጽሐኒ።

አ ዘበመስቀልከ አፃመውካ ለሲኦል ወነሰትካ፣ ንስት አጽዋኒሆሙ ለእለ ይትሄየሉ ላዕሌየ ሊተ።

አ ዘበመስቀልከ ሜጥኮ ለፈያታዊ ዘየማን ውስተ አሚን ዚአከ ወረሰይኮ ቀዳማዊ በዊአ ውስተ መንግሥተ ሰማያት፣ አብእኒ ውስተ ጽርኀ ተድላሆሙ ለቅዱሳን ሊተ።

አ ዘበመስቀልከ ረሰይኮሙ ለአባግዒከ ስቡሐን፣ ወሐተምኮሙ በነጸፍጸፈ ደምከ ክቡር፣ ሀበኒ ሊተ ማኅተመ ጸልቦከ ማኅየዊ ከመ ማኅተመ ዚአከ ጸዊርየ ግሩመ ውኩይ ዲበ ኀይለ ጸላዒ።

አ ዘበመስቀልከ አሰሰልከ ኵናተ እሳት እምኢደ ሱራፌል ወሰይፈ ዘይበርቅ እምኢደ ኪሩቤል እለ የዐቅቡ አንቀጸ ገነት፣ ወአባሕኮ ለአዳም ከመ ይባዕ ዐፀደ ገነት ዘእምኔሁ ወፅአ፣ አብሀኒ ሊተ በዊአ ውስተ ርስቶሙ ለቅዱሳን፤ እስመ አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ አሠነይከ ዓለመ ዘማሰነ ወሐደስከ ዓለመ ዘበልየ ወቀደስከ ዓለመ ዘረስሐ፣ ሐድስ ነፍስየ ወሥጋየ ሊተ።

አ ዘበመስቀልከ አጽገይካ ለዓፀደ ወይንከ እንተ ተተክለት በየማንከ ቅዱስ፣ ወረሰይካ ትፍረይ መሃይምናነ፣ ረስየኒ አጽገይ ጽጌ ሃይማኖት ወእፍረይ ፍሬ ንስሐ አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ ፈደይከ እዳሃ ለሔዋን፣ ወአግዓዝኮ ለአዳም እምጻዕረ ሞት፣ አግዕዘኒ ሊተኒ እምአርዑተ ኃጢአት ከመ እትቀነይ ለከ በንጹሕ ልብ አነ ገብርከ።





አ ዘበመስቀልከ መራሕኮሙ ለሐዋርያቲከ ቅዱሳን፣ ምርሐኒ ፍኖተ ርትዕት እንተ ባቲ አሐውር አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ አባሕኮሙ ይኪዱ ኵሎ ኃይለ ጸላኢ፣ ወአሰልጠንኮሙ ከመ ያልስሑ ኅምዘ አፍአት ወአቃርብት፣ ኅበኒ ከመ አልስሕ ሥልጣኖ ለሰማልያል ሳጥና አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ ተሣየጥከ ሕዝበከ እምኀርማ ለአሪት፣ ኢትግድፈኒ ሊተ ለሤጠ ደምከ አላ ረስየኒ ጽሙደ ለአርዑተ ወንጌልከ ቅዱስ ከመ እትመካህ በመስቀልከ አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ ፈታሕኮሙ ለእለ በሙቃሔ ሰይጣን ስንሱላን፣ ፍትሐኒ ሊተ እማዕሠረ ኃጢአት ዘኢይት ፈታሕ ሊተ ለገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ አብራህከ ሎሙ ለእለ ውስተ ጽልመት፣ አብርህ ሊተ ብርሃነ መለኮትከ ከመ እርዓይ ብርሃነ ገጽከ ዘምሉዕ በዞለሄ አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ አኅየልኮሙ ለሰማዕታት መዋዕያን፣ ወአጥፋእከ ሎሙ ላህበ እሳት፣ ወአክፋዕከ ሎሙ ስነነ አናብስት፣ ወባላህኮሙ እምፃእራተ ኵነኔ መፍርህ፣ ባልሀኒ ሊተ እም ዕለት እኪት ወእም ሰዓተ መንሱት ከመ በዳኅና እንግር ጽድቀከ አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ ባረካ ለምድር፣ ወነዛኅካ በደመ ጽልበትከ፣ ንዝኃኒ በአዛብ ከመ እንጻሕ ወሕፅበኒ በማይ ዘውኅዘ እም ገቦከ ከመ እምበረድ ጸዓድዒድ እጽዓዱ አነ ገብርከ።

አ በዘመስቀልከ አመንተውካ ለመካን ከመ ትለድ ውሉደ ወአዋልደ እለ ይትቀነዩ ለከ ወለቤተ መቅደስከ፣ ረስየኒ ቅኑየ ለአርዑትከ ሠናይ ወለጾርከ ቀሊል ጽዉረ አነ ገብርከ።

አ ዘበመስቀልከ አርአይከ ኃይለ አድኅኖትከ በኢየሩሳሌም ሀገሮሙ ለዕብራውያን እለ ከልሁ በቅድመ መስቀልከ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ። ወካዕበ ጸርሑ እንዘ ይብሉ እመሰ ወልዱ አንተ ለእግዚአብሔር ሕያው ረድ እስኩ እመስቀልከ ንርዓይ ወንእመን ብከ።

(፲፰)ወአርአይከ ኃይለ መስቀልከ። መስቀልከ አጽለሞ ለፀሐይ እምንጸሬ ዕርቃንከ ወአደመና ለወርኅ እም ርእየተ ሥጋከ ቅዱስ። ወእለ አርዮብ ይበርሁ እምጊዜ ስሱ ሰዓት። ወጊዜ ስሱ ሰዓት አፅነንከ ርእሰከ ወመጠከ ነፍሰከ ውስተ እደ አቡከ። አድለቅለቀት ምድር እመሠረታቲሃ። ወጸዋልዕት ተሰጥቁ ወእከዮሙ ለከሐያድያን ዕብን ተሰጥቀ። ወአልባቢሆሙ ለሰቃልያን ኢመምዐ አላ ጸንዐ እምዕብን። የብሰ ልቦሙ። ዘሐፂን ስርወ ክሳደሙ። ወዘብርት ፍጽሞሙ። ነቅዐ ኰኵሕ፤ ወተከሥቱ መቃብራት። ወጽላሌ ልቦሙ ተሐትሙ በጽልመተ ግላ። ፀሐይኒ አእመረ እግዚኦ። ወወርኅኒ አእመረ አምላኮ። ወከዋክብትኒ አእመሩ ገባሪሆሙ፤ እስመ ሠወሩ ብርሃኖሙ እምነጽሮ ዕርቃንከ። ወጸዋልዕትኒ አእመሩ ፈጣሪሆሙ ወተሰጥቁ እም ፍርሃተ ሞት። ምድርኒ አእመረት ዘሣረራ፤ እስመ አንቀልቀለት እም ኃይለ መስቀልከ። ኰኵሕኒ አእመረ ዘአጽንዖ እስመ ነቅዐ እምንጥበተ ደምከ።

(፲፱)እሉ ኵሎሙ አእምሩከ አወልደ እግዚአብሔር ከመ አንተ ፈጠርካሆሙ፤ ወእስራኤልሰ ኢያእመሩከ። ወሕዝ ብየኒ ኢጠየቁከ። ህየንተ ሠናይት እኪተ ፈደዩከ። ወህየንተ ዘአፍቀርኮሙ ጸልኡከ። ዓምደ ደመና ዘአንጦላዕከ ሎሙ ከመ ኢያውዕዮሙ ላህበ ፀሐይ፣ ይዘልፎሙ በእንተ ዘአሰ ተቀጸሉከ አክሊል ዘሦከ። ዓምደ እሳት ብሩህ ዘመርሐሙ በሌሊት እንዘ ይኬልሎሙ በሱራሄሁ፣ ይዘልፎሙ በእንተ ዘገልበቡከ ለተሣልቆ እንዘይብሉ ተነበይ ለነ ክርስቶስ፤ መኑ ውእቱ ዘጸፍአከ።

(፳)ማየ ትእምርት ዘኰኵሐ ኮሬብ ይዘልፎሙ በእንተ ዘአስተዩከ ብሂአ ዘምስለ ሐሞት።

መና በገዳም ዘሴሰይኮሙ ይዘልፎሙ በእንተ ዘሠርዑ ማዕደ ለበሊዐ ፍሥሐ እንዘ ቅንው አንተ በኅጻውንተ መስቀል።

ማየ ባሕር እንተ ተሰጠት ሎሙ ከመ ይርከቡ ምሕዋረ በዓምደ እሳት ማእከለ ማየ ባሕር ትዛለፎሙ በእንተ ዘሰጠጡ ልብሰከ ወተካፈሉ ለርእሶሙ።





ከይሲ ዘብርት ዘቀልዓ ሎሙ ሙሴ በትእዛዘ ዚአከ እምከመ ነሰኮሙ ከይሲ በገዳም ከመ ይሕየው በነጽሮቱ ይዛለፎሙ በእንተ ዘሰቀሉከ ዲበ ዕፀ መስቀል ውስተ ኢየሩሳሌም በአደዊሆሙ ለደቂቀ ያዕቆብ።

(፳፩)ወተፀርአ ኃይለ ትንቢት እምኔሆሙ። ወአልቦ እንከ ዘተንሥአ ነቢይ እም እስራኤል ወኢደምፀ ቃለ ትንቢት በኢየሩሳሌም ወበኵሉ አድያሚሃ። ሰጠጠ ቀያፋ ልብሶ እንዘ ይትመዓዕ፤ ወተአተተ ቅብዐ ክህነት እምሌዋውያን፤ እስመ ጽሑፍ በእንቲአሆሙ በውስተ ኦሪት ዘይብል አልባሲሆሙ ኢይስጥጡ ወኢይብጥሁ ሥጋሆሙ፤ እስመ ቅዱሳን እሙንቱ ለእግዚአብሔር። ወእንበይነ ቀያፋ እንከ ተአተተ ቅድስናሆሙ። ተሰጠ መንጦላዕተ ምኵራብ። ወአልቦ እንከ ዘይፈቅዱ። ወይብሉ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍቶሙ ለሕዝብ አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር፤ እስመ። ኵሉ ዘያነግሥ ርእሶ አላዌ ነጋሢ ውእቱ። አእመረ ሎሙ መንግሥተ ሮም ወከህድዎ ለወልደ ዳዊት። ወእምዝ በጠለ መንግሥተ አይሁድ እምኢየሩሳሌም። ጸጋ ዘተውህበ ለያዕቆብ መጠዉ ለአሕዛብ መንግሥተ ወክህነተ ወትንቢተ። ወተመጠዉ አሕዛብ ህብተ እምእስራኤል ምስለ ክርስቶስ። ወንሕነ ውሉደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አመነ ብከ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር በህላዌከ ወወልደ ዳዊት በሥጋዌከ። ወከመ ትንግሥ ለነ ለዝላፉ። ወምናኔከ ዘበኀበ እሉ ክብረ ኮነ ለነ በከመ ጽሑፍ ዘይብል እብን ዘመነንዎ ነደቅት ውእቱ ኮነ ውስተ ርእሰ ማእዘንት። እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ።

(፳፪)አኮ ለነጊሥ ባሕቲቱ ዘንፈቅድከ አላ ፍጹመ ናመልከከ እንዘ ንትአመን ከመ ዕሩይ አንተ ምስለ አብ በመለኮትከ፣ ወዘውግአ በዕበይከ ምስለ መንፈስ ቅዱስ። አልቦ ሰዓት ማእከሌከ ወማእከሌሆሙ። አልቦ ዕለት ማእከለ አብ ወማእከሌከ። አልቦ ቀዲመ ህላዌ ለአብ እምኔከ፣ ወኢተቀዲመ ህላዌከ እምነ መንፈስ ቅዱስ።

(፳፫)አኅረምከ ህላዌከ እምጠይቆ ሕሊና እጓለ እመሕያው፣ ወእምተአይሮ ሕሊና መላእክት። አኅረምከ ህላዌከ ዘበላዕሉ እም ተገሥሦ በእደ እጓለ እመሕያው፣ ወእም ተለክፎ በእደ መላእክት ትጉሃን።

አሕረምከ ሀላዌከ ዘበአርያም እምተነጽሮ ለኵሉ በከመ ፈቀደ ዘእንበለ በከመ ፈቀድከ።

(፳፬)ወኢንፈቅድ ዓዲ ሊቀ ካህናት ሰብእ መዋቲ ዘኢይክል አድኅኖ ለርእሱ እምእደ ሞት። አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘአብ ስምዐ ኮነ ለከ በውስተ ዮርዳኖስ እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘኪያሁ ሠመርኩ። ወሎቱ ስምዕዎ።

(፳፭)አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘመጦከ ነፍሰከ ወቤዘውከ አባግዒከ።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘንጹሕ እምኃጢአት ወልዑል እምሰማያት።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዲበ መስቀል ዘአቅረብከ ርእሰከ መሥዋዕተ ለዘወለደከ።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘለሊከ ሠዋዒ ወለሊከ መሥዋዕት።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘለሊከ መጸንሕሕ ወለሊከ ጽንሐሕ።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘቅቡዕ እምኀበ አብ መንፈስ ቅዱስ። ዘለሊከ ትትቀረብ መሥዋዕተ ርእሰከ ከመ ትሥረይ ሎሙ ኃጢአቶሙ።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናቲነ ዘእምለፌ ሦዕከ ርእሰከ ለዝላፉ እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

(፳፮)ከመዝ እንከንተ ጋነይ ለአርዌ ብርት ዘከህነትከ። ንሰግድ ቅድመ መስቀልከ ቅዱስ በዘዲቤሁ ተጠብሐ ሥጋከ እንዘ ንብል መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ። ቅድመ መስቀልከ ንሰግድ አ ሊቅነ፤ ወለቅንዋተ እደዊከ ወእገሪከ ናስተበርከ። ወርግዘተ ገቦከ ንኤምኅ። ወለኵናት ለዘረገዘከ ንሁብ ስብሐተ ወውዳሴ። ወትንሣኤከ ንዜኑ፤ ወሥርዓተከ ንትአመን። ወበንብረትከ ዘየማነ አብ ንትሜካህ እንዘ ንብል ብነ ኀበ እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት አማኑኤል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነበረ በየማነ ዘወለደ። ውእቱ ይመጽእ ካዕበ በደመና ሰማይ ምስለ ኃይል ወመላእክቲሁ ምስሌሁ ወመስቀሉ ቅድሜሁ።





አሜሃ አለ ወግዑከ ይበክዩ። ወለ እለሰ ይነሥኡ ማኅተመ ስምከ ይከውን ሎሙ ሰላም ወሣህለ እግዚአብሔር።

(፳፯)ወይእዜኒ እንከ ንዌድሰከ ኦኢየሱስ ክርስቶስ ፈዳየ እዳነ በመስቀልከ፤ ወገባሬ ሣህልከ በሞትከ ማዕከሌነ ወማዕከለ አቡከ፤ ወከፋሊ መንግሥተ ሰማያት ለነ በትንሣኤከ። በነጠብጣበ ደምከ ተጽሕፈ ምሕረትከ በሰሌዳ መስቀልከ። ወበርግዘተ ገቦከ ዘውኅዘ ደም ወማይ አእመኖ ለሐራዊ ዘወግዓከ። ወጽላሎተ መስቀልከ ዘለከፎ ለፈያታዊ ዘየማን ሜጠ ውስተ አሚነ ዚአከ። በከመ ተሳተፈከ ፈያታዊ በሕማማተ መስቀልከ ከማሁ ተሳተፈከ በመንግሥተ ሰማያት፤ እስመ ትቤሎ አንተ እመ ንፈድፋደ። ከመ ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት። ወ፩ሰ ፈያታዊ ዘኢለከፎ አሥረ ምሕረትከ ዘጸረፈ ላዕሌከ እንዘ ይብል እመሰ ወልደ እግዚአብሔር አንተ አድኅን ርእሰከ ወኪያነሂ። ወገሠጾ ካልኡ እንዘ ይብል ለነሰ ዘበርቱዕ ረከብነ ዘይደልወነ፤ በኃጢአትነ ተፈደይነ። ወዝንቱሰ አልቦ እኩይ ዘገብረ። ወተመይጠ ኀቤከ እንዘ ይብል ተዘከረኒ እግዚኦ በምሕረትከ አመ ትመጽእ በስብሐቲከ። ስሐቦቶ ሐብለ ምሕረትከ ለፈያታይ ዘየማን። ዕሩይ ሕማማተ መስቀል ዘረከቦሙ ለ፪ሆሙ። ወበዕሩይ ኃጣውእ ተኮነኑ። አኮ በእንቲአከ እሙንቱ ዘተሰቅሉ አላ በእንተ ተፈድዮቶሙ። በቃለ ጸሪፍ ዘወፅአ እም አፉሁ ተኃጕለ ፈያታይ ዘፀጋም። ወበቃለ አስተብቍዖ ዘወፅአ እም አፉሁ ድኅነ ፈያታይ ዘየማን። ወተፈጸመ ላዕሌሆሙ ዘተብህለ በወንጌል እምቃልከ ትጸድቅ ወእም ቃልከ ትትኴነን።

(፳፰)ወአነሂ እጸርሕ ኀቤከ ኦእግዚእየ ወአምላኪየ ወመድኃኒየ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ እብል ተዘከረኒ እግዚኦ በምሕረትከ አመ ትመጽእ በስብሐቲከ በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን በኀበ ቅዱስ ወማኅተመ ዕፀ መስቀልከ።

(፳፱)ተዘከረኒ እግዚኦ በምሕረትከ በከመ ተዘከርኮ ለማቴዎስ መጸብሐዊ፤ ወረሰይኮ ወንጌላዌ ወሱታፌ ከፍሎሙ ለሐዋርያቲከ ቅዱሳን።

ተዘከረኒ እግዚኦ በምሕረትከ በከመ ተዘከርኮ ለጳውሎስ እንዘ ሰዳዲ ውእቱ ወረሰይኮ ሐዋርያ ወሰባኬ ወንጌለ መንግሥት ለጽዋዔ አሕዛብ እስከያንከሩ በእንቲአሁ እለ ሰምዑ እንዘ ይብሉ ዝኩእ ዘቀዲሙ ይሰድድ ዘይእዜ ይሜህር ቃለ ሃይማኖት። ወየአኵትዎ ለእግዚአብሔር በእንቲአሁ ዘጸጋ ዘተውህበ።

ተዘከረኒ እግዚኦ በምሕረትከ በከመ ተዘከርካ ለዘማ እንተ ቀበዓተከ ዕፍረተ፤ ወአርሐሰት እገሪከ በአንብዓ ወመዝመዘተከ በሥእርታ። ወትቤላ ሃይማኖትኪ አሕየወተኪ፤ተኃድገ ለኪ ኃጢአትኪ። ወበለኒ ሊተ ሃይማኖትከ አሕይወተከ። ወረስየኒ ድልወ ለመንግሥተ አቡከ ሊተ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

## ፫

(፴)ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ግበር ሣህለከ በእንቲአየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐው ምሕረተከ ላዕሌየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀፅረኒ በሐፁረ መስቀልከ፤ ወከልለኒ በወልታ መድኃኒትከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አዑድ ጥቅማ ለሥጋየ በኃይለ መስቀልከ መዋዒ ፀር።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ መግበኒ በአእላፍ ትጉሃን መላእክቲከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አወልትወኒ ንዋየ መስቀልከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ውስተ አፉሆሙ ለቅዱሳን።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ዝከር ለእለ ይጼውዕዎ በጽድቅ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኮከበ ብርሃን ጽባሐዊ ምከሆን ለአብያዘ መንፈስ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ፀሐየ ጽድቅ ዘዘልፈ ያበርህ በገጸ ቅዱሳን።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኦመ ዘይት ዘሠረፀ እምቤተ ያዕቆብ። በትረ ሃይማኖት ዘወፅአ እምሥርወ እሴይ። ወጽጌ ዘዐርገት እምጒንዱ ለዳዊት።





ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንበሳ ዘሞአ እምነገደ ይሁዳ ዘእምግርማ መዓቱ ተሀውኩ መኳንንተ ጽልመት፤ ወእም ድምፀ ጣኅሩ አንቀልቀሉ መሠረታተ አድባር።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀስታመ መስቀልከ ሂጾ ለመስተአግል፤ ወሐፃውንተ ቅንዋቲሁ ግበር አሕፃ ርሱናተ በዘትነድፎ ለጸላኢ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አርኢ ኃይለ አድኅኖትከ ላዕሌየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሢም ብርሃነ ገጽከ ላዕሌየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገሰ መስቀልከ የሀሉ ምስሌየ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅስም ልሳንየ በዜወ መለኮትከ ከመ አይድዕ ውዳሴ መስቀልከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ምላዕ አፉየ ስብሐቲከ ከመ እሰብሕ አኰቴተከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አጽንዖን ለመከየድየ ውስተ ፍኖትከ ከመእትሉ አሠረ ጽድቀሙ ለመከየድከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አጽንዓኒ ለገቢረ ፈቃድከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አውድድ ውስተ ሥጋየ ፈሪሆተከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐው ዲበ ርእስየ ዘይተ ምሕረትከ። ወያንጸፈጽፍ ውስተ ገጽየ ቅብዐ ሣህልከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተዳልወኒ ለነሢአ ምሥጢረከ ሰማያዌ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አርፍቀኒ ውስተ ማእድከ መለኮታዊ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥመር ብየ በከመ ሠመርኮሙ ለቅዱሳን።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሱቀኒ እምትንታኔ ወአንሥአኒ ወእምወዲቅ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አድኅነኒ እምንዳቤ። ርኢ ሕማምየ ወስራኅየ ወኅድግ ሊተ ኃጢአትየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አድኅነኒ እምእደ ፀርየ ወእምእለ ሮዱኒ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አብርህ ገጸከ ላዕለ ገብርከ ወኢይትኃፈር እግዚኦ እስመ ጸዋዕኩከ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይለ መስቀልከ ይኩነኒ ዓቃቤ በኵሉ መዋዕል ኀበ ወፈርኩ ወበኵሉ ለያልይ ኀበ ቤትኩ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ተስፋየ እም ንእስየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ እምከርሠ እምየ አንተ አምላኪየ። ወበውስተ ማኅፀን አንተ ከደንከኒ። ወአንተ ዝክርየ በኵሉ ጊዜ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ቀርነ መድኃኒትየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ አክሊለ ርእስየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ጥዑም ለአፉየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ጽዋዐ መድኃኒት ሐዋዝ ለጕርዔየ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ልብሰ ዘኢተአንመ ወክዳን ዘኢተፈትለ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ወርቅ ዘተመከአበ ወባሕርይ ዘተረከበ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ምናን ዘበዝኀ ወመከሊት ዘረብሐ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ጸዋሬ ሕማማት በእንተ ኃጢአተ አዳም ወደቂቁ።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ተኢጋሤ ሕማማተ መስቀል በእንተ ስሕተተ ሔዋን ወአዋልዲሃ።





ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ውእቱ ተወካፌ ሐፃውንተ ቅንዋተ መስቀል በእንተ ጌጋየ እጓለ እመሕያው።

ኦ ዘተወከፍከ ሕማማተ መስቀል በእንተ ኃጣውኢነ ወተወከፍ ጸሎትየ ከመ ዕጣን በቅድሜከ።

ኦ ዘተአገሥከ መፃእርተ መስቀል በእንተ ጌጋይየ ጸግወኒ ትእግሥተ እንተ ውስተ ሕፅንከ ተሐድር። ረስየኒ ጽሙደ ውስተ አርዑተ መስቀል።

(፹፩)ወእለ ተንሥኡ ላዕሌየ በዓመፃ ወበኃይል በኃይለ መስቀልከ ይትየዩ፤ ወእምገጸ መስቀልከ ይንፍፁ። ፈኑ ላዕሌሆሙ ፍርሃተ አንስት እስከ ይሜምዑ እም ድምጸ ቈጽል ዘይትሐወክ በአፍአ። ያፃምዎሙ መጥባሕት ለውሉደሙ። ወበውስተ አብያቲሆሙ ይኩን ድንጋጼ። ወሊተሰ ይኩን ዳኅና ወሰላም እም ኀቤከ በኵሉ አዝማን ወበኵሉ መዋዕል።

(፹፪)ኦ እግዚእየ አንሥእ ኃይለከ ወነዐ አድኅነነ። ኦ አምላከ ኃያላን ሚጠነ፤ አብርህ ገጸከ ላዕሌነ ወንድኃን። ኦ እግዚእየ በመስቀልከ ኩነነ መርሐ ውስተ ኵሉ ፍናው ኀበ ፈቀድከ። ረዳኤ ወመሰውረ ኩኑኒ እስመ አንተ ውእቱ ኃይልየ ወፀወንየ፤ ጽንዕየ ወመድኃኒተ ነፍስየ። መዓልተ ሀሉ ምስሌየ ወሌሊተ ንበር ማዕከሌነ። ኢትኅድገኒ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ መዋዕል።

(፹፫)ተዘከር እግዚኦ ርደተከ እምአርያም ወኅድረተከ ውስተ ከርሠ ቅድስት ወንጽሕት ድንግል በ፪ ማርያም ወልደትከ እምኔሃ ወሕፅነተከ በአጥባቲሃ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።

ተዘከር እግዚኦ ልህቀተከ በበሕቅ ወውርዛዌከ ዘበንጽሕ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ።

ተዘከር እግዚኦ ጥምቀተከ በእደ ዮሐንስ እንዘ ከሡት ዕርቃንከ ማዕከለ ባሕር። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ፃምዎተከ በሐዊረ ፍኖት ወተመከሮተከ በገዳም እምኀበ ዲያብሎስ አመ ርኅብከ ሶበ ጾምከ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ።

ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ሥጋከ ወደመከ ዘወሀብኮሙ ለአርዳኢከ በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ ትትአሐዝ፤ ትቤሎሙ ንስእዎ ወብልዕዎ ለዝንቱ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ። ንሥኡ ስትዩ ዘንተ ጽዋዐ ደምየ ውእቱ። ኢይሰቲ እንከ እምዝንቱ ዓጺረ ፍሬ ወይን እስከ እሰትዮ ሐዲሰ በመንግሥተ ሰማያት ዘአቡየ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ተእኅዞተከ እምአግብርተ ሊቀ ካህናት ወተጸፍዖተከ በዐውደ ቀያፋ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ቀዊሞተከ በዐውደ ቀያፋ ወተፅእሎተከ እምነበ ዓውድ።

ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ተኮርዖተከ በበትረ ሀለት ወተቀሥፎተከ በጥብጣቤ ዘሐብል። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ተሰቅሎተከ በዲበ ዕፅ ወተቀንዎተከ በሐፃውንት። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ዘአስተዩከ ብሂአ ዘምስለ ሐሞት፤ ወዘመጠውከ ነፍሰከ ለሞት። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ተገንዞተከ በልብሰ ገርዜን ወተወድዮተከ ውስተ መቃብር ወንበረተከ ውስቴቱ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ዘእንበለ እንሰሐስሆ ነፍስ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ተንሥኦተከ እሙታን በሣልስት ዕለት ወአስተርእዮተከ ለአርድእት እንዘ ሀለዉ ውስተ ፅርሕ ዘዕፁው ኆኅቱ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ።

ተዘከር እግዚኦ ዕርገተከ ውስተ ሰማያት ወንብረተከ በየማነ አብ። ዘንተ ተዘኪረከ አናሕሲ ኃጣውእየ ሊተ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።





(፴፬)እመ ዳግም ምጽአትከ ኖልቄኒ ምስለ አባግዒከ ቡሩካን፤ ወክፍለኒ ርስተ ውስተ ሀገሪቶሙ ለቅዱሳን። አኮኑ እግዚኦ ለበስከ ሥጋ ለአድኅኖትየ። ዘኢይማስን ሥጋ ረሰይኮ ለዘይማስን።

(፴፭)ለእመሰ አነ እትኃጐል ለምንት ለከ እግዚኦ ለቢሰ ሥጋ ምድራዊ።

ለእመሰ አነ እዴየን ለምንት ለከ እግዚኦ አንሶሰዎትከ ውስተ ዓለም ፴ወ፫ ዓመተ ፫ አውራኃ፤ ወፃምዎትከ በዲበ ምድር በከመ ሕገ እጓለ እምሕያው ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ።

ለእመ አነ እትኴነን ለምንት ለከ እግዚኦ ተኀምዮ እደዊከ ከመ ሠራቂ ወተጸፍአ መላትሒከ ከመ ጊጉይ።

ለእመሰ አነ እዴየን ወእማቀይ ለምንት ለከ እግዚኦ ተኰርዖ ርእሰከ ከመ እንስሳ ወተቀስፎ ዘባንከ ከመ አላዊ ሕግ።

ለእመሰ አነ ኢይድኅን ለምንት ለከ እግዚኦ ተአግሦ ኃፍረተ መስቀል ወተወክፎ ምራቀ ርኩሳን ወጽእለተ ከሐድያን።

(፴፮)ሐሰ ለከ እግዚኦ ኢትግበር ዘንተ ደይነ። ኢትመንነኒ ለሤጠ ደምከ። ለከሰ እግዚኦ ረባሐ ለነጊድከ ለእመ ድኅንኩ አነ። ለከሰ እግዚኦ ረባሐ ለስቅለትከ ለእመ ሐዮኩ አነ። ለከሰ እግዚኦ ረባሐ ለሕማማቲከ እመ ጸደቁ አነ። ተዘከር እግዚኦ ዘትቤሰ ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን ወዘኢአምነ ይደየን።

(፴፯)አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር፤ አምላክ ወልደ አምላክ፤ ብርሃን ወልደ ብርሃን፤ ንጹሕ ወልደ ንጹሕ። ወተጠመቁኒ በማይ ዘውኅዘ እምገቦከ። ወበእንተዝ ኢይደልወኒ ኵነኔ። ወእመሰ ኃጢአተኑ ትትዓቀብ እግዚኦ መኑ ይቀውም ቅድሜከ። ወባሕቱ ከመ ኢይትሐሰው ቃልከ ተሣሃለኒ እስመ አንተ ትቤ ኵሉ ዘየአምን ብየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም። ስረይ ሊተ ኃጢአትየ ኦ ዘባሕቲትከ ዘእንበለ ኃጢአት። ኢትዝክር ጌጋይየ ኦ ዘባሕቲትከ ዘእንበለ ጌጋይ።

(፹፰)አንሰ ውኩል በአሚነ መስቀልከ ቅዱስ፤ ይትፌሥሐኒ ልሳንየ ወከናፍርየ ውዳሴ መስቀልከ። በኃይለ መስቀልከ ከልለኒ ከመ ወልታ ሥሙር ሲተ ገብረ መስቀል።

(፹፱)ኀቤከ እግዚኦ አንቃዕደኩ አዕይንትየ። ሰፋሕኩ እደዊየ ወአንሣእኩ ርእሰ ሕሊናየ። ኀቤከ ጸራሕኩ ወእቤለከ አንተ ተስፋየ ወአንተ መክፈልትየ በምድረ ሕያዋን። ነጽር ላዕሌየ እስመ ሐመምኩ ፈድፋደ። አ አምላከ ኃያላን ኢትኅድገኒ አንተ ለዝሉፉ እመ አአብስ ለከ። ጽሉ እዝነከ ኀበ ስእለትየ። ለትብጻሕ ጸሎትየ ቅድሜከ በጽርሐ መቅደስከ። ተሣሃለኒ ወስምዓኒ ለከ ይብለከ ልብየ። ወኃሥሥኩ ገጸከ። ገጸ ዚአከ አኃሥሥ እግዚኦ። ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ። ረዳኤ ኩነኒ ወኢትግድፈኒ።

(፺)አንተሰ እግዚኦ ለዓለም ትነብር። ወዝክርከኒ ለትውልደ ትውልድ። አንተ እግዚኦ አቅደምከ ሣርሮታ ለምድር፡ ወግብረ እደዊከ እማንቱ ሰማያት። እማንቱሰ ይትኃጐላ ወአንተሰ ትሄሉ። ወኩሉ ከመ ልብስ ይበሊ። ወከመ ሞጣሕት ትዌልጦሙ ወይትዌለጡ። ወለከሰ አልቦቱ ጥንተ ለቀዳሚ መዋዕሊከ ወኢተፍጻሜት ለደኃሪትከ። ኀቡዕ አንተ እም ኀቡአን። ወአመ ፈቀድከ ከሠትከ ርእሰከ ለመሬታዊያን።

(፺፩)እንዘ በሰማያት ንቡር አንተ በየማነ አቡከ፣ በታሕቱ ቅድመ ዐውደ ጲላጦስ ቆምከ።

እንዘ በአርያም መንጦላዕተ እሳት ይሴውረከ፣ በምድር ከሐድያን ከሠቱ ዕርቃነከ።

እንዘ በላዕሉ ማኅበረ መላእክት ይባርኩከ፣ ወበቀራንዮ ማኅበረ አይሁድ ይጸርፉ ላዕሌከ።

እንዘ በመልዕልተ ሰማያት በአክናፈ ኪሩቤል ትትኬለል፣ ወበኢየሩሳሌም አክሊለ ሦክ ትትቄጸል።

እንዘ ዲበ ጌርጌላ በሰረገላ እሳት ትጼዓን፣ ወበሊቶስጥሮስ ዲበ ዕፀ መስቀልከ ተሰቀልከ፤ ወበነጸፍጻፈ ደምከ ተቀብዐ መስቀልከ።





## ፬

(፺፪)አ ኬ ዕፅ በደመ አምላኩ ዘተቀደሰ ወበማይ ዘውኅዘ እምገቦ ፈጣሪሁ ዘተጠመቀ።

አ ኬ ዕፅ ዘኮኖሙ አክሊለ ለዕፀወ ገነት ወክብረ ለዕፀወ ገዳም።

አ ኬ ዕፅ ዘኮነ ምጥባሐ ለበግዐ እግዚአብሔር ጸባዖት።

አ ኬ ዕፅ ዘኮነ ምሥዋዐ ፋሲካሁ ለአምላከ እስራኤል።

አ ኬ ዕፅ ዘኮነ ነቅዐ ወይነ ምሥጢር ኀልጎታዊ።

አ ኬ ዕፅ ዘአንጠብጠበ እምኔሁ ደመ ሕግ ወሥርዓት ለማኅተመ መሃይምናን።

አ ኬ ዕፅ ዘውኅዘ እምኔሁ ምንዛሕ ለምሕፃበ አባግዐ ቡሩካን።

አ ኬ ዕፅ ዘቀደሳ ለምድር ወአተበ ለሰማይ ወባረከ ኵሎ ዓለመ በበረከተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

አ ኬ ዕፅ ዘአስተሳፈሮሙ ለሰማያዊያን ምስለ ምድራውያን።

አ ኬ ዕፅ ዘአድኃኖ ለአዳም እምስሕተት ወረሰዮ ለሔዋን አግዓዚተ እምፃዕረ ሞት።

አ ኬ ዕፅ ዘበእንቲአሁ ተጽሕፈ በኦሪት ወነቢያት ወገሃደ ተሰብከ በሐዋርያት።

አ ኬ ዕፅ ዘዘረዎሙ ለእለ ተከልዎ፤ ወአስተጋብኦሙ ለእለ አመንዎ።

አ ኬ ዕፅ ዘአመሥረታ ለቤተ ክርስቲያን ዲበ ሃይማኖተ ኢየሱስ ክርስቶስ።

አ ኬ ዕፅ ዘአጥአሞ ለልሱን ወአንጽሖ ለርሱን።

አ ኬ ዕፅ ዘአልዓሎ ለነዳይ ወአጽደቆ ለጊጉይ።

አ ኬ ዕፅ ዘአጽንዖ ለድኩም ወአጥዐዮ ለሕሙም።

ኦ ኬ ዕፀ ዘአስተባዝኖ ለውሑድ ወአስተጣበቦ ለአብድ።

ኦ ኬ ዕፀ ዘአፍረያ ለመካን ወአብርሃ ለጸላም።

ኦ ኬ ዕፀ ትምክህተ ኵሉ ዓለም።

(፵፫)እንዘ ንቁሕ ልብነ ወክሡታት አዕይንቲነ ወፍሡሓት ከናፍሪነ ናሌዕል ስብሐተ መስቀል። ኦ እግዚእየ ስብሐተ መስቀልከ ያነቅሆሙ ለጽዑራን ወይሬስዮሙ ከመ ይኅበሩ ሰብሐ ምስለ ማኅበረ ትጉሃን።

(፵፬)ስብሐተ መስቀልከ ምሉዕ በኵለሄ ወንኩር ጥቀ ለልብ።

ስብሐተ መስቀልከ ይጥዕም ለዘ ያነብቦ ወይኤድሞሙ ለሰማዕያን።

ስብሐተ መስቀልከ መሰንቆሁ ውእቱ ለዘየአምን ብከ፤ወዘለፋሁ ውእቱ ለዘይክህደከ።

ስብሐተ መስቀልከ ዕንዚራሁ ውእቱ ለዘያፈቅረከ፤ ወጽዕለቱ ውእቱ ለዘ ይጼአለከ።

ስብሐተ መስቀልከ ያስተፌሥሖ ለልብ ከመ ሰትየ ወይነ ከራሚ። ወነገረ መስቀልከ ጽእለት ውእቱ በኀበ አብዳን፤ ወትምክህት ውእቱ በኀበ ጠቢባን፤ በከመ ይቤ ጳውሎስ ወነገረ መስቀሉሰ ለኅርቱማን ዕበድ ይመስሎሙ። ወለነሰ ለእለ አመነ ኀይለ እግዚአብሔር ውእቱ።

(፵፭)ስብሐተ መስቀልከ ያብርህ ለነ። ወይኩነነ መርሐ ከመ ዓምደ እሳት ዘአብርሃ ሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወመርሆሙ ፵ዓመተ በገዳም እምሐቅለ ሴይር እስከ ቃዴስ በርኔ። ወይእዜኒ ትመርሐኒ የማንከ ጽንዕት ወመዝራዕትከ ልዕልት በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ። ኦ ጠቢበ ጠቢባን ክሥቶን ለአዕይንትየ ወእርዐይ መድምመከ እምሕግከ፤ እስመ ፈላሲ አነ በውስተ ምድር ወነግድ ከመ ኵሉ አበውየ። ስሕተኒ ከመ አእርፍ ዘእንበለ እሑር ኀበ ኢይገብእ።

(፵፮)ረስየኒ እግዚኦ እፍረይ ፍሬ ንስሐ ዘእንበለ እትገዘም በሰይፈ ሙስና።





ረስየኒ እግዚኦ ከመ አንብብ ስብሐተ መስቀልከ እንበለ ይትፈጸም አፉየ በሞት።

ረስየኒ እግዚኦ እጐድጕድ አንቀጸ ጽርሐከ እምቅድመ እትዓሰር በሰናስል ዘኢይትፈታሕ።

ረስየኒ እግዚኦ ከመ እግበር ረብሐ ነፍስየ እምቅድመ ይጸራእ ሤጥ ወምሥያጥ።

ረስየኒ እግዚኦ አስተዳሉ ቅብዐ ለማኅቶት እምቅድመ ይትአፀው ኆኅተ ጽርኅ ለመርዓዊ።

ረስየኒ እግዚኦ አስተዳሉ ስንቀ ለፍኖት እምቅድመ ይኩን ውዑየ ወይትነፋሕ ቀርን።

ረስየኒ እግዚኦ ዕፍዲ እዳ ዘላዕሌየ እምቅድመ ይትነበብ መጽሐፍ ዘይከውን ስምዐ በእንተ ኃጣውእየ።

ረስየኒ እግዚኦ እትጋህ በስብሐት እምቅድመ ይምጽአኒ አርምሞ ዘኢያበውህ ለተናግሮ።

ረስየኒ እግዚኦ አሀሉ ብከ ወበመንፈስከ ቅዱስ።

ረስየኒ እግዚኦ እትሉ አሠረ ወንጌልከ እንዘ እትመረጐዝ መስቀለከ።

ረስየኒ እግዚኦ ጥሉለ በመዓዛ ዕፍረትከ ዘረሰዮን ለደናግል ከሞ ይትልዋ ድኅሬከ ወሰማዕትኒ ከመ ይጹሩ ሱታፌ ሕማማቲከ ወለጻድቃንኒ ከመ ይንሥኡ አርዑተ መስቀልከ።

(፵፯)ወኵሉ ዘነሥአ መስቀለ ሞቱ ኢይንህካ ለነፍሱ እም ሕማመ ዝ ዓለም እምአፅባ ወምንዳቤ ወተፅናስ። በከመ ትቤ ለሊከ በወንጌል ዘይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ሊይግድፋ። ወዘሰገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ይረከባ። ምንተ ይበቍዖ ለሰብእ ለእመ ኵሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ኃጕለ። ዘንተ ፈራህኩ እግዚኦ አድኅነኒ እምኀጕለ ነፍስየ ሊተ። ጥቡዕ ልብየ እግዚኦ በትውክልተ ቅንዋቲከ።

ጥቡዕ ልብየ እግዚኦ ለስብሐቲከ። ፍቅርከ ያንቅሐኒ እምንዋመ ሐኬት ወይክሥት አዕይንተ ልብየ ለውዳሴ መስቀልከ።

(፵፰)መስቀልከ ዕፅ ዘኢይነቅዝ።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢየአብር።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢይማስን።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢያየብሶ ላህበ ፀሐይ ወኢሐሩረ ነፋሳት።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢይክሉ አንቅልቅሎቶ ወሐይዝት ወኢንፍሐተ ነፋሳት።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢይክሉ ገፍትኦቶ መዋግደ ባሕር።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢይክሉ አውድቆቶ ክበደ ዝናማት።

መስቀልከ ዕፅ ዘኢይክሉ ቀሪቦቶ መናፍስት ርኩሳን።

መስቀልከ ዕፅ ዘአልቦ ዘይመስሎ እምዕፀወ ገነት፤ ወአልቦ ዘይትኤረዮ እምዕፀወ ገዳም።

መስቀልከ ዕፅ ዘአልቦ ዘይመስሎ እምዕፀወ አርዝ። ወዕፀወ ምርስኔ ኢይትኤረዮ። ወኢላጤኑስ ከመ ሠርፁ። ወዕፀወ ቄድሮንኒ ኢይሤንዮ። ወዕፀወ ጳውቄናሂ ኢይመስሎ።

መስቀልከ ጽሕደተ ዕፅ ዘኢይትሜካህ ላዕለ ዕፀው።

መስቀልከ ዕፅ ዘሠምሮ እግዚአብሔር ይዕርግ ውስቴቱ።

መስቀልከ ዕፅ ዘአንጠብጠበ እምአዕጹቂሁ ዝናማተ ወይን። ወደመናሁኒ ደመና ብርሃን ዘአርያም ዘውእቱ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወበጠለ ምሕረት ዘውህዘ እምኔሁ ተሰቅዩ መሃይምናን። ወነሥኡ መሃይምናን ማሕተመ ጥምቀት እምኔሁ። ወሶበሂ የአትቡ ገጾሙ በተእምርተ መስቀል ይጕይይ ሰይጣን እምቅድመ ገጾሙ በከመ ይብል ትምህርተ ሐዋርያት ወዘልፈ ጸሐቅ ለአቲበ ፍጽምከ እስመ ትእምርተ መስቀል እንከ ትእምርተ ሕማም ውእቱ ዲበ ሰይጣን።





(፵፱)ወሀበ ሀሎ መስቀል ይደጉጽ ልቦ። ወእምዝከረ መስቀልከ ይሜምእ ከመ ይጕየይ።

(፶)ወነቢያትኒ አርአዩ አርአያ መስቀልከ እግዚኦ። ሙሴ ገብረ አርአያ መስቀል በገዳመ ራፊድ። አመ አዘዞ ለኢያሱ ይትአኀዞ ለአማሌቅ ዐርገሙሴ ውስተ ደብር ወሰፍሐ ፪ እደዊሁ ወአልዓለ ርቡባቲሆን እምነግህ እስከ ሰርክ በአርአያ መስቀልከ። ወሶበ ያስተጋብእ እደዊሁ የዐፅብ እስራኤል ወይሄይል አማሌቅ። ወሶበ ይሰፍሕ እደዊሁ ይነትዕ አማሌቅ ወይመውዕ እስራኤል። ወወዓሉ ሖር ወአሮን እንዘ ይጸውሩ እደዊሁ። ወእደዊሁሰ ለሙሴ ክቡዳት። ወአንበሩ ሎቱ ዕብነ ዐቢየ እምለፌ ወእ ምለፌ ከመ ኢያስተጋብእ እደዊሁ፤

(፶፩)እስመ በሰፍሐተ እደዊሁ በአርአያ መስቀልከ ይትመውዑ አማሌቅ። ወከማሁ ጽብዖሙ በኃይለ መስቀልከ ለእለ ይትቃረኑኒ ወባርከ ተጻብዖትየ ሊተ።

(፶፪)ወካዕበ ሙሴ አርአየ ትእምርተ መስቀልከ አመ ይወፅኡ እስራኤል እም ግብፅ ወቤተ ያዕቆብ እምሕዝበ ፀር ዘበጠ ባሕረ በበትሩ ምዕረ ርቱዐ። ወደገመ ዝብጠተ ግድመ። ወበዝ ኮነ ትእምርተ መስቀል። ወቆመ ማይ ከመ ዐረፍት እምለፌ ወከመ ዐረፍት እምለፌ። ወኃለፉ ደቂቀ እስራኤል በማዕከሉ። ወሊተኒ ጺሕ ሊተ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት ማዕከለ ባሕረ ሙስና። ወኃድፈኒ በኃይለ መስቀልከ ሊተ።

(፶፫)ወካዕበ ዓዲ ሙሴ አርዐየ ትእምርተ መስቀል አመ ዘበጠ ኰኵሐ በበትሩ። ዘበጦ ምዕረ ርቱዐ ወደገመ ዝብጠተ ግድመ ለፌ ወለፌ ኀበ ይቀውማ እገሪሁ ለእግዚአብሔር። ወነቅዐ ማይ እምነ ኰኵሕ ልሙፅ፤ እስመ በትእምርተ መስቀልከ ተገብረ ዝ ተአምር። ወከማሁ ሊተኒ አንቅዕ ሊተ ማየ ሕይወት ለአንጽሖተ ርስሐትየ ሊተ በበትረ ኃይለ መስቀልከ። ኢትመጥወኒ ለግሙራ ለፍዳ ኃጢአትየ። በእንተ አብርሃም ፍቁርከ፤ ወበእንተ ይስሐቅ ቍልዔከ፤ ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ። በእንተ ሙሴ ገብርከ ዘተመጠወ ሕገ እምእደዊከ። በእንተ ዳዊት ዘተረከበ ምእመነ በቅድሜከ። ወበእንተ ኵሎሙ ነቢያቲከ እለ ሰበኩ ስርቀተከ ውስተ ዓለም። በእንተ ሐዋርያቲከ ቅዱሳን እለ ከልሑ ከመ ቃለ ቀርን በሰምዐ ወንጌልከ ቅዱስ። ወፈድፋደሰ በእንተ ቅድስት

ወንጽሕት ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ። ወበአንተ ቅዱስ ወቡሩክ ዕፀ መስቀልከ። ባርከኒ በበረከትከ ወበበረከተ አቡከ ሰማያዊ። ወበበረከተ መንፈስከ ማኅየዊ ወበበረከተ ኵሎሙ ቅዱሳን እለ እምዓለም አስመሩከ።

(፶፬)ኦ እግዚኦ ጽድቅ በወልታ የዐውድከ፤ ወሣህልከ ይሜግቦሙ ለመሃይምናን።

ኦ እግዚኦ ሰማያት ወሰማየ ሰማያት ሰቁላን በትእዛዝከ። ወምድርኒ ጸንዓት ዲበ ማይ በቃልከ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብትኒ ያበርሃ በሥልጣንከ። መላእከተ ገጽኒ ወመላእከተ ስባሔ ክቡራን በቃለ አፉከ። እምኵሉ ሰብእ አዕበይኮ ለአዳም ዘለሐኮ በኢዴከ። ወሰአልኮ በመልክእከ ዘኢይማስን። ወነፋሕከ ውስተ ገጹ መንፈሰ ሕይወት። ወኵሎ አግረርከ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ፤ አባግዓኒ ወኵሎ አልህምተ ወዓዲ እንስሳ ዘገዳም ወአዕዋፈ ሰማይኒ ወዓሣተ ባሕር ወዘኒ የሐውር ውስተ ፍኖተ ባሕር። ወእምፃእከ ኵሎ ዘነፍሰ ሕይወት ከመ ይርአይ ወምንተ ይሰምዮሙ። ወዘሰመዮሙ አዳም ለለነፍሰ ሕይወት፤ ውእቱ ይከውን ስሞሙ።

(፶፭)ወሶበ አበሰ አዳም ወበልዓ ዘአዘዝኮ ከመ ኢይብላዕ እምኔሁ ወወፅአ እምገነተ ትፍሥሕት። ወአንተሰ ፈደይከ ዕዳሁ ለአዳም ዘበበሊዐ ዕፅ በዕፀ መስቀልከ ክቡር ወማኅየዊ። ወሊተኒ ፍድየኒ ዕዳየ በእንተ ሕማማተ መስቀልከ ማኅየዊ፤ ወአናሕሲ ኵሎ ኃጣውኢየ። ወካዕበ ሐደስከ ዓለመ እምድኅረ አይኅ ለአቡነ ኖኅ። ወመሐልከ ሎቱ እንዘ ትብል መሐልኩ እንከ ከመ ኢይደግም ረጊሞታ ለምድር። ወኢያማስና በማየ አይኅ። ወእምከመ መጽአ እንከ ዝናም እሠይም ቀስትየ በውስተ ደመናት። ወሶበ ይጸልም እንከ ደመና ለረዊይ በዝናም እሬኢ እንከ ዝኰ ቀስተ ትእምርት ዘኪዳንየ። ወእዜከሮ ለኪዳንየ ዘምስሌከ፤ ወኢያማስኖ ለዓለም በማየ አይኅ ዳግመ።

(፶፮)ወሊተኒ ሢም ሊተ ቀስተ ትእምርት ዘኪዳን ዝውእቱ መስቀልከ ቅዱስ ትእምርተ ኪዳንከ ምስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን። መስቀልከ ቅዱስ ቀስታመ መዊዕ ዘውስተ እደዊሆሙ ለመሃይምናን። መስቀልከ ቅዱስ ቀስታመ ሙስናሆሙ ለዕልዋን። ይኩነኒ ረዳኤ ኃይለ መስቀልከ ቅዱስ ሊተ። ወካዕበ አቀምከ ኪዳነ ምስለ አብርሃም አመ አዕረገ ዲበ ምሥዋዕ ለይስሐቅ ወልዱ





ከመ ይሡዖ። ሠፀረ ዕፀ ለመሥዋዕት ወአጾሮ ዲበ መትከፍቱ። ወይቤሎ ይስሐቅ ለአብርሃም ናሁ ዕፅ ለመሥዋዕት፤ ወናሁ መጥባሕት፤ አይቴ ሀሎ በግዕ ለሠዊዕ። ወይቤሎ አብርሃም እግዚአብሔር ይሬኢ ሎቱ በግዖ ወልድየ።

(፶፯)መንፈሰ ትንቢት ይትነበብ በአፈ ፪ሆሙ። ይቤ ይስሐቅ አይቴ ሀሎ በግዑ ለመሥዋዕት። እንዘ ይሴአል በእንተ መሥዋዕተ በግዕ ምድራዊ ወፍካሬ ትንቢትሰ ይመይጥ ቃለ ኀበ ወልደ እግዚአብሔር። ይቤ አብርሃም እግዚአ ብሔር። ይሬኢ ሎቱ በግዖ። ውእቱሰ ይቤ በእንተ ሠዊዐ ወልዱ። ወፍካሬ ትንቢትሰ ይመይጥ ቃለ ኀበ በግዕ ሰማያዊ። ወይስ ሐቅስ ዘሖረ እንዘ ይጸውር ዕፀ በዘ ይሠውዕ አቡሁ አርአያ መድኅን ውእቱ ዘሖረ ቀራንዮ እንዘ ይፀውር መስቀሎ በዘይሠውዕዎ አይሁድ አበዊሁ እመንገለ እሙ። በከመ ይቤ ጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ሎሙ ሕገ ወሎሙ ሥርዓተ። ሎሙ አሰፈወ ትርሲተ ወልድ። እሙንቱ አበዊነ፤ ወእም ላዕሌሆሙ ተወልደ ክርስቶስ። ወደብረ ማስኖሂ አምሳለ ቀራንዮ ውእቱ። ወበግዕ ዘተሠዐ ህየንተ ይስሐቅ አርአያ ትስብእቱ ለመድኃኒነ ውእቱ በከመ ይቤ ኢሳይያስ መጽአ ከመ በግዕ ይጠባሕ ኀበ ዘይወስድዎ ይጥብሕዎ። ወከመ በግዕ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርጾ ወከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ፤ እስመ ይነሥእዎ ለፍትሑ ወመኑ የአምርዎ ለልደቱ። በኃጢአተ ሕዝብ በጽሐ ለመዊት።

(፶፰)ወይስሐቅስ ሰኪቦ ዲበ ምሥዋዕ ተሐዘቦ እምድኅረ ተመልሐ መጥበሕተ አቡሁ ላዕሌሁ። ዓዲሁ ሕያው ውእቱ፤ እስመ ድኅነ በዘተዘብሐ በግዕ ዘእግዚአብሔር በከመ መለኮት ሕያው ውእቱ ወኢልኩፍ በሕማማተ መስቀል። እንዘ ሀሎ ዲበ ዕፀ መስቀል ምስለ ትስብእቱ በከመ ይስሐቅ ኢተጠብሐ ምስለ በግዕ ወከማሁ መለኮትኒ ኢሐመ ምስለ ትስብእቱ። ወባሕቱ ጽምረትሰ ፩ ወኢይ ትፈለጥ አሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅፅበተ ዓይን። ኦ ዘኢተፈልጠ መለኮትከ እምትስብእትከ ኢትረስየኒ ፍሉጠ እመርዔተ አባግዒከ ጻድቃን ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ።

(፶፱)ያዕቆብኒ አርአየ አርአያ መስቀል አመ ባረኮሙ ለኤፍሬም ወለምናሴ። አቀሞ ዮሴፍ ለምናሴ በፀጋሙ ኀበ የማነ እስራኤል። ወለኤፍሬም አቀሞ በየማኑ ኀበ ጸጋመ እስራኤል። አስተኃለፈ እስራኤል እደዊሁ ወወደየ እዴሁ

ዘየማን ውስተ ርእሰ ኤፍሬም፣ ወእዴሁ ዘፀጋም ውስተ ርእሰ ምናሴ። ወይቤሎ ዮሴፍ ለእስራኤል። አ አባ እስመ ዝንቱ ዘይልሕቅ ደይ እዴከ ዘየማን ላዕሌሁ። ወይቤ እስራኤል አአምር ወልድየ አአምር። ዝኒ ይከውን ሕዝበ ዐቢየ። አእመረ እስራኤል ከመ በትእምርተ መስቀል ይጸንዕ በረከት።

(፷)ወበእንተዝ ገብረ እደዊሁ አርአያ መስቀል። ወከማሁ ባርኮ ለንጉሥነ ልብነ ድንግል በበረከተ መስቀልከ ቅዱስ ከመ ያዕርፍ ላዕሌሁ በረከተ ያዕቆብ እስራኤል ወሀብተ ጸጋ ዘተውህበ ሎቱ ወለዘርዑ። ቅብዐ ክህነት ወመንግሥት ወትንቢት ኢይሰስል እምኔሁ ወዘርዑ ወእምነ ዘርዐ ዘርዑ። ለዓለመ ዓለም አሜን።

(፷፩)ሚመጠነ ሀብተ ጸጋ ዘተውህበ ለክቡር ዕፀ መስቀልከ።

መስቀልከ ንዋየ ሐቅል ለፀብእ ወሰይፈ መለኮት ዘሐራ ዚአከ።

መስቀልከ ገፍታኤ ማዕከል እንተ ጽልእ ወነሳቴ ጥቅም ዘኃጣውእ።

መስቀልከ አብ ለእጓለ ማውታ ወመኰንኖሙ ለዕቤራት።

መስቀልከ መርስ ለእለ ይትመነደቡ በባሕር፤ ወመርሶ ለእለ ይሳከዩ ውስተ በድው።

መስቀልከ መርሐ ዕውር ወምርጉዘ ሐንካሳን ወኃይሎሙ ለፅቡሳን።

መስቀልከ ዕፅ ዘያልሕቅ ሕፃናተ መሃይማናን በአጥባተ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን።

መስቀልከ አክሊለ ነገሥት።

መስቀልከ ትምክህቶሙ ለመሲሐውያን።

መስቀልከ ዘይሴርዮሙ ለመሠርያን ወይዘርዎሙ ለመሰግላን።

መስቀልከ ሰያሚሆሙ ለካህናት ወአሳዪ ሩጸቶሙ ለዲያቆናት።

መስቀልከ ዘያነሥኦሙ ለውዱቃን፤ ወያረውጾሙ ከመ ኀየል ለፅውሳን።





መስቀልከ ዘኮነ ሕፄሃ ለመርዓት ወሕዳጋቲሃ ለእንተ ደኃርካ በምኩራብ።

መስቀልከ መሠረተ አሚን ወዓምደ ሃይማኖት ለእለ ይትዌከሉ ቦቱ።

መስቀልከ መብጠሴ ኵሉ ሰራይ ወመፅርዔ ኵሉ ሰገል።

በመስቀልከ ወበሰይፈ መዓትከ ሠርዎሙ ለፀረ መስቀልከ። ወእለ ይፈቅዱ ይገፍትኡ ወንጌለ መለኮትከ ይኩኑ ግፍቱዓነ እምገጸ ምድር።

(፷፪)አ እግዚኦ አንህል ቀርነ አይሁድ።

አ እግዚኦ ቀጥቀጥ ቀርነ አረሚ።

አ እግዚኦ ትትለዓል መዓትከ ላዕሌሆሙ፣ ወታንበልብል እሳተ ቅንዓትከ ዲቤሆሙ።

አ እግዚኦ ንስቶሙ ወኢትሕንጾሙ።

አ እግዚኦ አብርቅ መባርቅቲከ ወዝርዎሙ።

አ እግዚኦ ፈኑ አህጻከ ወሁኮሙ።

(፷፫)አ እግዚኦ ንሣእ ወልታ ወኲናተ ወተንሥእ ውስተ ረዲእትየ ለፀቢአቶሙ ለፀርየ። ወይኩን ዘልፈ መቅሠፍትከ ዲበ እለ የሐፍሩ ብከ ከመ ይበሉ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው። ወሰይፈ መዓትከኒ ይኩን ዲበ ኵሎሙ እለ ይሄሰው ቃለ ነቢያት ወኢየአምኑ በትምህርተ ሐዋርያት። እሉ እሙንቱ እለ ይትሜከሁ በኃሣሮሙ ወይዜኃሩ በፍትወተ ልቦሙ። እሉ እሙንቱ እለ ኮንዎ አፍራሰ ለሰይጣን፤ ወኮንዎሙ ማኅደረ ለአጋንንት። በመስቀልከ ሠርዎሙ እምድር ዝክሮሙ። ወአብሆ ካዕበ ለንጉሥነ ልብነ ድንግል መፍቀሬ ዚአከ ከመ ፍጡነ ይሥርዎሙ ወይደምስስ ዝክሮሙ። አብሖ እግዚኦ ለንጉሥነ ልብነ ድንግል ከመ ያመዝብራ ለሀገሪቶሙ። አብሖ እግዚኦ ለንጉሥነ ልብነ ድንግል ከመ ይማዕ ኵሎ ዓላውያነ ኀበ ሖረ ኃይለ መስቀልከ ይኩኖ ረዳኤ ወመሠውረ። መስቀልከ ይባልሆ እምትንሣኤ ፀር ዘኀቡዕ ወዘገሃድ። መስቀልከ ይፍልጥ ሎቱ በሙስና ወበመቅሠፍት ለእለ ይጸልእዎ

ወበሥህል ወበምሕረት ለአለ ያፈቅርዎ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

## ፭

(፲፬)በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ፤ ወበአምኖቱ እትፌሣሕ ከመ ዘረከበ ምሕርካ ብዙኃ።

በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ ወበስሚዖቱ እትኃሠይ ከመ ዘረከበ ወይነጽሩየ።

በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ በከመ ይትሜካህ ወልድ በክብረ አቡሁ።

በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ በከመ ይትሜካህ ገብር በዕበየ እግዚኡ።

በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ በከመ ትትሜካህ ዓመት በክብረ እግዝእታ።

በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ ወእዜኃር ከመ ጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ዘደቤ ሐሰ ሊተሰ እዜኃር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ።

(፲፭)በመስቀልከ እግዚኦ እትሜካህ ወእዜኃር ብከ እንዘ ዕብል

ስብሐት ለከ አ ዘተቀነውከ በሐፃውንተ መስቀል።

ስብሐት ለከ አ ዘተአገሥከ ኃፍረተ መስቀል።

ስብሐት ለከ አ ዘተወከፍከ ሕማማተ መስቀል።

ስብሐት ለከ አ ዘኢተሐከይከ ዐሪገ ዲበ ዕፀ መስቀል።

ስብሐት ለከ አ ዘእመስቀል ወረደከ ውስተ ሲኦል ወነሣእከ ሰቍማ እምእደ ጸላኢ ወሰለብከ እልገቶ ለመስተቃርነ መንግሥትከ። ወነጸሕኮ ለዲያብሎስ ዕቡይ በመስቀልከ።

ስብሐት ለከ አ ዘአጽደፍኮ ለዝጉር በመስቀልከ።





ስብሐት ለከ አ ዘዘለፍኮ ለሞት በመስቀልከ።

ስብሐት ለከ አ ዘቀሠፍኮ ለጽልመት በመስቀልከ።

ስብሐት ለከ አ ዘቀተልኮ ለሞት በመስቀልከ።

ስብሐት ለከ አ ዘአቍሰልኮ ለመቍስሊ በመስቀልከ።

ስብሐት ለከ አ ዘአመዝበርከ እፅዋኒሃ ለሲኦል በመስቀልከ።

ስብሐት ለከ አ ዘአንሐልካ ጥቅማ ለደይን በመስቀልከ።

(፲፮)ትሕትናከ እግዚኦ አውደቆሙ ለዕቡያን። ወኃይለ መስቀልከ ደምሰሰ ለሲኦል። በሞትከ ሐይዉ ምውታን። ወበትንሣኤከ ተኃፍሩ ሰቃልያን፤ ወበቅንዋተ እደዊከ ተደጒጸ ከርሠ ጸላኢ። ወበረምኅ መስቀልከ ተረግዘ አርዌ፤ በሰይፈ መለኮትከ ተወቅየ ርእሱ ለመልአከ ሞት። ወበበትረ ኃይልከ ተፀምደ ርእሱ ለከይሲ። አንተ አሕሰርኮ በመስቀልከ ለአርዌ ዓቢይ ዘበ ዘነቡ ይስሕብ አድባረ ዓለም ወገፍትዖን ለጽኑዓት። ይትሜጠዎ ለውጊዘ ተከዚ ዮርዳኖስ በቀራንብቲሁ ወኢይትከዐው። እምከመ ከሠተ ዓይኖ በሰቡዕ መዋዕል ያስተጋብእ። ወአልቦ ዘይክል ቀዊመ ቅድመ ገጹ። ወአንተሰ አኀሥርኮ በመስቀልከ ወተዋነይከ ወከመ እንተ ዖፍ ሰቁርከ እንጌ ወወደይከ ውስቴቱ ኀልቄተ። ወአርአይኮሙ ለአጋውንተ ሲኦል ወአልበስኮሙ ሐፍረተ ለሐራ ገሃነም።

(፲፯)በከዩ እለ ያበክዩ ወላሐዉ። ቈስሉ እለ ያቈስሉ። ወሐሙ እለ የሐምሙ። ተፈሥሑ ኣሕያን፤ ወአንፈርዓፁ ትኩዛን።

(፲፰)በመስቀልከ ተፈትሑ ሙቁሓን፤ ወጥዕዩ ሕሙማን።

በመስቀልከ ተሥዕረ መርገሙ ለአዳም፤ ወግዕዘተ ሔዋን።

በመስቀልከ ተሰጥቀ ሰቀ ጽልመት፤ ወተሰፍሐ ሠናያን ብርሃን።

በመስቀልከ ተሰብሩ ኆኃተ ብርት፤ ወተቀጥቀጡ መናስግት ዘኀፂን።

በመስቀልከ ተርኀዋ አናቅጸ ገነት ወተነጽፈ ዕረፍት።

በመስቀልከ ተሰልጠ ቃለ አሪት ወተአትበ ራዕየ ትንቢት።

በመስቀልከ ተውህበ ዜና ሰላም። ወተፈነዉ ሐዋርያት ለጽዋዔ አሕዛብ።

በመስቀልከ ተሰብከ ወንጌለ መለኮት፤ወአምኑ መሃይምናን።

በመስቀልከ ገነዩ ቅድሜከ ኢትዮጵያ ወጸላእትከ ሐመደ ይቀምሑ።

(፲፱)በመስቀልከ እምጽባሕ ወእምዓረብ ወመስአ አኰቴት ወስብሐት ይትቄረብ ለስምከ ቅዱስ። ወንሕነኒ ንባርከ ስመከ ቡሩከ። በእንተ መስቀልከ፤ ወንቄድስ ስመከ ቅዱሰ።

በመስቀልከ ናሌዕል ስመከ ልዑለ።

በመስቀልከ ናከብር ስመከ ክቡረ።

(፳)በእንተ መስቀልከ አንተ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ዘትቤሎሙ ለደቂቀ እስራኤል በአፈ ሙሴ ቀኖልዔከ ግበሩ ዘፈረ ደርከኖ ውስተ ጽንፈ ልብስከሙ ከመ ይኩንክሙ ትእምርተ ወንሕነኒ እለ ተጠመቅነ ገበርነ ትእምርተ ዕፀ መስቀልከ ክቡር ከመ ንኩን ፍሉጣን እምእለ ኢተጠምቁ።

(፳፩)አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ዘተሰባእከ እም ቅድስት ድንግል አንተ ኢተአምር ብእሴ ከመ ትቤዝዎ ለዓለም በሕማማተ መስቀልከ ማኅየዊ።

(፳፪)አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ወወልደ እጓለ እመ ሕያው ዘአሰፈውከነ ተሰፋ በመስቀልከ ወትንሣኤከ እም ቅድመ ትሰቀል እንዘ ትብል በከመ ሙሴ ሰቀሎ ለአርዌ ምድር በገዳም ከማሁ ሀለዎ ለወልደ እጓለ እመ ሕያው ይሰቅልዎ ወይቅትልዎ፤ ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት። ወአርዌሰ ዘብርት ዘሰቀሎ ሙሴ በገዳም አኮ ዘብከ ተሰቅለ ዘእንበለ ትእምርት አላ በአርአያ መስቀልከ ተሰቅለ። ዓቀመ ሙሴ ዕፀ መስቀልከ በአርዌ ምድር ዘብርት ግድመ ውስተ ዕፀ። ወበእንተዝ ተማዕተበ አርዌ ምድር ዘብርት ውስተ ዕፀ ዘዐቀመ ወድኅኑ ደቂቀ እስራኤል እምስነነ አርዌ ምድር ምስለ ሕምዝ። ወሊተኒ አድኅነኒ እምስነነ አከይስት ጸሊማን ምሉአነ ሕምዝ በኃይለ መስቀልከ ክቡር፤ እስመ አነ ገብርከ ወልደ ዓመትከ ወወልደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንከ አንተ





ተሣየጥካ በደምከ፤ ወአግዓዝካ በጽፍአትከ፤ ወአሠነይካ በሞትከ፤ ወአስተርአይካ በትንሣኤከ፤ ወአልዓልካ በዕርገትከ፤ ወአሰርጎካ በንብረትከ በየማነ አብ። ወኢታርኅቅ እንከ ምሕረተከ እምኔየ። ርድአኒ ወአድኅነኒ በኃይለ መስቀልከ ሊተኒ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ/ ገብረ መስቀል።

(፳፫)አአኰተከ እግዚኦ ዘሰፋሕከ እደዊከ ዲበ ዕፀ መስቀል ለአቲበ ኵሉ ዓለም ወለአድኅኖ አዳም ወለደቂቁ።

አአኰተከ እግዚኦ ዘበመስቀልከ ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ። ከመ ኢይሰለጥ ላዕሌሆሙ ስልጣነ ሞት።

አአኰተከ እግዚኦ ዘከሠትከ መስቀለከ ለቈስጠንጢኖስ ወልደ እሌኒ እምድኅረ ደፈኑ አይሁድ በጎልጎታ ወኢኃደጎ ለዓለም ይትሐተም በማኅተመ ጽልመት አላ አሠርገውኮ በብርሃነ መስቀልከ፤ ዝውእቱ ፀሐየ ቅዱሳን።

አአኰተከ እግዚኦ ዘፈጸምከ ላቲ ጸሕቃ ለዓመትከ እሌኒ ዘጸመወት በኃሢሠ መስቀልከ።

አአኰተከ እግዚኦ ለጢሰ ዕጣን ዘወሀብካ ትእምርተ ለርከበተ መስቀልከ ቅዱስ።

(፳፬)-አአኰተከ እግዚኦ ዘኢሜጥከ ገጸከ እምስእለታ ወኢያኀፈርካ እምትንታኔ ዘተመነየተ። ወረሰይካ ድልወተ ከመ ትክሥት ብርሃና ለዓለም።

አአኰተከ እግዚኦ ዘበረከበ መስቀልከ መላዕካ ትፍሥሕተ እስከ ትየብብ በአፉሃ ወትጠፍሕ በእዕዳዊሃ ወትጽሕስ በዕገሪሃ።

አአኰተከ እግዚኦ ዘበሐጸውንተ መስቀልከ ዘተገብረ በልጓመ ፈረስ ወልዳ ወአግረረ ፀረ በውስተ ፀብእ ወአኅየልኮሙ ለእለ የአምኑ። ወከማሁ በመስቀልከ ሀበኒ ኃይለ መዊዕ ወአግርር ፀርየ ሊተ ለገብርከ።

(፳፭)ወፈድፋደሰ አአኰተከ እግዚኦ ዘኢረሰይከነ ሱታፈሆሙ ለእስራኤላዊያን እለ ከህዱ መስቀለከ። እሉ እሙንቱ አዝማደ አበዊየ ሐዋርያት በሥጋ ወፀሮሙ እመንገለ ሃይማኖት። በከመ ይቤ ጳውሎስ እመንገለ ወንጌልሰ ፀርነ

እሙንቱ። ወእመንገለ ጎሬሰ አንዊነ። ወሊተሰ አእኰተከ እግዚኦ በእንተ ዘረሰይከኒ ጽሑቀ እምንእስየ በአምልኮ ዚአከ፤ ወውኩል በተስፋ መስቀልከ። ወአልብየ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌከ ወኢ.ምክሀ ዘእንበለ አሚን በመስቀልከ።

(፸፮)አአኰተከ እግዚኦ በእንተ ዘከሠትከ ሊተ መስቀለከ ቅዱሰ ዘቦቱ ተቀነዋ እደዊከ ቅዱሳት እለ ኢተቀንያ ለዓመፃ፤ ወእጋሪከ ቅዱሳት እለ ኢያንሶሰዋ ውስተ ፍናዋተ ኃጕል። ወበላዕሌሁ ረኩብከ ብሂአ ዘምስለ ሐሞት። በዲቤሁ ተረግዘ ገቦከ ቅዱስ። ወአንብሕብሐ ደም ወማይ። አአኰተከ እግዚኦ በእንተ ጸጋ ዘአፈድፈድከ ላዕሌየ፤ ዝ ውእቱ አሚን ዚአከ ወረኪበ መስቀልከ። ተአኰተከ ነፍስየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ ወይሴብሐከ ከናፍርየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ። ይባርኩከ አዕፅምትየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ።

(፸፯)ወይዌድሱከ መለያልይየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ።

እዬብብ በአፉየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ።

ወእኬልሕ በጕርዔየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ።

እጠፍሕ በእደዊዬ በእንተ ረኪበ መስቀልከ።

ወእጽሕስ በእገርየ በእንተ ረኪበ መስቀልከ።

(፸፰)ወይእዜኒ ያብርህ ሊተ መስቀልከ በኵላ ጎበ ወፈርኩ፤ ወበኵላ ጎቤሖርኩ፤ በፍናው ጎበ ነገድኩ፤ ወበውስተ ሀገር ጎበ ባእኩ። መዓልተ ጎበ ነበርኩ ወሌሊተ ጎበ ኖምኩ ኢይርሐቅ እምኔየ ሞገሰ መስቀልከ።

በመስቀልከ እግዚኦ ጎትመኒ ከመ እርከብ መዊዐ ዲበ ጸላእትየ።

ወእዜምር ለከ አምላኪየ በእምጣነ ኃይልየ፤ ወመጠነ ሀሎኩ እቀንት ሰይፈ መለኮትከ ዝውእቱ አሚነ መስቀልከ ቅዱስ። አሚነ መስቀልከ ቅዱስ ዘአብርሃ ሎሙ ለእለ ውስተ ጽልመት ያብርህ ሊተ ማኅቶተ ጥበበከ መለኮታዊ አሜን።

(፸፱)መስቀልከ ዘእንፈጸ ለሰማልያል ሳጥና ወዘረወ ሠራዊቶ ወከማሁ ያንፍጽ ለፀረ ዚአየ ወይዝርዎሙ ለእሊአሁ። ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወትትሌዓል





እዴከ ከመ ትስርዎሙ ለእለ ኢየአምኑ መስቀለከ። የማንከ ትፅብኦሙ ለእለ ይትዌከሉ በመፀልበ ሞትከ።

(፹)ፀልቦከ እግዚኦ ዘውእቱ ዐራተ ሕማምከ ዘበላዕሌሁ ሰከብከ። ጊዜ ስሱ ሰዓት ሆካ ለሰማይ ወአድለቅለቃ ለምድር። በእንተ ሕማምከ ጸልቦከ እግዚኦ ዘውእቱ ዐራተ መርዐከ ዘበላዕሌሁ ተመርዐውካ ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት ወሐፀብካ በነቅዐ ማይ ዘውኀዘ እምኔከ ወሐተምካ በፈልፈለ ደምከ ዘአንጸፍጸፈ እምገቦከ ዘየማን። እስመ እምየማንከ ነቅዐ ሕይወት። ወበእንተዝ ትሴዓለከ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንከ በማኅልየ ሰሎሞን እንዘ ትብል እይቴ ትሰክብ ጊዜ ቀትር ከመ ኢይኩን እንዘ እንጌጊ ውስተ መራዕየ ካልአኒከ። እይቴ ትሰክብ ጊዜ ቀትር ትቤ በእንተ ሰኪቦትከ ዲበ ዕፀ መስቀልከ ጊዜ ቀትር። ትደግም ወትብል እይቴ ትሬኢ፤ እስመ ኵሉ ዘይሬኢ መራእየ ይደልዎ ዐሪገ ውስተ ልዑል መካን ወይሬዒ አባግዒሁ ወይዋኅዮን በአብትር ለተኖልዎ። ወካዕበ ዓዲ ትደግም ወትብል ከመ ኢይኩን እንዘ እንጌጊ ውስተ መራእየ ካልአኒከ። ዝ ብሂል እምረኒ ጎበ ትሰቀል ከመ እእምን በመስቀልከ፤ ወከመ ኢይትልዎሙ ለኖሎት ካልአን እለ የዐቅቡ መራእየ ዓመፃ ወኢይነግፍዎሙ አባግዒሆሙ እምአፈ ተኵላ።

(፹፩)ወሊተኒ እግዚኦ ረአየኒ በበትረ ምሕረትከ ዘይመይጥ ውስተ ፍና ጽድቅ። በከመ ይቤ ዳዊት በትረ ጽድቅ ወበትረ መንግሥትከ። አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላእከ። ወበእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ ቅብዐ ትፍሥሕት እምእለ ከማከ። ከርቤ ወቀንዓት ወሰሊሆት እምነ አልባሲከ እም ከቡዳነ አቅርንት ዘእምኔሆሙ አስተፈሥሐከ። እለ መኑ እሙንቱ ከቡዳነ አቅርንት ዘእንበለ ዳእሙ ነገሥተ እሕዛብ ወነገሥተ ኢየሩሳሌም። ወከቡድ ሢመተ መንግሥት አዕረፈት ላዕሌሆሙ። ወዘይቤሰ ዘእምኔሆሙ አስተፈሥሐከ ውእቶሙሰ ኢከሀሉ አስተፈሥሖቶሙ ለእለ ውስተ ደይን። ወአንተሰ አስተፍሣሕኮሙ ለእለ ውስተ ደይን በመስቀልከ።

(፹፪)አንተ ውእቱ እግዚኦ ዘላዕለ ኵሉ፤ ወሥልጣንከ ዲበ ኵሉ፤ ወዕበይከ በመልዕልተ ኵሉ። እግዚኦ ኵሉ ተሠመ ይከ፤ ወበኵሉ ተብህልከ።

አንተ ውእቱ ሊቀ ካህናት።

አንተ ውእቱ ንጉሠ ነገሥት።

አንተ ውእቱ ዐቢይ ነቢይ።

አንተ ውእቱ ሊቀ ኖሎት።

አንተ ውእቱ በግዕ ነባቢ።

አንተ ውእቱ ላሕም መግዝዕ።

አንተ ውእቱ አንበሳ እጓለ አንበሳ።

አንተ ውእቱ አዘቅተ ማየ ሕይወት።

አንተ ውእቱ ቀርነ መድኃኒት።

አንተ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት።

አንተ ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ።

አንተ ውእቱ ኮከበ ብርሃን።

አንተ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት።

አንተ ውእቱ ጽዋዐ መድኃኒት።

አንተ ውእቱ አንቀጽ።

አንተ ውእቱ ወልደ እጓለ እመሕያው ወወልደ እግዚአ ብሔር።

ዘንተ ኵሎ ተሠመይከ በአንተ ፍቅረ ዚአነ።

(፳፫)ሊቀ ካህናት እንከ ተሠመይከ በከመ ይቤ ዳዊት በእንቲአከ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ። መልከ ጼዴቅሰ አመ ተራከበ ለአብርሃም ወአውጺአ ኅብስተ ወወይነ ወመጠዎ። ወአንተኒ ነሣእከ ኅብስተ ስርናይ ወጽዋዐ ወይን ወመጠውኮሙ ለአርዳኢከ እንዘ ትብል ዝንቱ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ። ዝንቱ ጽዋዐ ወይን ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአከሙ ይትወሀብ





ለቤዛ ብዙኃን። ቡሩክ አንተ እግዚአ ምሥጢረ ኅቡዐ ዘእመስቀልከ አርአይከነ። ቡሩክ አንተ እግዚእ።

(፳፬)ንጉሠ እንከ ተሠመይከ፤እስመ ይቤሎ ያዕቆብ ለይሁዳ ወልዱ በእንቲአከ፤ ይወፅእ እምኔከ ንጉሥ ዘየሐፅብ በወይን ልብሶ። ወበደመ ቀይሕ አፅፎ ዘየአስር በሐረገ ወይን አድጎ፤ ወበዕፀ ኢሎቄ ዕዋሎ።

(፳፭)ነቢየ እንከ ተሰመይከ፤ እስመ ይቤ ሙሴ በእንቲአከ ነቢየ ያነሥእ ለከሙ እግዚአብሔር እምውስተ አኀዊከሙ ዘከማየ ወዘይኄይስ። ወኵሉ ዘኢሰምዖ ለውእቱ ነቢይ ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምነ ሕዝባ። ዘከማየ ይቤ በእንተ ሕግ ሐዲስ ዘወሀብኮሙ ለአርዳኢከ ንጹሐን። በከመ ይቤ ወሀበ ሙሴ ሕገ ብሉየ ለደቂቀ እስራኤል፤ እስመ አልቦ እንከ ነቢይ ወሀቤ ሕግ ዘእንበለ ሙሴ ወዘእንበሌከ በከመ ይቤ ጳውሎስ፤ እስመ ከመ ሙሴ ምእመን በኵሉ ቤቱ። ወባሕቱ የዐቢ ክብሩ እምዘሙሴ። ወዘይቤሰ ሙሴ ወኵሉ ዘኢሰምዖ ለውእቱ ነቢይ ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምነ ሕዝባ በእንተ ሕዝበ አይሁድ እለ ዐለዉከ። ወበእንተዝ ትቤሎሙ ለአይሁድ ሶበሰ እምአመንክምዎ ለሙሴ እም አመንክሙኒ ኪያየ፤ እስመ በእንቲአየ ዘጸሐፈ ሙሴ። ወእመሰ ዘጸሐፈ ሙሴ ኢተአምኑ ወእፎ ቃልየ ተአምኑ።

(፳፮)ኖላዌ እንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር በእንቲአከ። ኖላዊሆሙ ለእስራኤል አፅምዕ። ዘይሬእዮሙ ከመ አባግዐ ለዮሴፍ። ወለሊከኒ ትቤ በቃለ ወንጌ ልከ ቅዱስ። አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር ዘእሜጡ ነፍስየ ቤዛ አባግዕየ። አማንከ አንተ ኖላዊ ኄር ዘመጦከ ነፍሰከ ቤዛ አባግዒከ በዲበ ዕፀ መስቀልከ።

(፳፯)በግዐ እንከ ተሠመይከ፤ እስመ ስምዐ ኮነ በእንቲአከ ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ፤ እንዘ ይብል ነበበ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም። አማንከ በግዕ አንተ ዘበአማን ዘተጠባሕከ በዲበ ዕፀ መስቀልከ ለመድኃኒተ ውሉደ ሰብእ።

(፳፰)ላሕመ እንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ በእንቲአከ ዳዊት አሠምሮ ለእግዚአብሔር እምላሕም ጣዕዋ ዘአብቈለ ቀርነ ወጽፍረ። ወበእንተ ወልድሂ

ዘኀርተሙ ተነግረ በውስተ ወንጌል ቅዱስ ዘከመ ይቤ አቡሁ አምጽኡ ላሕመ መግዝዐ ወጥብሑ ንትፈሣሕ፤ እስመ ዝንቱ ወልድየ ሞተሂ ወሐይወ፤ ተኀጕለሂ ወተረክበ። ወላሕምሰ መግዝዕ አንተ ውእቱ ዘተሠዓከ ዲበ ዕፀ መስቀልከ ለምሳሐ ቅዱሳን።

(፹፱)አንበሳ እጓለ አንበሳ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤሎ ያዕቆብ ለይሁዳ ወልዱ እንዘ ይትኔበይ በእንቲአከ ይሁዳ እጓለ አንበሳ ዕረግ ወልድየ እምኀዘአትከ። ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ። ወኢልበ ዘያነቅሐከ። ኢይጠፍእ ምልክና እምይሁዳ ወምስፍና እምአባሉ እስከ አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ። ወውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ።

(፺)ቀርነ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር በሀየ እበቍል ቀርነ ለዳዊት ወአስተዴሉ ማኀቶተ ለመ ሲሕየ። ዘካርያስኒ ይቤ አንሥአ ለነ ቀርነ መድኀኒትነ እም ቤተ ዳዊት ቍልዔሁ በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለ እምዓለም ኦሥመርዎ። ዳዊትኒ ይቤ ወእምአቅርንት ዘ፩ ቀርኑ ለብሕቱትየ። ወካዕበ ይቤ ወይትሌዓል ቀርንየ ከመ ዘ፩ ቀርኑ። ወይጠልል በቅብዕ ሲበትየ።

(፺፩)ዕብነ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ ዳንኤል በእንቲአከ ዕብን ተበትከ እምደብር ነዋህ ዘእንበለ እድ። ወሐረፀ አምሳለ ዘወርቅ። ዳዊትኒ ይቤ በእንቲአከ ዕብን ዘመነንዎ ነደቅት ውእቱ ኮነ ርእሰ ማእዘንት። እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ። ወነካር ይእቲ ለአዕይንቲነ። ዕብነ ሕይወት አንተ ለእለ የአምኑ ብከ። ወዕብነ ዕቅፍት አንተ ለእለ ኢየአምኑ ብከ ወለእለ ይትዓቀፉ በቃልከ። ወዕብነ ካህድ አንተ ለእለ ኢያሰምኩ በመስቀልከ። አንሰ አሰመኩ ብከ ኦ ዕብነ ሕይወት፤ ወአመንኩ ብከ ከመ አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው። ከለለኒ ከመ ወልታ ሥሙር በኃይለ መስቀልከ ለገብርከ።

(፺፪)አዘቅተ ከብር ዘማየ ሕይወት አንከ፤ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ ኢሳይያስ እንዘ ይዘልፎሙ ለእለ ይሰቅሉ ርእዩዋ ለኵሎሙ ዐንዐት አንተ ወቀርከሙ ወአዘቅት እምቅት አንተ ከረይከሙ። ለሊከኒ ትቤ በወንጌልከ ወዘሂ ይሰቲ እማይ ዘእሁቦ አነ ኢይጸምእ። ማየ ሕይወት ይውኅዝ እም ከናፍሪከ።





(፺፫)ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ትቤ ለሊከ በወንጌል ቅዱስ አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት። ዘየሐውር አንተ ኀቤየ ኢይትዓቀፍ፤ እስመ ይሬኢ ብርሃነ ዝንቱ ዓለም።

(፺፬)ፀሐየ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ትብል ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእንቲአከ ኢትርአያኒ፤ እስመ አነ ጸላም፤ እስመ ኢርአየኒ ፀሐይ። ወበመጽሐፈ ኪዳን ትቤ ርእሰከ ፀሐይ ዘኢየዐርብ ማኀቶት ዘኢይጠፍእ፤ ፀሐይ ዘዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን።

(፺፭)ኮከበ ብርሃን አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ በለዓም እንዘ ይትኔበይ አመ ጸውዖ ባላቅ ወልደ ሶፎር ይሠርቅ ኮከብ እምያዕቆብ። ወያስተርኢ እም እስራኤል። ወለአቡቀለምሲስ ትቤሎ አነ ውእቱ ኮከበ ብርሃን ጽባሐዊ። ዘእም ሥርወ ዳዊት ሠረፀ። ብርሃን ዘእምብርሃን አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ትቤ ለሊከ አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም። አንሶስዉ እንዘ ብከሙ ብርሃን ዘእንበለ ይርከብክሙ ጽልመት። እመኑ በብርሃኑ ከመ ትኩኑ ውሉደ ብርሃን። ዮሐንስኒ ወልደ ነጐድጓድ ይቤ ወሀሎ ፩ብእሲ ዘተፈነወ እምኀበ እግዚአብሔር ዘስሙ ዮሐንስ። ወውእቱ መጽአ ሰማዕተ ይኩን በእንተ ብርሃን ከመ ኵሉ ይእመን ቦቱ። ወለሊሁሰ ኢኮነ ብርሃነ ዳዕሙ ከመ ሰማዕተ ይኩን በእንተ ብርሃን። ወብርሃን ጽድቅሰ ዘያበርህ ለኵሉ ሰብእ ዘመጽአ ውስተ ዓለም። ወዓለምሰ ኢያእመሮ።

(፺፮)ኅብስተ ሕይወት አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ትቤ አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት። ዘበልዐ ሥጋየ የሐዩ በእንቲአየ።

((፺፯)ጽዋዐ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ለሊከ ትቤ ንስዑ ስትዩ፤ ዝንቱ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ። ወካዕበ ትቤ ዘሰትየ ደምየ ኢይጥዕም ለሞት።

(፺፰)አንቀጸ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ለሊከ ትቤ አነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ። ዘቦአ አንተ ኀቤየ ይበውእኒ ወይወፅእኒ ወይረክብ ምርዓየ።

(፺፱)ጽጌ አንከ ተሠመይከ፤ እስመ ይቤ ኢሳይያስ በእንቲአከ ትወፅእ በትር እምሥርወ እሴይ፤ ወየዐርግ ጽጌ ወእም ጕንዱ። ወየዐርፍ ዲቤሁ መንፈሰ

እግዚአብሔር ወመንፈስ ልቡና ወንጽሕ፤ መንፈስ ጥበብ ወአእምሮ። ቤተ ክርስቲያን ትብል በእንቲአከ ከናፍሪሁ ጽጌ እለ ያውኅዛ ከርቤ ፍጹመ።

(፻)ወልደ እጓለ እመሕያው እንከ ተሠመይከ፤ ተወሊደከ እምዘርዐ ዳዊት በሥጋ ሰብእ ወልደ እግዚአብሔር አንተ በህላዌከ። ወነገርከነ ለሊከ እንዘ ትብል፤ እስመ ወልደ እጓለ እመሕያው ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ።

(፻፩)አመንኩ ብከ አ ወልደ እግዚአብሔር ከመ አንተ ውእቱ መድኅነ ዓለም፤ ወፈዳዬ ኃጢአቶሙ ለደቂቀ አዳም።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ ጸዋሬ መስቀልከ በእንተ መድኃኒተ ውሉደ ሰብእ።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ አምላክ ወልደ አምላክ።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ ብርሃን ወልደ ብርሃን።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ ውኂዘ ማየ ሕይወት ንጹሕ ዘእም ንጹሕ ነቅዕ፤ ሕይወት ዘእምሕይወት፤ ወልድ ዋህድ ዘእምኔ እግዚአብሔር።

(፻፪) አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ ዕሩየ መለኮት አንተ ምስለ ዘወለደከ፤ ወህቡረ ህላዌ ምስለ አቡከ።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ ጽንዐ ሃይማኖት ወኢይትበተክ ፈትለ ትሥልስትከ ዘምስለ አቡከ ወመን ፈስከ።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ አክሊለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወሠርጐ መሃይምናን።

አመንኩ ብከ እግዚኦ ከመ አንተ ውእቱ መዓዛ ዕፍረት ቅድው ዘብከ ተቀብዑ ካህናት ወብከ ተቀብዑ ነገሥት መሢ ሐውያን። ወብከ ተመልዑ መላእክት።

(፻፫)ኢታእትት እምላዕሌየ ቅብዐ ጸጋ እግዚአብሔር አንተ እምነቤከ። ወሐጽረኒ በሐጹረ መስቀልከ። በላ ለነፍስየ አነ ውእቱ ረዳኢኪ። ሐተምኩኪ በእዴየ አዚዝ ወበመስቀልየ ማኅየዊ። ወኢታብሖሙ ለአጋንንት ለለከፈ





ሥጋየ። ወበጽላሎተ መስቀልከ ክልለኒ። ወበጽላሎተ ክነፊከ ሕቅፈኒ ከመ ዖፍ እንተ ተሐቅፍ እጕሊሃ ታሕተ ክነፊሃ። ወባርከኒ በበረከተ አበዊነ አዳም ወሴት ወሄኖክ፤ በበረከተ ኖኅ ወሴም ወያፌት፤ በበረከተ አብርሃም ይስሐቀ ወያዕቆብ እስራኤል፤ በበረከተ ሙሴ ወአሮን ወኵሎሙ ነቢያት፤ በበረከተ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ወኵሎሙ ሐዋርያት፤ በበረከተ ሰማዕት መዋዕያን፤ ወበረከተ ደናግል ንጹሐን፤ ወበበረከተ ጻድቃን ወመስተጋድላን፤ ወበበረከተ መላእክት ትጉሃን፤ ወበበረከተ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ ወፈድፋደሰ በትንብልናሃ ለቅድስት ወንጽሕት ወቡርክት ማርያም ወላ ዲተ አምላክ፤ በበረከተ መስቀልከ ክቡር ወማኅየዊ ማእተበ ጸጋ ትእምርተ መድኃኒት። ለይኩን ብርሃንከ ላዕሌየ ለገብርከ ፍሥሐ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

(፻፬) ሰላም ሰላም ለመስቀለ ዋህድ ሰላም፤

ዘንሳለም ይምና ወጽግሞ

ከዋሎ ወፍጽሞ።

ለብሔረ ሰላም ንስአሞ

ዘእግዚአብሔር ቀስታሞ።

ዘኮና አራተ ሕማሞ።

ውተቀብዐ ደሞ።

ንብሎ ሰላም በኢያርምሞ

እንዘ ንጼውዕ ስሞ።

ለአርዌ ዘተጸሞ።

ወገመጸ ፍጽሞ

ወንበላ ሰላመ ለወላዲቱ በእንተ ዘኮነቶ እሞ

ተሠምየት በንጽሕ ጽርሐ አርያሞ

ኃይለ ጸሎታ ይኩነነ ጸረ አድከሞ።

ዝከራ ለተርጉሞ

ስእንኩ ፈጽሞ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ለዘፈጠረ ከመ ናምልኮ።

††††††††††††††††††††††††





# ክፍል ሁለት

# የአማርኛ ትርጉም

## ፩

(፩)ትናንት የሌለበት ቀዳማዊ፣

ዛሬ የሌለበት ማዕከላዊ፣

ነገ የሌለበት ደኃራዊ በሚሆን በእግዚአብሔር ስም

ለዘመኑ ሥፍር ሳይኖርበት ጥንታዊ ነው፤

ድካም ሳያገኘው ሁሉን የፈጠረ ነው፤

መጠን የሌለው የምሕረት ባሕር ነው፤

(፪)ታላቅነቱ እንዴት እንደሆነ፣ ምስጋናውንም ከፍ ከፍ በማድረግ ውዳሴ መስቀልን እንጽፋለን፣

አስቀድሞ ስለ እርሱ እንዴት ትንቢት እንደተነገረ፤

መስቀል ዕፀ ሕይወት ነው፤

መስቀል ዕፀ መድኃኒት ነው፤

መስቀል ዕፀ ትንቢት ነው፤

መስቀል ዕፀ ዕረፍት ነው፤

(፫)መስቀል ሰይጣንን የሚያጠፋ ምሳር ነው፤ የአጋንንትንም ራሶች የሚቆርጥ ሰይፍ ነው፤

መስቀል ርኩሳን መናፍስትን የሚወጋቸው የእሳት ዘገር ነው፤ የአመስቴ ማውያንንም[13] ሠራዊት የሚመታ የመብረቅ ጦር ነው

መስቀል ማኅተመ ሥላሴ[14] የሌለው ሰው ወደእርሱ ሊቀር በው የማይቻለው አምባ መጠጊያ ነው

መስቀል ከግራም ከቀኝም ለሚመጣ (ጠላት) የጽድቅ ጋሻ ነው

ጳውሎስ ‹ውጊያችሁ ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም[15]› እንዳለው መስቀል የጦር መሣርያ ነው

መስቀል የጦር ውጋት ሊቀድደው፣ የቀስትና የዘንግም ጫፍ ሊበሳው የማይችል የሃይማኖት ጥሩር ነው

መስቀል አማሌቃውያንን ለመዋጋት በራፊድ በረሐ በተዘረጋው በሙሴ እጅ አምሳል የተሠራ ነው[16]

መስቀል በሙሴ እጅ ወደ ውስጥ በተጨመረ ጊዜ መራራውን ውኃ በሱር በረሐ ያጣፈጠ ነው[17]

መስቀል የቅድስናና የንጽሕና ማኅተም ነው

[13] በዕብራይስጡ ‹ማስጤማሕ› ካለው የተወሰደ ሲሆን ‹ጠላት፣ ከሳሽ፣ጠበኛ› ማለት ነው›› በቤተ ክርስቲያን ድርሰቶች አጋን ንትን ሠራዊተ መስቴማ ይላቸዋል:: ከሳሽ ‹ሰይጣን› ማለት ሲሆን ‹ሠራዊተ መስቴማ› የሰይጣን ሠራዊት ወይም አጋንንት ማለቱ ነው::

[14] ማኅተመ ሥላሴ ያለው የሥላሴን ልጅነት ነው::

[15] ኤፌ 6÷12

[16] ዘጸ 17÷ 81-3

[17] ዘጸ 15÷23-25





መስቀል ለሚጋደሉ የድል አክሊል፣ ወደ በጉ ሰርግ ለተጠሩትም የሰርግ ልብሳቸው ነው[18]

መስቀል የማይነጥፍ ምንጭ፣በቁዔትም (ጥቅምም) የሞላበት የክብር ጉድጓድ ነው

(፬)መስቀል አራቱ ወንዞች የሚያጠጡት የገነት ዛፍ ነው:: የመጀመርያው ወንዝ ስሙ ኤፌሶን ይባላል፣ እርሱም እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ያዘጋጀውን የምሥጢርን ወይን ያፈስሳል፤ የሁለተኛውም ስም ግዮን ነው፣ ከእርሱም የንጹሐን ዕድል ፈንታ የሚሆን ማር ይፈስሳል፤ የሦስተኛውም ወንዝ ስም ጢሮስ[19] ይባላል፣ እርሱም የሚጋደሉትን ሥጋ የሚያለመልም የዘይትን ቅባት ያፈስሳል፤ የአራተኛውም ወንዝ ስም ኤፍራጥስ ይባላል እርሱም የማስተዋልን ወተት ያመነጫል፣ እርሱም የደስታና የሐሴት መጠጥ ነው[20]

የወይን ወንዝ ማነው? የማርስ ወንዝ ማነው? የዘይትስ ወንዝ ማነው? የወተትስ ወንዝ ማነው? ፈለገ ወይን ከተሰኘ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፤ ከጎኑ የደስታ ወይን ፈስሷልና[21] ዳዊት ‹በልባችን ውስጥ ደስታን ጨመርክ፣ ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ[22] ዘይትም ፊትን ያበራል?[23]› እንዳለ::

(፭)ነቢዩ ሦስቱን በአንድ ቃል አጣምሮ አመለከተ፤ ‹ከስንዴ ፍሬና ከወይን› ሲል ስለ እግዚአብሔር ልጅ ቁርባን ስለ ሥጋውና ደሙ መናገሩ ነው፤ ‹ዘይትም ፊትን ያበራል› ሲልም ለጥምቀት ማኅተምነት ስለተሰጠው ስለ በለሳን[24] ቅብአት ነው:: እርሱም የጌታችን የልስላሴው ምሳሌ ነው:: እርሱን

[18] ማቴ 22÷1-4

[19] ጤግሮስን ማለቱ ነው::

[20] ዘፍ 2÷10-14

[21] የደስታ ወይን ያለው በተሰቀለ ጊዜ ከጎኑ የፈሰሰውን ደሙን ነው::

[22] መዝ 4÷7-8

[23] መዝ 103÷15

[24] የሽቱ እንጨት ሲሆን በይሁዳና በገሊላ ይልቁንም በኢያሪኮ ይበቅላል::ቅብዐ ሜሮን የሚዘጋጀው ከእርሱ ነው:: (ኪወክ፣ 274)

በማመን የሚኖር ሁሉ አይሻከርም፣ ከሐር ይልቅ ለስላሳ ይሆናል እንጂ:: ስለዚህም ምክንያት ጽኑዕ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በዚህ የበለሳን ዘይት ይታተማል:: የክርስቶስን ልስላሴውን ይለብስ ዘንድ፤ ዳዊት በመዝሙር ‹በፊቴ ማዕድን አዘጋጀህልኝ፣ በጠላቶቼ ፊት ለፊት፤ ራሴንም በዘይት ቀባህ፣ ጽዋዬም የተትረፈረፈ ነው› እንዳለው[25]፤ በዚህም መዝሙር መጀመርያ ላይ ‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤የሚያሳጣኝም የለም[26]› አለ:: በክርስቶስ የሚያምን የክርስቶስ መንጋ ነው:: እግዚአብሔርም እረኛው ይሆናል፤ ከመንፈስ ቅዱስም መንገድ አንዳች የሚያጣው ነገር የለም:: ዳግመኛም ደግም እንዲህ ይላል ‹በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፣ በዕረፍት ወኃ ዘንድ ይመራኛል፣ ነፍሴን መለሳት፣ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ›[27] የለመ ለመው መስክ የተባለች የክርስቶስ መንጋ የሚሠማራባት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ‹በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል› ማለትም ጥምቀት ነው:: ‹ነፍሴን መለሳት፣ በጽድቅ መንገድም መራኝ› ማለትም ካለማወቅ ወደ ማወቅ መለሰኝ ማለት ነው::

(፮)በእውነትም በስምህ የተነሣ በሞት ጥላ ውስጥ እንኳን ብሔድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም[28]:: በክርስቶስ የሚያምንም ሁሉ ከስሙ የተነሣ ሞትን አይፈራም:: በወንጌል ‹በሰው ፊት የሚመሰክርልኝን ሁሉ በሰማያት በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊት የሚክደኝንም፣ እኔም በሰማያት በአባቴ ፊት እክደዋለሁ›[29] እንደሚል:: ደግሞም ነቢይ ‹በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል[30]› ይላል:: ‹በትርህ› ያለው የሃይማኖትን በትር ነው:: ወደ መናፍቃን ስሕተት እንዳንወድቅ በእርሱ እንመረኮዛለንና:: ‹ምርኩዝህም› ሲል ምርኩዘ መስቀልን ማለቱ ነው:: ምእመናን ከመናፍቃን ጋር እንዳ ይተባበሩ በእርሱ ይገሠጻሉና::

---

[25] መዝ 22÷5
[26] መዝ 22÷1
[27] መዝ 22÷2-3
[28] መዝ 22÷4
[29] ማቴ 10÷32-33
[30] መዝ 22÷4





(፯)‹በፊቴ ማዕድን አዘጋጀህልኝ› ሲልም ይህንን ስለ ሥርዓተ ቁርባን ይናገራል:: ደግሞም ‹ራሴን በዘይት ቀባህ› ይላል:: ይህንንም ስለ በለሳን ዘይት ይናገራል:: የሐዋርያት ትምህርትም ‹የበለሳን ዘይት የሃይማኖት ኃይል ነው›[31] ይላል:: በዚህም የተነሣ መድኃኒታችን የወይንና የዘይት ወንዝ ተሰኘ:: ዳግመኛም የማርና የወተት ወንዝ ተባለ:: ለአባቶቻችን ማርና ወተት የምታፈሰውን ምድር ሊያወርሳቸው ተስፋ ሰጥቷቸው ነበርና:: ይህም ከመድኃኒታችን ጎን የፈሰሰው የሐዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው:: ዳዊት ‹ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ ከማርና ከስኳርም ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ[32]› አለ:: ቤተ ክርስቲያንም ‹አንደበቱ እጅግ ጣፋጭ ነው፤ እርሱም ፈጽሞ ያማረ ነው[33]› ትላለች:: ዳግመኛም ‹ማሬን ከእንጀራዬ ጋር በላሁት፣ ወይኔንም ከወተቴ ጋር ጠጣሁት›[34] ትላለች:: ይህም የአሪት ደስታ ከተበላ በኋላ የተሠራውን መሥዋዕተ ወንጌል ነው:: ያዕቆብም ‹ዓይኖቹ ከወይን ይቀላሉ፣ ጥርሶቹም ከወተት ይልቅ ይነጣሉ[35]› አለ:: በዚህም ምክንያት አምላካችን አማኑኤል የማርና የወተት ወንዝ ተብሎ ተጠራ::

(፰)ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና በገነት ዛፎች መካከል ስለተተከለው ሕይወት ዛፍ እንናገር:: ዕፀ ሕይወት የተባለም መስቀል ነው:: የገነት ዛፎች የተባሉትም ምእመናን ናቸው:: በራስዋ ላይ መርገምን ባመጣችው በሔዋን ፋንታም ድንግል በረከትን ከመልአኩ ሰማች:: እርሱም ‹አንቺ ቡርክት ነሽ፣ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው[36]› አላት:: የአምላክን ትእዛዝ በመተላለፍ ከዛፏ በበላው በአዳም ፋንታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቱ ቃል በመታዘዝ እጆቹን በዕፀ መስቀል ላይ ዘረጋ:: ከገነት በሚወጡትና ወደ አራቱ መዓዝነ ዓለም በሚከፋፈሉት በአራቱ ወንዞች ፋንታም በአራቱ መዓዝን የተሰበኩ አራቱ የተቀደሱ ወንጌላት አሉ::

---

[31] ዲድስቅልያ፣ ዐንቀጽ 3
[32] መዝ 118÷103
[33] መኃ 5÷16
[34] መኃ 5÷1
[35] ዘፍ 49÷12
[36] ሉቃ 1÷28

(፱)አ፣ የእግዚአብሔር የጥበቡ ጥልቅነት፤ አባታችንን አዳምን ከመፍጠሩ በፊት የሚመገበውንና ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ አዘጋጀለት፡፡ ጻድቃንም ከመወለዳቸው በፊት የደስታን ገነት አስቀድሞ አዘጋጀላቸው፡፡ ኃጥአንም ከመወለዳቸው በፊት መከራ የሚቀበሉበትን ገሃነም አዘጋጀ፡፡ ሳይፈጥራቸው በፊት ሥራቸውን ዐወቀ፡፡ ከእናታቸው ማኅፀን ሳይወጡ በፊትም መኖርያቸውን አዘጋጀላቸው፡፡ በመጽሐፈ ኪዳን ላይ እርሱ ራሱ «ከመታሰቡ በፊት ሁሉን ያውቃል፤ ከመታሰቡም በፊት ይመረምራል» እንዳለ[37]፡፡ ዳዊትም ኃጥአን ሳይፈጽሙት በፊት ሥራቸውን እንደሚያውቅ ሲናገር እንዲህ ብሏል ‹ኃጥአን ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ፤ ከሆድ ጀምረውም ሳቱ፣ ሐሰትንም ተናገሩ›[38]፡፡ ነቢይ ይህንን ያለው የሐሰተኞችን ኃጢአት ከእናታቸው ማኅፀን ሳይወጡ በፊት ስለመታወቁ ነው፡፡

(፲)በሆድ ውስጥ ከማን ጋር ተነጋግረው ነው? ከማንስ ጋር ሐሰትን ተናገሩ? የቅዱሳን ጽድቃቸው በእግዚአብሔር ስለ መታወቃቸው እግዚአብሔር ለኤርምያስ ‹ከእናትህ ማኅፀን ሳትወጣ በፊት ዐወቅኩህ፤ ሳልፈጥርህም በፊት ቀደስኩህ[39]› ያለውን እንናገራለን፡፡ ነቢዩም ‹ያዕቆብን ወደድኩ፤ ዔሳውንም ጠላሁ› ብሏል፡፡ ይህም የሁለቱም ተግባራቸው ሳይለይ በፊት፣ ዔሳውም ብኩርናውን ለያዕቆብ ሳይሸጥ በፊት ነው፡፡ እግዚአብሔርም ለርብቃ ‹በሆድሽ ውስጥ ያሉት ሁለት ሕዝቦች ናቸው፤ ሁለትም ሕዝብ ከሆድሽ ይወጣሉ፤ ከሕዝብም ሕዝብ ይበልጣል፤ ታናሹም ለታላቁ ይገዛል[40]› አላት፡፡

(፲፩)ሔዋንንም ስለ ድንግል ማርያም ብሎ ‹ሕይወት[41]› ብሎ ጠራት፡፡ የዓለም ሁሉ ሕይወት ከእርስዋ እንደሚወጣ ፈጣሪ ዐውቋልና፡፡ በገነት ዛፎች መካከል ያለውንም ዛፍ ‹የሕይወት ዛፍ›[42] ብሎ ጠራው፡፡ በመስቀሉ ዓለም

[37] ኪዳን ዘነግህ
[38] መዝ 57÷3
[39] ኤር 1÷5
[40] ዘፍ 25÷22-24
[41] ዘፍ 3÷20
[42] ዘፍ 2÷9





ሁሉ እንደሚድን ዐውቋልና፡፡ የሕይወት ዛፍም አስቀድሞ በአምላክ እጅ በገነት ዛፎች መካከል ተተክሎ ነበር፡፡ በቀራንዮም በአይሁድ እጅ ተተከለ፡፡ አይሁድም መስቀሉን ከእርሱ ለእርሱ አቀረቡለት፡፡ በፈቃዱ ለሕማም ሰጡት፤ ይገድሉትም ዘንድ ወደደ፡፡ እነርሱም መታሰቢያው ከገጸ ምድር የሚጠፋ መሰላቸው፡፡ በመስቀሉ እንደሚሰደዱ፣ በትንሣኤውም እንደሚለዩ አላወቁምና፡፡

(፲፪)አ፣ እጅግ የሚደንቅ ነው፤ የተሰቀለው ድል አደረገ፣ የሰቀሉትም ድል ሆኑ፤

አ፣ እጅግ ያስገርማል፤ የሞተው ያሳፍራቸዋል፣ የገደሉትም ያፍራሉ፤

አ፣ እጅግ ያስደምማል፤የታመመው መከራን አመጣ፤ ሕማሙንም ያመጡበት መከራው ደረሰባቸው፡፡ ዕፀ መስቀሉን የተከሉት ተሰደዱ፤ እርሱን የሰቀሉት በዓለም ተበተኑ፡፡ ሊቀ ካህናቱም በራሱ ላይ ‹ሕግ አለን፤ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፤ እርሱ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓልና›[43] አለ፡፡ እነርሱም ለእግዚአብሔርና ለሙሴ ሕግ የሚቀኑ መሰላቸው፡፡ ከሰቀሉት በቀር እግዚአብሔር ማነው? ከሰቀሉትስ በቀር ኦሪትን የሰጠ ማነው? በአፋ ቸው ወደዱት፤ በአንደበታቸው ግን ዋሹት፡፡ ሐሰትን ሊናገሩ በወደዱም ጊዜ እውነቱን ተናገሩ፡፡ ‹ሕግ አለን፤ በሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል› ሲሉ እውነት ተናገሩ፡፡ ሙሴ በሕጉ ላይ ‹መድኃኒታችሁን በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ታዩታላችሁ[44]› አለ፡፡ ፀሐይ እያላቸው በብርሃኑ ግን የማይመላለሱበት ሕግ አላቸው፡፡ ሕይወትን ለሞት ለመስጠት፣ ነገር ግን በሚያድናቸው ላለመ ጠቀም የሚሆን ሕግ አላቸው፡፡ በጉን እንዲያርዱት ነገር ግን ካረዱት በግ እንዳይበሉ የሚያደርግ ሕግ አላቸው፡፡ የምሥጢሩን ወይን የሚቀዱበት ነገር

[43] ዮሐ 19÷ 7
[44] ይህ ጥቅስ እኛ በምናውቀው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም፤ ያላገኘነው ቅጅ ይኖራል፤ ምናልባትም በዘኁ 21÷9 ያለውን ሊያነሣ ይሆናል፡፡

ግን የማይቀዱበት ሕግ አላቸው፡፡ ቀያፋም ‹ሕዝብና ዓለምም ሁሉ ከሚጠፉ አንድ ሰው ብንገድል ይሻለናል›[45] አለ፡፡

(፲፫)በእውነትም የእግዚአብሔርን ልጅ ሊገድሉት ይገባል፤ ለሙታን ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ በእውነትም የእግዚአብሔርን ልጅ ሊገድሉት ይገባል፤ በመስቀሉ ዓለምን ይቀድሳት ዘንድ ባይሰቀል ኖሮ ባልዳንንም ነበር፡፡ ባይሞት ኖሮ ሕይወትን ባላገኘን ነበር፡፡ የእነርሱ ስሕተት ለአሕዛብ ሀብት ሆነ፤ ይሰቅሉት ዘንድ ዕራቁቱን አደረጉት፤ መብራት ልብስን ሊሸፈን አይገባውምና፤ ለሚፈልጉት ሁሉ ብርሃኑን ያሳይ ዘንድ በማብርያው ላይ ሊኖር ይገባዋል እንጂ፡፡ ወደ መስቀል ላይ አወጡት፤ መብራት በምድር ላይ ሊቀመጥ አይገባውምና፤ በብርሃኑ ለሚመላለሱ ያበራላቸው ዘንድ ወደ መቅረዙ ሊወጣ ይገባዋል እንጂ፡፡ እርሱ ራሱ በወንጌል ‹መብራት አብርተው በአልጋ ሥር አያደርጓትም፤ ወይም በዕንቅብ አይሸፍኗትም፤ ነገር ግን ለሁሉ ታበራ ዘንድ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጧታል[46]› እንዳለ፡፡

(፲፬)መቅረዝ የተባለውም መስቀል ነው፤ መብራት የተባለውም አማኑኤል ነው፤ እንግዲህ በወልደ እግዚአብሔር በብርሃኑ እንመላለስ፡፡ በእርሱ የሚያምን ሁሉም ወደ ብርሃን ይሔዳል፤‹ጨለማ አያገኘውምና›[47]፡፡ ስለዚህም ከነቢዩ ዳዊት ጋር አብሬ ወደ እርሱ እንዲህ እጮኻለሁ ‹በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን፤ በጽድቅህም ፊትህን እናያለን›[48]፡፡ ደግሞም ‹ኖን፣ ሕግህ ለእግሬ መብራት፤ለመንገዴም ብርሃን ነው[49]› እላለሁ፤ ዳግመኛም ከነቢዩ ከኢሳይያስ ጋር አብሬ ‹ትእዛዝህ በምድር ላይ ብርሃን ነው› እላለሁ[50]፡፡

[45] ዮሐ 18÷14
[46] ማቴ 5÷15
[47] ዮሐ 1÷5
[48] መዝ 35÷9፤10፤ መዝ 16÷15
[49] መዝ 118÷105
[50] ኢሳ 26÷9





(፲፭)እንግዲህ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ የፊትህን ብርሃን በላዬ ላይ አሳይ፤ እንደበቴንም ቅዱስ መስቀልህን ለማመስገን ክፈት፤ የነፍሴንም ቅጽር በመስቀልህ ስም እጠር፤ ሥጋዬንም ወደ መለኮታዊ ቅዱስ ሥጋህ አስጠጋ፡፡

አ፣ ታላቅ መታሰቢያ፤ አሁን እገልጥሃለሁ፤ መለኮትህን ከሥጋዊ ሟች ፍጥረታችን ጋር አንድ ያደረግክ አንተ ማነህ? ከማይሞተውና ከማይበ ሰብሰው መለኮትህም ጋር አንድ አደረግከው፡፡

(፲፮)በመስቀል ስም በሰው ልጅ አንደበት ሊነገር የማይችል ምሥጢር አለ፤

በመስቀል ስም የሰቃልያንን ማኅበር የሚበትን ምሥጢር አለ ፤

በመስቀል ስም የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጥ ምሥጢር አለ፤

ነፍሴን የሚቃወሟትንም ሁሉ ቀጥቅጥ፤ኃይላቸውንም አድክም በጠላቴ መውደቅም እኔ አገልጋይህ ፍሥሐ ክርስቶስ እንድደሰት አድርገኝ፤ ለዓለም ዓለም፤ አሜን፡፡

## ፬

(፲፯)አ፣ ከመስቀልህ ትዕቢተኛውን እንደ ተገደለ አድርገህ ያነሰቆልከው ሆይ፣ በአገልጋይህ በፍሥሐ ጽዮን ላይ ያደረችውን ኃጢአት ግደል፤

አ፣ በመስቀልህ ጨለማን የሻርከው ሆይ፣ ጠላቴን መታሰቢያው በዓለም ላይ እንዳይገኝ አድርገህ አጥፋው የኔም የአገልጋይህ ኑሮ በጸጥታና በጭምትነት ይሁን፤

አ፣ በመስቀል ተኩላውን የጣልኸው፣ በጉንም ከአፉ ያስጣልከው ሆይ፣ እኔን አገልጋ ይህን ፍሥሐ ጽዮንንም ከጠላቴ አፍ አስጥለኝ፤

አ፣ በመስቀልህ ሰውን ከሰማያዊው አባትህ ጋር ያስታረቅከው ሆይ፣ ለእኔም ከአንተ የሆነችውን ሰላም አታርቅብኝ፤

አ፣ ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ በመስቀልህ ምልክትን የሰጠሃቸው[51] ሆይ፣ በእኔም ላይ ለመልካም ምልክቱን አድርግ፣ አንተ አቤቱ እንደ ረዳኸኝና ደስ እንዳሰኘኸኝ አይተው ጠላቶቻችን እንዲያፍሩ[52]፤

አ፣ በመስቀልህ ኀያሉን እባብ ያደንከው ሆይ፣ በችንካሮችህ ብረትም አስወገድከው፤ በእኔ በአገልጋይህ ላይ ክፉ የሚወ ድዱትንም አጥፋቸው፤

አ፣ በመስቀልህ ቤልሖርን[53] የተዋጋኸው ሆይ፣ በላዩም ላይ ኃፍረትንም ወደ ራሱ መለስከ፣ የእኔ የአገልጋይህ የፍሥሐ ጽዮንንም ጠላቴን መከራን አልብሰው፤

አ፣ በመስቀልህ የትዕቢተኞችን ብርታት የሻርከ፣ የቅዱሳንንም ጸሎት ከፍ ከፍ ያደረግከ ሆይ፣ ታላቅነትን ከአንተ ዘንድ ስጠኝ፤

አ፣ በመስቀልህ ቤተ ክርስቲያንህን የባረከሃት፣ በስምህም የቀደስካት፣ ከጎንህ በወጣው ውኃም ያጠብካት ሆይ፣ እኔንም እጠበኝ፣ ከኃጢአቴም አንጻኝ፤ ከበደሌም አጥራኝ፤

አ፣ በመስቀልህ ሲኦልን የቀጠቀጥካት፣ ያጠፋሃታም ሆይ፣ በእኔ ላይ የሚነሣሡብኝን ምሽጋቸውን አፍርስ፤

አ፣ በመስቀልህ በቀኝ የተሰቀለውን ሽፍታ አንተን ወደ ማመን የመለስከው፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት አስቀድሞ መግባትንም የሰጠኸው ሆይ፣ እኔንም ወደ ቅዱሳን የደስታቸው አዳራሽ አግባኝ፤

አ፣ በመስቀልህ በጎችህን የሰቡ እንዲሆኑ ያደረግካቸው፣ በደምህም ነጠብጣብ ያተምካቸው ሆይ፣ ለእኔም ሕይወት ሰጭ የሆነውን መስቀልህን ስጠኝ፣ ያንተን ማኅተም ተሸክሜ በጠላት ላይ እበረታታበት ዘንድ፤

---

[51] መዝ 59÷4

[52] መዝ 85÷17

[53] ዕብራውያን ለሰይጣን ከሚሰጧቸው ስሞች አንዱ





አ፣ በመስቀልህ የእሳትን ጦር ከሱራፌል እጅ፣ የሚያስደነግጠውንም ሰይፍ ከሱራፌል እጅ ያስወገድህ፣ አዳምንም ወደ ወጣበት ወደ ገነት ዐጸድ ይገባ ዘንድ ያበቃኸው ሆይ፣ እኔንም ወደ ቅዱሳን ርስታቸው እንድገባ አብቃኝ፣እኔ አገል ጋይህ ነኝና፤

አ፣ በመስቀልህ የተበላሸውን ዓለም ያሳመርከው፣ የአረጀውንም ዓለም ያደስከው፣ ያደፈውንም ዓለም የቀደስከው ሆይ፣ የእኔንም ነፍሴንና ሥጋዬን አድስ፤

አ፣ በመስቀልህ በተቀደሰው ቀኝህ የተተከለችውን የወይንህን ተክል እንድ ታፈራ ያደረግካት፣ አማንያንንም እንድታፈራ ያበቃሃት ሆይ፣ እኔ ባርያህም የሃይማኖትን አበባ እንዳብብ፣ የንስሐንም ፍሬ እንዳፈራ አብቃኝ፤

አ፣ በመስቀልህ የሔዋንን ዕዳ የከፈልክላት፣ አዳምንም ከሞት ጣር ነጻ ያወጣኸው ሆይ፣ እኔን ባርያህን ከኃጢአት ቀንበር ነጻ አውጣኝ፣ በንጹሕ ልብ ለአንተ እገዛልህ ዘንድ፤

አ፣ በመስቀልህ ቅዱሳን ሐዋርያትህን የመራሐቸው ሆይ፣ እኔን ባርያህንም በእርስዋ እሔድ ዘንድ በቅን መንገድ ምራኝ፤

አ፣ በመስቀልህ (ሐዋርያትን) የጠላት ኃይሎችን ሁሉ እንዲያሳድዱ ያበቃሃቸው፣ የእፉኝቶችንና የጊንጦችንና መርዝም እንዲያረክሱ ሥልጣን የሰጠኻቸው ሆይ፣እኔም የሰማልያል ሰይጣንን መርዝ የማረክስበትን ኃይል ስጠኝ፤

አ፣ በመስቀልህ ምእመናንን ከኦሪት ሕግ የገዛኻቸው ሆይ፣ እኔንም በደምህ የተገዛሁ ከመሆን አትተወኝ፣ ነገር ግን እኔ ባርያህ በመስቀልህ እመካ ዘንድ በቅዱስ ወንጌልህ ቀንበር የተጠመድኩ አድርገኝ፤

አ፣ በመስቀልህ በሰይጣን ሠንሰለት የታሠሩትን የፈታሃቸው ሆይ፣ እኔ ባርያህ ልፈታበት ካልቻልኩት እሥራት የኃጢአት ማሠርያ ፍታኝ፤

አ፣ በመስቀልህ በጨለማ ውስጥ ለነበሩት ያበራህላቸው ሆይ፣ እኔ ባርያህ ምሉዕ በኩለሄ የሆነውን ፊትህን አይ ዘንድ ብርሃን መሎኮትህን አብራልኝ፤

አ፣ በመስቀልህ ድል ነሽዎቹ ሰማዕታትን ያበረታሃቸው፣ የእሳቱን ዋዕይም ያጠፋህላቸው፣ የአናብስትን ጥርሶችንም ያደነዝከላቸው፣ ከሚያስፈራ ቅጣትም የታደግካቸው ሆይ፣ እኔንም ከከፉ ዕለትና ከጥፋት ሰዓት አውጣኝ፤ እውነትህን በሰላም እናገር ዘንድ፤

አ፣ በመስቀልህ ምድርን የባረከሃት፣ በመስቀልህም ደም የረጨሃት፣ እኔንም ‹በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ፣ከጎንህ በሚወጣ ውኃም እጠበኝ እንደ በረዶ ነጭ እሆናለሁ[54]፤

አ፣ በመስቀልህ መካኒቱን ላንተና ለቤተ መቅደስህ የሚገዙ ወንዶችንና ሴቶችን ትወልድ ዘንድ መንታ ወላጅ ያደረግካት[55]፣ እኔንም ልዝብ ለሆነው ቀንበርህን እንድገዛ፣ ቀላል የሆነውን ሸክምህንም እንድሸከም አድርገኝ፤

አ፣ በመስቀልህ የዕብራውያን ሀገር በሆነው በኢየሩሳሌም የማዳንህን ኃይል ያሳየህ ሆይ፣ እነርሱ በመስቀልህ ፊት ‹ደሙ በእኛና በልጅ ልጆቻችን ላይ ይለፍ[56]› ብለው ጮኹ ዳግመኛም ‹አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እስኪ ከመስቀል ውረድ[57]› ብለው ተጣሩ፤

(፲፰)የመስቀልህን ኃይል አሳየህ፤ መስቀልህ ዕርቃንህን እንዳትመለከት ፀሐይን አጨለምካት፣ ቅዱሱ ሥጋህንም እንዳታይ ጨረቃን አደመንካት፣ አርዮብ[58]ም ከስድስት ሰዓት ጀምሮ ይወጣል፤ በስድስት ሰዓትም ራስህን ዘንበል አድርገህ ነፍስህንም ወደ አባትህ እጅ አሳልፈህ ሰጠህ፤ ምድርም ከመሠረቷ ተንቀጠቀጠች፤ ዋሻዎችም ተሰነጣጠቁ[59]፤ የከሃድያን ከፋታቸው

[54] መዝ 50÷9፤ 50÷7

[55] ማቴ 11÷30

[56] መዝ 27÷25

[57] መዝ 27÷40

[58] በዕብራይስጥ ‹ኦሬዎን›፣ በግሪክ ‹ከሲል› የሚሏቸው የተሰባ ሰቡ ከዋክብት፡፡ በሌላም በኩል አራቱ ዐበይት ከዋክብት ከሚባሉት አንዱም አርዮብ ነው፡፡ ‹ጽዱል ኮከብ፣ በጣም የሚያበራ› ኪ.ወክ፣ ገጽ 241

[59] ማቴ 24÷29፤27÷ 45-52፤ ዮሐ 19÷30





የሚሆነውም ድንጋይ ተሰነጠቀ፤ ነገር ግን የሰቃልያኑ ልብ አልተንቀጠቀጠም፤ ጸና እንጂ፡፡ ልባቸው ደነደነ፤ የአንገታቸውም ጅማት እንደ ብረት ሆነ፤ ገጻቸውም እንደ ነሐስ ሆነ፤ ዐለቱ ተሰነጠቀ፤ መቃብራትም ተከፈቱ፡፡ ነገር ግን የልባቸው ሰሌዳ በጨለማ መሸፈኛ ተሸፈነ፡፡ ፀሐይም ጌታውን ዐወቀ፤ጨረቃም አምላኩን ዐወቀ፤ ከዋክብትም ፈጣሪያቸውን ዐወቁ፤ ዕርቃን ስውነትህን እንዳያሳዩ ብርሃናቸውን ከልክለዋልና፡፡ ዋሻዎችም ሠሪያቸውን ዐወቁ፤ ሞትን ከመፍራት የተነሣም ተሰነጣጠቁ፤ ምድርም የመሠረታትን ዐወቀች፤ ከመስቀልህ ኃይል የተነሣም ተንቀጠቀጠች፤ ዐለትም ያጸናው ማን እንደ ሆነ ዐወቀ፤ ከደምህ መንጠብም የተነሣ ተሰነጠቀ፤

(፲፱)የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ እነዚህ ሁሉም አንተ እንደ ፈጠርካቸው ዐወቁ፤ እሥራኤል ግን አላወቁህም፡፡ ሕዝቤም አልተረዱህም፡፡ ስለ መልካ ምም ፋንታ ክፉን መለሱልህ፤ ስለማፍቀርህም ጠሉህ[60]፤ የፀሐይ ዋዕይ እንዳ ያቃጥላቸው የደመና ዓምድ የጋረድከላቸውን የእሾህ አክሊል ደፍተው ተሳለቁብህ፤ በጸዳሉ ከልሎ በሌሊት የመራቸው የብርሃን ዓምድ፣ ፊትህን ሸፍነው እየተሳለቁ «ክርስቶስ ሆይ የመታህ ማን እንደሆነ ትንቢት ተናገር»[61] ስለ ማለታቸው ይወቅሳቸዋል፡፡

(፳)የኮሬብ ዐለት የምልክት ውኃ[62] ሐሞትና ከርቤን ስላጠጡህ[63] ይወቅሳቸዋል፤

በምድረ በዳ የመገብካቸው መና[64]፣ አንተ በብረት ችንካር ተቸንከረህ በመስቀል እያለህ በደስታ ለመመገብ ስላዘጋጁት ማዕድ ይወቅሳቸዋል፤

በባሕሩ መካከል መንገድን ያገኙ ዘንድ በዓምደ እሳት የተከፈለላቸው ባሕር[65] ልብስህን ስለቀደዱትና ስለ ተካፈሉት[66] ይወቅሳቸዋል፤

[60] መዝ 108÷ 5

[61] ማቴ 26÷68፤ ሉቃ 22÷64

[62] ዘጸ 17÷6-7

[63] ማቴ 27÷48፤፤ መዝ 68÷21

[64] ዘጸ 16

በምድረ በዳ እባቡ ሲነድፋቸው እርሱን በመመልከት ይድኑ ዘንድ በአንተ ትእዛዝ ሙሴ የሠራላቸው የነሐሱ እባብ[67] በያዕቆብ ልጆች እጅ በኢየሩሳሌም አንተን ስለ መስቀላቸው ይወቅሳቸዋል፤

(፳፩)ከእነርሱ ዘንድ የትንቢት ኃይል ተሻረ፤ ከዚያም በኋላ ከእሥራኤል ነቢይ አልተነሣም፤ የትንቢት ቃሉንም በኢየሩሳሌምና በአውራጃዎቿ አላሰማም፤ ቀያፋም እየተቆጣ ልብሱን ቀደደ፤ ከሌዋውያንም ቅብዐ ክህነት ቀረ፤ ስለ እነርሱ በኦሪት እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለና ‹ልብሳቸውን አይቅደዱ፣ ሰውነታቸውንም አይብጡ፣ እነርሱ ለእግዚአብሔር የተለዩ ናቸውና፤›[68]:: ነገር ግን ስለ ቀያፋ ቅድስናቸው ከእነርሱ ተወገደ፤ የምኩራብ መጋረጃም ተቀደደ[69]፤ ስለዚህ የሚፈልጉት (መሲሕ) የለም፤ ሊቃነ ካህናትና ጸሐፍቶቻቸውም ለሕዝቡ «ከቄሣር በቀር ንጉሥ የለንም[70]» «ራሱን ንጉሥ አድርጎ የሚቆጥርም ሁሉ በንጉሥ (ቄሣር) ያመፀ ነው»[71] አሉ:: ስለዚህም እርሱ (ቀያፋ) ስለእነርሱ ሆኖ የሮምን መንግሥት ዕውቅና ሰጠላቸው፤ የዳዊትንም ልጅ ካደ፤ ያን ጊዜም የአይሁድ መንግሥት ከኢየሩሳሌም አለፈ:: ለያዕቆብ የተሰጠውን የመንግሥት፣ የክህነትና የትንቢት ጸጋም ለአሕዛብ ሰጧቸው:: አሕዛብም ሀብትን ከክርስቶስ ጋር ከእሥራኤል ተቀበሉ::

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ግን አንተ በህላዌህ የእግዚአብሔር ልጅ፣ በሥጋህም የዳዊት ልጅ እንደሆንክ አመንንብህ፤ እስከ መጨረሻውም ለእኛ ትነግሥልን ዘንድ ወደድን በእነርሱ ዘንድ

---

[65] ዘጸ 14÷15-31
[66] ሉቃ 23÷35፤ መዝ 21÷18
[67] ዘኁ 21÷8፤ ዮሐ 3÷13
[68] ዘሌዋ 21÷10
[69] ሉቃ 23÷46
[70] ዮሐ 19÷15
[71] ዮሐ 19÷12





መናቅህ ለእኛ ክብር ሆነን መጽሐፍ «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ይሆናል» እንዲል[72] ይህቺም ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች::

(፳፪)አንተን የምንፈልግህ ለመንገሥ ብቻ አይደለም፤ ፈጽመን እናመልክሃለን እንጂ:: አንተ በመለኮትህ ከአብ ጋር ትክክል እንደሆንክ፣ በክብርም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ መሆንህን እናምናለንና በአንተና በእነርሱም መካከል (በህልውና) አንዲትም ሰዓት ልዩነት የለም:: በአንተና በአብ መካከልም (በህልውና) የዕለት ልዩነት የለም:: ለአብ በህላዌ ከአንተ መቅደም የለውም፤ ያንተም ህላዌ ከመንፈስ ቅዱስ አይቀድምም::

(፳፫)ህላዌህን በሰው ልጅ ኅሊና ከመመርመር፤ በመላእክትም ልቡና ከመታወቅ ሠወርከው:: ህላዌህንም በሰዎች ልጆች እጅ ከመዳሰስ፣ በትጉሃን መላእክትም እጅ ከመነካት ከፍ አደረግከው:: አንተ ከፈቀድክለት በቀር ሌላ በማንም እንዳይታይ ሕላዌህን በአርያም ከመታየት ሠወርከው::

(፳፬)እንግዲህ ራሱን እንኳን ከሞት ማዳን የማይቻለው፣ ሟች ሰው የሆነ ሊቀ ካህናት አንፈልግም፤ አብ ስለ አንተ በዮርዳኖስ ‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት›[73] ብሎ የመሰከረልህ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

(፳፭)ነፍስህን ሰጥተህ በገችህን የተቤዠህ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

ከኃጢአት ንጹሐ የሆንክ ከሰማያትም በላይ ከፍ ከፍ ያልክ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

ለአባትህ ራስህን መሥዋዕት አድርገህ በመስቀል ላይ ያቀረብክ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

አንተው ሠዋ፣ አንተውም መሥዋዕት የሆንክ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

አጣኙም ዕጣኑም የሆንክ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

---

[72] መዝ 117÷22
[73] ሉቃ 3÷22፤9÷35

መንፈስ ቅዱስን ከአብ ዘንድ የተቀባህ፣ የሕዝቡንም ኃጢአት ታስተሠርይ ዘንድ ራስህን መሥዋዕት አድርገህ ያቀረብክ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤[74]

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ራስህን እስከ ለዓለመ ዓለም የዘወትር መሥዋዕት ያደረግክ ሊቀ ካህናታችን አንተ ነህ፤

(፳፮)እንደዚህ አድርገን የክህነትህን አርዌ ብርት[75] ከፍ ከፍ እናደርጋለን፤ በእርሱ ላይ ሥጋህ ለተሠዋበት መስቀልህም ‹መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው› እያልን እንሰግዳለን፡፡ ጌታችን ሆይ በመስቀልህ ፊት እንሰግዳለን፤ ለእጅህና ለእግርህ ችንካሮችም እንንበረከካለን፡፡ ለተወጋውም ጎንህ እምኃ እናቀርባለን፤ ለወጉህ እሾሆችም ምስጋናና ውዳሴ እናቀርባለን፤ ትንሣኤህን እንና ገራለን፣ በሥርዓትህም እንታመናለን፡፡ በአብ ቀኝ በመቀመጥህም ‹ለእኛ በእግዚአብሔር ዘንድ በሰማያት አባት አለን፤ እርሱም በአባቱ ቀኝ የተቀ መጠ አማኑኤል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እርሱም ዳግመኛ በሰማይ ደመና ከኃይልና ከመላእክቱ ጋር፣ መስቀሉንም ከፊቱ አድርጎ ይመጣል፤ ያን ጊዜም የወጉህ ያለቅሳሉ፤ የስምህን ማኅተም ላገኙት ግን የእግዚአብሔር ሰላምና ምሕረት ይሆንላቸዋል›[76] እያልን እንመካለን፡፡

(፳፯)እንግዲህ ዕዳችንን በመስቀል ላይ የከፈልክልን፣ በሞትህም በእኛና በአባትህ መካከል ምሕረትን ያደረግክ፤ በትንሣኤህም መንግሥተ ሰማያትን የከፈልከን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እናወድስሃለን፡፡ በደምህ ነጠብጣብ ምሕ ረትህ በመስቀልህ ሰሌዳ ተጻፈ፤ በጎንህ መወጋት በወጣው ደምና ውኃም

[74] አባ ጊዮርጊስ ይህንን የሚለው በመዝ 44÷7 ያለውን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መቀባትን በተዋሕዶ ነው የሚተረጉሙት፡፡ የሥጋ ከመለ ኮት ጋር ተዋሕዶ አምላክ መሆኑ ነው ሹመቱ፡፡ መለኮት በሥጋ ሲዋረድ፣ ሥጋ በመለ ኮት ከብሯልና፡፡ ይህን ተዋሕዶ ያከናወነው መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ‹ቀባዕ› ተብሏል፡፡ አከናዋኝ ሲል ነው፡፡ የመዝሙረ ዳዊት ትርጓሜም ‹እንዳንተ ያሉ ነቢያት ካህናት ከተቀ ቡት ልዩ የሚሆን ቅብዐ ትፍሥሕትን ማለት ልዩ ተዋሕዶን አዋሐድህ› ሲል ነው ይላል፡፡ (መዝሙረ ዳዊት ትርጓሜ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ፣ 1982 ዓም፣ ገጽ 241)

[75] ጳጳሳት ስለ ክህነታቸው የእባብ ምልክት ያለበት(አርዌ ብርት) ይይዛሉ፡፡ ይኼም ወደ ዕባብነት የተለወጠችው የሙሴ በትር ምሳሌ ነው፡፡

[76] ራእይ 3÷12፤7÷4



ውዳሴ መስቀል ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

የወጋህ ጭፍራ አመነ፡፡ ፈያታዊ ዘየማንን የነካው የመስቀልህ ጥላ ወደ እምነት መለሰው፡፡ ፈያታዊ ዘየማን በመስቀልህ ሕማማት እንደ ተሳተፈ ሁሉ በመንግሥተ ሰማያትም ካንተ ተሳተፈ፡፡ አንተ ‹ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆን ዘንድ አብልጠህ እመን[77]› አልከው፤ የምሕረትህ ጎዳና ያልነካው አንደኛው ሽፍታ ግን ‹አንተስ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ አንተንም እኛንም አድን› ብሎ የሰደበህን ሌላኛው እንዲህ ሲል ገሠጸው ‹እኛስ የሚገባንን አግኝተናል፤ በኃጢአታችንም ተከፍሎናል፤ ይህ ግን ምንም የሠራው ክፉ ነገር የለም፡፡ ወደ አንተም ፊቱን መልሶ ‹አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ በምሕረትህ አስበኝ[78]› አለህ፡፡ የምሕረትህ ሰንሠለት ፈያታዊ ዘየማንን ሳበችው፤ ሁለቱ ንም ያገኛቸው የመስቀል መከራ አንድ ዓይነት ነው፤ በአንድ ዓይነት ኃጢአ ትም ተፈረደባቸው፤ እነርሱስ የተሰቀሉት ስለ በደላቸው እንጂ ስለ አንተ አልነበረም፤ በግራ የተሰቀለው ሽፍታ ከአንደበቱ በወጣው የስድብ ቃል ምክ ንያት ጠፋ፤ በቀኝ የተሰቀለውም ሽፍታ ከአፉ በወጣው የልመና ቃል ምክ ንያት ዳነ፤ ‹ከቃልህ የተነሣ ይፈረድልሃል፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃል[79]› ያለው የወንጌል ቃል ተፈጸመ፡፡

(፳፰)ጌታዬ አምላኬ፣መድኃኒቴም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ «አቤቱ ከቅዱሱና ከታተ መው (በደምህ) መስቀል በቀኝ የተሰቀለውን ሽፍታ እንዳሰብከው ሁሉ እኔንም በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ በቸርነትህ አስበኝ» እያልኩ እኔም ወደ አንተ እጣራለሁ፡፡

(፳፱)አቤቱ ቀራጩ ማቴዎስን እንዳሰብከው[80] ዕድል ፈንታውንም ከቅዱሳን ሐዋርያት ጋር እንዳደረግከው ሁሉ እኔንም አስበኝ፡፡

አቤቱ አሳዳጅ የነበረውን ጳውሎስን እንዳሰብከው እኔንም አስበኝ[81]፤ (እርሱን) አሕዛብን የሚጠራ፣ የመንግሥትን ወንጌል የሚሰብክ እንዳደረ

[77] ሉቃ 23÷43

[78] ሉቃ 23÷39-42

[79] ሉቃ 23÷39-42

[80] ማቴ 9÷9

[81] የሐዋ 9

ግከው፣ የሰሙትም ሁሉ ስለ እርሱ እንዲህ እያሉ ያደንቁ ነበር። ‹ይህስ አስቀ ድሞ ያሳድድ የነበረውን ሃይማኖት አሁን ይሰብከዋል› ለእርሱ ስለ ተሰጠ ውም ጸጋ እግዚአብሔርን ያመሰግኑት[82] ነበር።

አቤቱ ሽቱ የቀባችህን፣ እግርህንም በዕንባዋ ያራሰችውን፣ በፀጉርዋም ያበሰ ችውን ዘማ እንዳሰብካት እኔንም አስበኝ፤ ‹እምነትሽ አድኖሻል፣ ኃጢአትሽም ሁሉ ተሠርዮልሻል› እንዳልካትም[83] እኔንም ‹እምነትህ አድኖሃል› በለኝ፤ እኔን ባርያህን ፍሥሐ ክርስቶስንም ለአባትህ መንግሥት የበቃሁ አድርገኝ ለዓለመ ዓለም፣ አሜን።

## ፲

(፩)አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምሕረትህን ስለ እኔ አድርግ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምሕረትህን በላዬ ላይ ጨምር፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በመስቀልህ አጥር ከበበኝ፣ በመድኃኒትህም ጋሻ ከልለኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የሰውነቴን አጥር ጠላትን አሸናፊ በሆነው መስቀልህ ከበብ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በትጉሃን አእላፍ መላእክትህ መግበኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የመስቀልህን መሣርያ አስታጥቀኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ በቅዱሳን አንደበት አንተ የሚጣፍጥ ስም ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በእውነት ለሚጠሩህ አንተ የሚጣፍጥ እሳቤ ነህ፤

[82] ገላ 1÷23
[83] ዮሐ 11÷2፤12÷3





አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ አንተ መንፈስ ኮከባቸው ለደበዘዘባቸው መመኪያ የሆንክ የአጥቢያ ኮከብ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ በቅዱሳን ገጽ ላይ ዘወትር የሚያበራ የጽድቅ ፀሐይ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ከቤተ ያዕቆብ የወጣ የዘይት ዛፍ፣ ከእሴይ ሥር የወጣ የሃይማኖት በትር፣ ከዳዊት ግንድ የበቀለችም አበባ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ከቁጣው የተነሣ የጨለማ አበጋዞች የደነገጡለት፣ ከግሣቱም የተነሣ የምድር ተራሮች የተንቀጠቀጡለት ከይሁዳ ነገድ የተገኘ አሸናፊ አንበሳ ነህ[84]፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ በመስቀልህ ቀስት የሚታገለንን ውጋው፣ ከችንካሮቹም ብረት እርሱን የምት ወጋበት የጋለ ጦር ሥራ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ የማዳንህን ኃይል በእኔ ላይ ግለጥ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ የብርሃንህን ገጽ በላዬ ላይ ሹም፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ሞገስ መስቀልህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ከእኔ ጋር ይኑር፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ አንደበቴን በመለኮትህ ጨውነት አጣፍጥ፣ የመስቀልህን ውዳሴ እናገር ዘንድ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣በአንደበቴ ምስጋናህን ምላ፣ አኮቴትህን አመሰግን ዘንድ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ እግሮቼን በመንገድህ አጽና፣ የእግሮ ችህን የጽድቅ ፈለግ እከተል ዘንድ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ፈቃድህን ለመፈጸም አጽናኝ፤

[84] ራእይ 5÷5

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ አንተን መፍራትን በሰውነቴ አሳድር፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ምሕረትህን በራሴ ላይ አድርግ፣ በገጼም ላይ የምሕረትህ ዘይት ይፍሰስ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ሰማያዊ ምሥጢርህን ለመቀበል የተዘጋጀሁ አድርገኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ በመለኮታዊ ማዕድህ እንድቀመጥ አድርገኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ በቅዱሳንህ ደስ እንዳለህ ሁሉ በእኔም ደስ ይበልህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ስፍገመገም ደግፈኝ፣ ከውድቀትም አንሣኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ከችግር አድነኝ፣ መከራዬንና ሕማሜንም ተመልከት፣ ኃጢአቴንም ይቅር በል፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ከጠላቶቼና ከሚያሳድዱኝ ታደገኝ[85]፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣በአገልጋይህ ላይ ፊትህን አብራ፣ አቤቱ አልፈር፣ ጠርቼሃለሁና[86]፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ መስቀልህ በምውልበት ቦታና በማድር በትም ሥፍራ ሁሉ ጠባቂ ይሁነኝ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ከሕፃንነቴ ጀምረህ ተስፋዬ አንተ ነህ፤[87]

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ከእናቴ ማኅፀን ጀምረህ አንተ አምላኬ ነህ[88]፣ በማኅፀንም አንተ ሠወርከኝ፣ በሁሉም ጊዜ አንተ እሳቤዬ ነህ[89]፤

[85] መዝ 30÷16፤31÷15
[86] ሉቃ 9÷26፤
[87] መዝ 70÷5





አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ የመድኃኒቴ ቀንድ አንተ ነህ[90]፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ የእራሴ አክሊል አንተ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ለአፌ ጣፋጭ የሆንክ የሕይወት እንጀራ አንተ ነህ[91]፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ለጉሮሮዬ መልካም የሆንክ የመድኃኒት ጽዋዕ አንተ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ያልተሸመነ ጨርቅ፣ ያልተፈተለም ልብስ አንተ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ እጥፍ የሆንክ ወርቅ፣ የተገኘህም ዕንቁ[92] አንተ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ የበዛ ምናን፣ የተተረፈም መክሊት አንተ ነህ[93]፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ስለ አዳምና ስለ ልጆቹ ስትል መከራን የተሸከምክ አንተ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ በሔዋንና በልጆቿ ስሕተት ምክንያት የመስቀልን ሕማማት የተሸከምክ አንተ ነህ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ስለ ሰው ልጆች በደል ስትል የመስቀልን ችንካሮች የተቀበልክ አንተ ነህ፤

[88] መዝ 21÷11
[89] መዝ 70÷6
[90] ሉቃ 1÷69
[91] ዮሐ 6÷35
[92] ማቴ 13÷45
[93] ማቴ 25÷15፤ ሉቃ 19÷11-25

የመስቀልን ሕማማት ስለ ኃጢአታችን ስትል የተቀበልክ ሆይ፣ ጸሎቴን እንደ ዕጣን በፊትህ ተቀበል[94]፤

ስለ በደሌ ስትል የመስቀልን መከራዎች የታገሥክ ሆይ፣ በዕቅፍህ የምትኖር ትዕግሥትን አድለኝ፣ በመስቀል ቀንበር የተጠመድኩ እሆን ዘንድም አብቃኝ፤

(፴፩)በዐመፃና በኃይል በላዬ ላይ የተነሡ በመስቀልህ ኃይል ይሸሹ፣ ከመስ ቀልህም ፊት ይጥፉ፣ በውጭ ባለ የቅጠል ድምፅ እስኪደነግጡ የሴቶችን ፍር ሃት ስደድባቸው፤ ልጆቻቸውን ሰይፍ መከራ ያምጣባቸው፣ በቤቶቻቸውም ውስጥ ድንጋጤ ይሁን፤ ለእኔ ግን በዘመናትና በዕለታት ሁሉ ከአንተ ዘንድ ደኅንነትና ሰላም ይሁን፤

(፴፪)አቤቱ ጌታዬ ሆይ ኃይልህን አንሣ፣መጥተህም አድነን፣ የኃያላን አምላክ ሆይ መልሰን፣ እንድንም ዘንድ ፊትህን በላያችን ላይ አብራ[95]፤ ጌታዬ ሆይ በመስቀልህ ወደ ወደድከው መንገዶች ሁሉ መሪ ሁነን፤ ረዳቴና መሸሸጊያዬ ሁነኝ[96]፤ ኃይሌና መጠጊያዬ፣ ብርታቴና የነፍሴም መድኃኒት አንተ ነህና[97] በቀን ከእኔ ጋር፣ ሌሊትም በመካከሌ ሁን፣ በጊዜውና በዕለቱም ሁሉ አትተወኝ

(፴፫)አቤቱ ከአርአያም መውረድህን፣ በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በቅድ ስት ንጽሕት ማርያም ማኅፀንም ማደርህን፣ ከእርሷ መወለድህን፣ ጡቶቿንም ጠብተህ ማደግህን አስብ፡፡ ይህንንም አስበህ የእኔን የአገልጋይህን የፍሥሐ ክርስቶስን ኃጢአት ይቅር በለኝ፤

አቤቱ በየጥቂቱ የሆነውን እድገትህን፣ በንጽሕና የሆነውን ወጣትነትህንም አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

[94] መዝ 140÷2
[95] መዝ 79÷3-4፤ መዝ 80÷2-3
[96] መዝ 26÷9
[97] መዝ 17÷3፤ መዝ 18÷2፤ መዝ 30÷4፤ መዝ 31÷3





አቤቱ በባሕር መካከል ዕርቃንህን ተገልጠህ በዮሐንስ እጅ የተደረገውን ጥምቀትህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ የእኔን ኃጢአት ይቅር በለኝ፤

አቤቱ መንገድ በመጓዝ መንገላታትህን፣ በበረሐም እስኪርብህ ድረስ ዐርባ ቀንና ሌሊት በጾምክ ጊዜ ከዲያብሎስ ዘንድ መፈተንህን አስብ፤ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

አቤቱ በተያዝክባት ሌሊት ለሐዋርያት የሰጠሃቸውን ሥጋህንና ደምህን አስብ፣ አልካቸውም ሕንኩ ብሉ፣ ይህ ሥጋዬ ነው፤ ይህንንም ጽዋ ጠጡ፣ እርሱ ደሜ ነው በመንግሥተ ሰማያት ከአባቴ ዘንድ አዲሱን የወይን ጠጅ እስክጠጣ ድረስ ከእርሱ አልጠጣም[98]፣ ይህንን አስበህ የእኔን ኃጢአት ይቅር በል፤

አቤቱ በሊቀ ካህናቱ ባሮች መያዝህን፣ በቀያፋ አደባባይም በጥፊ መመታ ትህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በል፤

አቤቱ በቀያፋ አደባባይ መቆምህን፣ በአደባባይ ባሉትም መሰደብህን አስብ፤ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

አቤቱ በሰንሰለት በትር መመታትህን፣ በብረት ጅራፍም መገረፍህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

አቤቱ በእንጨት ላይ መሰቀልህን፣ በችንካርም መቸንከርህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በል፤

አቤቱ ሐሞትን ከመጣጣ ጋር ቀላቅለው ያጠጡህን፣ ነፍስህንም ለሞት መስጠትህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ የእኔን ኃጢአት ይቅር በለኝ፤

አቤቱ በሐር ልብስ መገነዝህን፣ በመቃብርም መግባትህን፣ በዚያም ሦስት ቀንና ሌሊት ያለ ነፍስ እንቅስቃሴ መቆየትህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

[98] ማቴ 26÷27-29

አቤቱ በሦስተኛው ቀን መነሣትህን፣ በሩ በተዘጋ አዳራሽ ለነበሩት ሐዋርያ ትህም መገለጥክን አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

አቤቱ ወደ ሰማያት ማረግህን፣ በአብም ቀኝ መቀመጥህን አስብ፣ ይህንንም አስበህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤

(፴፭)በዳግም ምጽአትህ ከብሩካን በጎችህ አንዱ አድርገኝ፣ በቅዱሳን ሀገርም ዕድል ፈንታዬን አድርገው፤ አቤቱ ሥጋን የለበስከው ለማዳን አይደለምን? የሚጠፋውንም ሥጋ የማይጠፋ አደረግከው፤

እኔማ የምጠፋ ከሆን አቤቱ ለምን ምድራዊ ሥጋን ለበስከ?

እኔማ ከተፈረደብኝ አንተ በምድር ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወራትን ለምን ተመላለስክ? ለምንስ ከኃጢአት ብቻ በቀር እንደ ሰው ልጆች በምድር ላይ መከራን ተቀበልክ?

አቤቱ እኔ ከተኮነንኩማ እጅህ እንደ ሌባ ለምን ታሠረ? ጉንጭህስ እንደ ከፉ ለምን በጥፊ ተመታ?

አቤቱ እኔ ከተፈረደብኝ የምሰቃይም ከሆነማ አንተ ለምን እንደ እንስሳ ራስህን ተመታህ? እንደ ሕግ አፍራሽስ ጀርባህ ለምን ተገረፈ?

አቤቱ እኔማ የማልድን ከሆነ፣ አንተ ኃፍረተ መስቀልን፣ የርኩሳንን ምራቅና የከሐድያንንም ስድብን ለምን ታገሥክ?

(፴፮)አቤቱ በአንዳች ምክንያት ይህንን ፍርድ አታድርግ፤ በደምህ ከመገዛ ትም የወጣሁ አታድርገኝ፤ አቤቱ እኔ ከዳንኩስ ለአንተ የንግድህ ትርፍ እሆናለሁ፤ እኔ ሕያው ከሆንኩ አቤቱ የስቅለትህ ትርፍ እሆናለሁ፤ እኔ ከጸደ ቅኩስ አቤቱ የሕማማትህ ትርፍ እሆናለሁ፤አቤቱ ‹ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነም ይፈረድ በታል[99]› ያልከውን አስብ፤

[99] ማር16÷16





(፴፯)አቤቱ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር፣የአምላክ ልጅ አምላክ፣ የብርሃን ልጅ ብርሃን፣ የንጹሕ ልጅ ንጹሕ እንደሆንክ አመንኩብህ፤ ከጎንህ በፈሰሰው በማየ ገቦም ተጠመቅኩ፡፡ ስለዚህም ኩነኔ የተገባኝ አይደለሁም፤ ኃጢአትንማ ከተቆጣጠርክ በፊትህ ማን ሊቆም ይችላል? አንተ ‹የሚያምን ብኝ ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው[100]› ብለሃልና፤ ስለማይታበለው ቃልህ ተለመነኝ፤ ኃጢአት የሌለብህ አንተ ብቻ ነህና፣ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤ በደል የሌለብህ አንተ ብቻ ነህና፣ በደሌን አታስብብኝ፤

(፴፰)እኔ ቅዱስ መስቀልህን በማመን ታምኛለሁና፣መስቀልህን ማወደስ ለአን ደበቴና ለከንፈሮቼ ደስታን ይሰጣቸዋል፤ እኔን ገብረ መስቀልን በመስቀልህ ኃይል እንደ መልካም ጋሻ ከልለኝ[101]፤

(፴፱)አቤቱ ወደ አንተ ዓይኖቼን አነሣለሁ[102]፣ እጆቼን ዘረጋሁ፣ የኅሊናዬንም ራስ አነሣሁ፤ወደ አንተም እንዲህ እያልኩ ተጣራሁ ‹በሕያዋን ምድር ተስፋዬ አንተ ነህ፣ ዕድል ፋንታዬም አንተ ነህ[103]፤ እጅግ ታምሜያለሁና[104] ወደ እኔ ተመልከት፤ የኃያላን አምላክ ሆይ ብበድልህም አንተ እስከ መቼውም አትተ ወኝ፤ ጆሮህንም ወደ ልመናዬ አዘንብል[105]፤ ጸሎቴም በፊትህ ወደ መቅደስህ አዳራሽ ትድረስ[106]፤ ተለመነኝ፣ ልቡናዬ የሚልህንም ስማኝ፤ አቤቱ ፊትህን እሻለሁ፤ አቤቱ ፊትህን ከእኔ አትመልስ፤ ረዳቴም ሁነኝ፣ አትተወኝም[107]፤

(፵)አቤቱ አንተ ግን ለዘለዓለም ትኖራለህ፤ መታሰቢያህም ለልጅ ልጅ ነው[108]፤ አቤቱ አንተ አስቀድመህ ምድርን መሠረትክ፤ ሰማያትም የእጅህ

[100] ዮሐ 3÷16
[101] መዝ 5÷13
[102] መዝ 24÷1፤መዝ122÷1
[103] መዝ 15÷5
[104] መዝ 141÷7፤ መዝ 142÷6
[105] መዝ 87÷3፤ መዝ 88÷2
[106] መዝ 118÷170
[107] መዝ 26÷7-9
[108] መዝ 15÷5

ሥራዎች ናቸው፤ እነርሱ ይጠፋሉ፣ አንተ ግን ትኖራለህ፤ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጋረጃም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጣሉም[109]፤ አንተ ግን ለቅድምናህ መጀመርያ፣ ለኋለኛነትህም መጨረሻ የለህም፤

አንተ ከተሠወሩት ሁሉ የተሠወርክ ነህ፤ እንደ ወደድከም ራስህን ለመሬ ታውያን ገለጥክ፤

(፷፩)አንተ በበሰማያት በአባትህ ቀኝ ተቀምጠህ እያለህ፣ በታች በጲላጦስ አደባባይ ቆምክ፤

በአርአያም የእሳት መጋረጃዎች የሚሠውሩህ፣ በምድር ላይ ከሐድያን ዕራቁ ትህን ገለጡት፤

በላይ ማኅበረ መላእክት የሚያመሰግኑህን፣ በቀራንዮ ግን ማኅበረ አይሁድ ይሰድቡሃል፤

በላይ በሰማያት በኪሩቤል ክንፍ የምትከለለው፣ በኢየሩሳሌም ግን የእሾህ አክሊል ተቀዳጀህ፤

በጌርጌላ በእሳት ሠረገላ ላይ የምትቀመጠው፣ በሊቶስጥሮስ ግን በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀልክ፤ መስቀልህም በደምህ ነጠብጣብ ተቀባ፤

## ፬

(፷፪)በአምላኩ ደም የተቀደሰ፣ ከፈጣሪው ጎን በወጣ ውኃም የተጠመቀ ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

ለገነት ዛፎች አክሊል፣ ለገዳም ዛፎችም ክብር የሆናቸው ዕፅ እንዴት ያለ ነው !

ለአሽናፊ የእግዚአብሔር በግ መሠዊያ የሆነው ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

[109] መዝ 101÷26-27





ለእሥራኤል አምላክ የፋሲካው መሠዊያ የሆነ ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

የጎልጎታዊው የምሥጢር ወይን መፍለቂያ የሆነ ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

ከእርሱ ምእመናንን ለማተም የሚሆን የሕግና የሥርዓት ደምን ያንጠባጠበ ዕፅ ምን ዓይነት ነው!

ብሩካን በጎችን ለማጠቢያ የሚሆን ምንጭን ያወጣ ዕፅ ምን ዓይነት ነው!

ምድርን የቀደሳት፣ሰማይንም ያማተበበት፣ዓለምንም ሁሉ በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በረከት የባረከ ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

ሰማያውያንን ከምድራውያን ያስተባበራቸው ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

አዳምን ከስሕተት ያዳነው፣ ሔዋንንም ከሞት ጻዕረኛነት ነጻ ያወጣት ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

ስለ እርሱ (አስቀድሞ) በኦሪትና በነቢያት የተነገረ፣ በሐዋርያትም በገሐድ የተሰበከ ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

የተከሉትን የበተናቸው፣ ያመኑትንም የሰበሰባቸው ዕፅ እንዴት ያለ ነው!

ቤተ ክርስቲያንን በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ላይ የመሠረታት ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

እልሜውን ያጣፈጠ፣ ርኩሱንም ያነጻ ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

ድኻውን ከፍ ከፍ ያደረገ፣ በደለኛውንም ያጸደቀ ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

ደካማን ያበረታ፣ ሕመምተኛውንም ያዳነ ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

ጥቂቱን ያበዛ፣ ሰነፉንም ጥበበኛ ያደረገ ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

መካኗን ወላድ ያደረገ፣ ጨለማውንም ያበራ ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

የዓለም ሁሉ መመኪያ የሆነ ዕፅ እንደምን ያለ ነው!

(፶፫)ልባችንን አንቅተን፣ ዓይኖቻችንንም ገልጠን፣ ከንፈሮቻችንንም ደስ አሰኝተን የመስቀልን ምስጋና ከፍ ከፍ እናደርጋለን፤ አቤቱ ጌታዬ ሆይ የመስቀልህ ምስጋና የተኙትን አንቅቶ ከትጉሃን ማኅበር ጋር አንድ ሆነው እንዲያመሰግኑ ያደርጋቸዋል፤

(፶፬)የመስቀልህ ምስጋና በሁሉም የመላ፤ ለልቡናም እጅግ የሚደንቅ ነው፤ የመስቀልህ ምስጋና ለሚያነበው የሚጥም፣ለሚሰሙትም የሚያስደምም ነው፤

የመስቀልህ ምስጋና ለሚያምንብህ መሰንቆው፣ ለሚክድህም ተግሣጹ ነው፤

የመስቀልህ ምስጋና ለሚያፈቅርህ እንዚራው፣ ለሚጠላህ ግን ስድቡ ነው፤

የመስቀልህ ምስጋና የከረመ ወይን እንደጠጣ ሁሉ ልብን ደስ ያሰኘዋል፤ነገረ መስቀልህ በሰነፎች ዘንድ ስድብ፣ በጠቢባን ዘንድ ግን ትምክህት ነው፤ ጳውሎስ ‹የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው[110]› እንዳለ፤

(፶፭)የመስቀልህ ምስጋና ያበራልናል፤ የእሥራኤልን ልጆች ከሲይር በረሐ እስከ ቃዴስ ምድረ በዳ እንዳበራላቸው ዓምደ እሳት[111] መሪ ይሁነን፤ እንግዲህስ የበረታች ቀኝህ፣ ከፍ ከፍ ያለችም ከንድህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ትምራኝ፤

ጠቢበ ጠቢባን ሆይ ዓይኖቼን ክፈት፣ ድንቅ ነገሮችን ከሕግህ ውስጥ አይ ዘንድ፤ እኔ በምድር ላይ ሁሉ ስደተኛ[112]፤እንደ አባቶቼም መጻተኛ ነኝና[113]፤ ወደማልመለስበት ከመሔዴ በፊት አሳርፈኝ[114]፤

(፶፮)አቤቱ በጥፋት ሰይፍ ሳልቆረጥ የንስሐን ፍሬ እንዳፈራ አድርገኝ፤

[110] 1ኛቆሮ 1፥18
[111] ዘፃ 1፥2-3፤9
[112] መዝ 38፥14
[113] መዝ 118፥18
[114] መዝ38፥13-14፤ መዝ 29፥12-13





አቤቱ እንደበቴ በሞት ሳይዘጋ በፊት የመስቀልህን ምስጋና እናገር ዘንድ አብቃኝ፤

አቤቱ በማይፈታ ሰንሰለት ከመታሠሬ በፊት የደጅህን በር አንኳኳ ዘንድ አብቃኝ፤

አቤቱ ገበያውና ግብይቱ ከማለቁ በፊት ለነፍሴ የሚጠቅመኝን እንድሸምት አብቃኝ፤

አቤቱ የሙሽራው ደጅ ከመዘጋቱ በፊት የመብራቱን ዘይት እገዛ[115] ዘንድ አብቃኝ፤

አቤቱ ጨኸት ከመሆኑና መለከትም ከመነፋቱ በፊት ለመንገዴ ስንቅን እንዳዘጋጅ አብቃኝ፤

አቤቱ ስለ ኃጢአቴ ምስክር የሚሆነው መጽሐፍ ከመነበቡ በፊት ዕዳዬን እንድከፍል አብቃኝ፤

አቤቱ ለመናገር የማይቻልበት ዝምታ ከመምጣቱ በፊት በምስጋና እተጋ ዘንድ የበቃሁ አድርገኝ፤

አቤቱ በአንተና በቅዱስ መንፈስህ እኖር ዘንድ የበቃሁ አድርገኝ፤

አቤቱ የወንጌልህን ፈለግ እንድከተል፣ በመስቀልህም እንድ መረኮዝ አብቃኝ፤

አቤቱ ከኋላህ ይከተሉህ ዘንድ እንዳበቃሃቸው እንደ ደናግል[116]፣ ሕማማትህን ሱታፌ እንዲሸከሙ እንዳደረግካቸው እንደ ሰማዕታት፣ የመስቀልህን ቀንበር እንዲያነሡ እንዳበቃሃቸው እንደ ጻድቃን በሹቱህ መዓዛ የረካሁ አድርገኝ፤

(፶፯)የመስቀሉን ሞት የተቀበለ ሁሉ የዚህ ዓለም መከራ፣ ችግር፣ስቃይና ጭንቅ አይነካውም፤ አንተ በወንጌል ‹ነፍሱን ሊያድናት የሚወድ ቢኖር

[115] ማቴ 25
[116] ማቴ 27፥55

ይተዋት፤ ነፍሱን ስለ እኔ የተዋት ሁሉ ያገኛታል[117]፣ እንዳልከ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል[118] ይህንን ፈርቻለሁና አቤቱ በነፍሴ ከመጥፋት አድነኝ፤ አቤቱ በችንካሮችህ በመመካት ልቤ የጸና ነው፤ አቤቱ ልቤ ለምስጋናህ የተጋ ነው፤ ፍቅርህ ከሐኬት እንቅልፍ ያነቃኝ፤ መስቀልህንም ለማወደስ የልቡናዬን ዓይኖች ይግለጥልኝ፤

(፶፰)መስቀልህ የማይነቅዝ ዕፅ ነው፤

መስቀልህ የማይዋጋ (የማይደርቅ) ዕፅ ነው፤

መስቀልህ የማይጠፋ ዕፅ ነው፤

መስቀልህ የፀሐይ ሙቀት፣ የነፋሳትም ግርፋት የማያደርቀው ዕፅ ነው፤

መስቀልህ ውኆችና የነፋሳት ንጽውጽውታዎች ሊያነዋውጡት የማይቻላቸው ዕፅ ነው፤

መስቀልህ የባሕር ሞገዶች ሊገፉት የማይቻላቸው ዕፅ ነው፤

መስቀልህ የዝናማት ከብደት ሊጥሉት የማይቻላቸው ዕፅ ነው፤

መስቀልህ ርኩሳን መናፍስት ሊቀርቡት የማይቻላቸው ዕፅ ነው፤

መስቀልህ ከገነት ዛፎች መካከል የሚመስለው የሌለ፤ ከበረሐ እንጨቶች መካከልም የሚተካከለው የሌለ ዕፅ ነው፤

መስቀልህ ከአርዘ ሊባኖስ መካከል የሚመስለው፣ ከምርሰኔም[119] ዛፎች መካከል የሚተካከለው የሌለ ዕፅ ነው፤የኢላጤኖስ[120] ዛፎችም እንደ አበቃቀሉ

117 ማቴ 10+39፤
118 ማቴ16+25-26
119 የበቱ እንጨት ባርሰነት ወይም አደስ(ኪ.ወክ፣ ገጽ 611)
120 ቁመቱ ረዥየም፣ ቅጠሉ ሰፋፊ፣ ፍሬው መድኃኒት የሚሆን ዛፍ( ኪ.ወክ፣ ገጽ 222)





አይሆኑም፤የቄድሮንም [121]ዛፎች በውበት አይተካከሉትም፤የጳውቄናም[122] ዛፎች አይመስሉትም፤

መስቀልህ በሌሎች ዛፎች ላይ የማይመካ ለስላሳ ዕፅ ነው፤

መስቀልህ በእርሱ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ይል ዘንድ የወደደው ዕፅ ነው፤

መስቀልህ ከቅርንጫፎቹ የወይንን ዝናማት ያንጠባጠበ ዕፅ ነው፤ ደመናውም ከአርያም የሆነ የብርሃን ደመና ነው፤ እርሱም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ምእመናንም ከእርሱ ከሚንጠባጠበው የምሕረት ዝናብ እንዲረኩ አደረገ፤ ከእርሱም ምእመናን የጥምቀትን ማኅተም ወሰዱ፤ ፊታቸውንም በመስቀል ምልክት ባማተቡ ጊዜ ሰይጣን ከፊታቸው ይሸሻል፤ የሐዋርያት ትምህርት ሐዘውትረህ ገጽህን በመስቀል ምልክት ለማማተብ ትጋ፣የመስቀል ምልክት በሰይጣን ላይ የሕማም ምልክት ነውና፤[123]፣ እንዳሉ፡፡

(፶፱)መስቀል ባለበትም ሁሉ ልቡን ይመታዋል፤ መስቀልህንም በማሰብ ጊዜ ሰይጣን ይሸሽ ዘንድ ይጨነቃል፤

(፷)አቤቱ ነቢያት የመስቀልህን ምልክት አሳዩ፤ ሙሴ የመስቀልን ምልክት በራፊድ ምድረ በዳ ሠራ፤ ኢያሱን አማሌቃውያንን እንዲዋጋቸው አዝዞ እርሱ ወደ ተራራ ወጣ፣ ሁለት እጆቹንም ዘርግቶ በመስቀልም አምሳል ከፍ አድርጎ ከጠዋት እስከ ማታ ቆየ፣ እጆቹንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ያሸንፋል፣ እሥራኤልም ይሸነፋል፤ እጆቹን በዘረጋ ጊዜ ግን አማሌቅ ይሸሻል፤ እሥራኤልም ያሸንፋል፤ አሮንና ሖርም እጆቹን ተሸከመው ዋሉ፤ የሙሴም እጆች ከባዶች ነበሩ፤ ስለዚህም እጆቹን እንዳያወርድ ታላላቅ ድንጋዮችን በወዲህና በወዲያ አደረጉ፤

121 የሊባኖስ ዛፍ (ኪ.ወክ፣ 784)
122 እንደ ጥድ እንደ ዝግባ ያለ ዛፍ (ኪ.ወክ፣ ገጽ 905)
123 መጽሐፈ ሲኖዶስ፣ ተፈሰሐ ውሉደነ፣ ዐንቀጽ 47

(፶፩)በመስቀልህ አምሳል በተዘረጉት እጆቹ አማሌቅ ድል ሆኑ[124]፤ እንደ ዚሁም የሚጣሉኝን በመስቀልህ ኃይል ተጣላቸው፤ የእኔንም ውጊያዬን ባርክ፡፡

(፶፪)እንደዚሁም ሙሴ የመስቀልህን ምልክት እሥራኤል ከግብጽ ሲወጡ፣ የያዕቆብም ወገኖች ከጠላቶቻቸው ሲላቀቁ አሳየ፤ አንድ ጊዜ ባሕሩን በበትሩ ወደፊት መታው፣ ደግሞም አግድም መታው፤ በዚህም የመስቀል ምልክት ሆነ ውኃውም እንደ ግድግዳ በዚህና በዚያ በኩል ቆመ፤ የእሥራኤልም ልጆች በመካከሉ አለፉ፡፡ አቤቱ ለእኔም በጥፋት ባሕር መካከል የጽድቅንና የሕይወትን መንገድ ጥረግልኝ፣ በመስቀልህ ኃይልም ቅዘፍልኝ፡

(፶፫)ዳግመኛም ሙሴ በበትሩ ዐለቱን በመታ ጊዜ የመስቀልን ምልክት አሳየ፤ አንድ ጊዜ ወደፊት መታው፣ እንደ ገናም አግድም የእግዚአብሔር እግሮች ወደቆሙበት ወዲህና ወዲያ መታው፤ ከጠጣሩ ዐለትም ውኃ ወጣ፡፡ በመስቀልህም ምልክት ይህ ተአምር ተደረገ፤ አሁንም ርኩሰቴን ለማንጻት ይሆን ዘንድ በበትረ መስቀልህ ኃይል ለእኔም የሕይወትን ውኃ አፍልቅልኝ፡፡

ለኃጢአቴ ፍዳ መቼውኑም አሳልፈህ አትስጠኝ፤ ስለ ወዳጅህ ስለ አብርሃም፣ ስለ ባለሟልህም ስለ ይስሐቅ፣ ስለ ቅዱስህም ስለ እሥራኤል ብለህ፤ በፊትህም ታማኝ ሆኖ ስለተገኘ ስለ ዳዊት፣ መምጣትህን በዓለም ሁሉ ስለ ሰበኩ ስለ ነቢያት፣ ስለ ቅዱስ ወንጌልህ ለመመስከር ሲሉ እንደ ቀንደ መለከት ስለ ጮኹት ሐዋርያት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ወላዲተ አምላክ ስለ ሆነች ስለ ቅድስት ንጽሕት ድንግል ማርያም፣ ስለ ቅዱስና ቡሩክ ዕፀ መስቀልህ ስትል በበረከትህና በሰማያዊው አባትህ በረከት፣ ማኅያዊ በሆነው መንፈስህም በረከት፣ከዓለም ሁሉ በፊት ጀምረው ደስ ባሰኙህ[125] በቅዱሳኑ ሁሉ በረከት ባርከኝ፡፡

[124] ዘጸ 17፥8-13
[125] ሉቃ 1፥70



ውዳሴ መስቀል ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

(፶፬)አቤቱ ጽድቅ እንደ ጋሻ ይከብብሃል[126]፣ ምሕረትህም የሚያምኑትን ሁሉ ይመግባቸዋል፤

አቤቱ ሰማያትና የሰማያትም ሰማያት በትእዛዝህ ተሰቀሉ፣ ምድርም በቃልህ በውኃ ላይ ጸናች፣ ፀሐይና ጨረቃ፣ ከዋክብትም በትእዛዝህ ያበራሉ፤ የፊትህ መላእክት፣ የምስጋናም መላእክት በአፍህ ቃል የከበሩ ናቸው፡፡ ከሰው ሁሉ አዳምን ከፍ አደረግከው፣ በእጅህም ሠራኸው በማይጠፋ መልክህ አምሳልም ሳልከው፤ የሕይወትንም መንፈስ በፊቱ ላይ እፍ አልክበት፤ ሁሉንም ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፤ በጎችንና ላሞችን ሁሉ፣ የዱር እንስሳትንና የሰማይ አዕዋፍን፣ የባሕር ዓሦችንና በባሕር ውስጥ የሚመላለሰውን ሁሉ፣ እንዲያያቸውና ስምም እንዲሰጣቸው ነፍስን ሁሉ አመጣህለት፤ አዳም ሕይወት ላለው ሁሉ የሰየመው ስሙ እንደዚያው ይሆናል፡፡

(፶፭)አዳም ከእርሱ እንዳይበላ ያዘዝከውን በልቶ በበደለ ጊዜ ከደስታ ገነት ወጣ፤ አንተ ግን አዳም ዕፀን በመብላት ያመጣውን ፍዳ ክቡርና ማኅያዊ በሚሆን መስቀል ከፈልክለት፡፡ ማኅያዊ ስለሚሆን ሕማማተ መስቀልህ ስትል የእኔንም ዕዳ ከፈልልኝ፤ ኃጢአቴንም ሁሉ ደምስስ፤ ዳግመኛም ለአባታችን ለኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ ምድርን አደስካት፤ ለእርሱም ምድር ዳግመኛ ላትረገም፣ በውኃም ላትጠፋ ማልኩልህ፤ ዝናምም በሆነ ጊዜ ሁሉ ቀስቴን በደመና ላይ እሰይማለሁ፤ ደመናትም ምድርን ሲያርሱ በተዘጋጁ ጊዜ እኔ የቃል ኪዳኔን ምልክቱን አያለሁ፤ ከአንተ ጋር ያደረግ ኩትንም ቃል ኪዳን አስባለሁ፤ ዳግመኛም ዓለምን በንፍር ውኃ አላጠፋትም[127]፣ ብለህም ማልክለት፡፡

(፶፮)አሁንም በእኔ ላይ የኪዳን ምልክት የሆነውን ቅዱስ መስቀልህን አድርግ፤ (እርሱ) ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋር ያደረግከው ቃል ኪዳን ምልክት ነውና፡፡ ቅዱስ መስቀልህ በምእመናን እጅ ያለ የማሸነፊያ ጦር ነው፤ ቅዱስ መስቀልህ ለዐማፅያን የሚያጠፋቸው ቀስት ነው፤ ለእኔ ግን የመስቀልህ ኃይል ረዳት ይሁነኝ፤ ዳግመኛም ልጁ ይስሐቅን ሊሠዋ ወደ መሠዊያው

[126] መዝ 90፥5፤ 94፥4
[127] ዘፍ 9፥8-17

በወጣ ጊዜ ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳንን አደረግክ፤ ለመሥዋዕቱም እንጨትን ፈለጠ፣ በትከሻውም አሸከመው፤ ይስሐቅም አብርሃምን ‹እነሆ ለመሥዋዕቱ የሚሆን እንጨት አለ፣ ቢለዋም አለ፤ የሚሠዋው በግ ግን ወዴት አለ?› ብሎ ጠየቀው፤ አብርሃምም ‹በጉን እግዚአብሔር ያዘጋጃል ልጄ› አለው።

(፶፯)የትንቢት መንፈስ በሁለቱም እንደበት ይናገራል፤ ይስሐቅ ስለ ምድራዊ በግ ሲጠይቅ ‹የመሥዋዕቱ በግ የት አለ?› አለ። የትንቢት ትርጓሜ ግን ቃሉን ወደ እግዚአብሔር ልጅ ይመልሰዋል፤ አብርሃምም ‹እግዚአብሔር በጉን ያዘጋጃል» አለው፤ይህንንም ስለ ልጁ መሠዋት ተናገረው፤የትንቢቱ ትርጓሜ ግን ወደ ሰማያዊው በግ ይመልሰዋል፤ ይስሐቅ አባቱ እርሱን የሚሠዋበትን መሠዊያ እንጨት ይዞ መጓዙ በእናቱ በኩል አባቶቹ የሆኑ አይሁድ በእርሱ ይሠውት ዘንድ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ የሔደ የመድኅን ምሳሌ ነው። የጥበብ ምንጭ የሚሆን ጳውሎስም ‹ሕግ ነበራቸው፣ ሥርዓትም ነበራቸው፤ ለእነርሱ ልጅ ይሆን ዘንድ ተስፋን ሰጣቸው፤ እነርሱ አባቶቻችን ናቸው፤ከእነርሱም ክርስቶስ ተወልዷል[128]› አለ፤ ደብረ ማሲኖማ[129] የቀራንዮ ምሳሌ ነው፤ በይስሐቅ ፋንታ የተሠዋው በግም የመድኃኒታችን ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ ‹ወደሚወስዱት ሥፍራ እንደ በግ ሊሠዋ መጣ፤ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ በሕማሙ ጊዜ አፉን አልከፈተም፤ ሊፈርዱበትም ወሰዱት፤ ልደቱን ማን ያውቃል? ስለ ሕዝቡም ኃጢአት ለሞት ተሰጠ[130]› አለ።

(፶፰)ይስሐቅም የአባቱ ቢላዋ በላዩ ላይ በተዘረጋ ጊዜ በመሠዊያው ላይ ተጋድሞ የሚሆነውን ነገር ተረዳ፤ በእርሱ ፋንታ ከእግዚአብሔር የመጣው በግ ተሠውቷ ልና። ይስሐቅ አልሞተም፤ እንዲሁም መለኮትም ከሥጋ ጋር በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ ሕያው ነው እንጂ የመስቀልም ሕማማት አላገ

[128] ሮሜ 9÷4-5

[129] አባ ጊዮርጊስ አብርሃም ልጁን ሊሠዋ የወሰደበትን ተራራ ደብረ ማሲኖ ይለዋል። መጽሐፍ ቅዱስ አካባቢውን ‹የሞሪያ ምድር› ነው የሚለው (ዘፍ 22÷2) ማሲኖ ማለት በግእዝ የጥፋት ተራራ ማለት ነው። ጌታቸው ኃይሌ ደራሲው ሐርማ የሚለውን ቦታ አስቦ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሐርማ የሚለውም ሆነ ማሲኖ የሚለው ትርጉም ጥፋት የሚለው ነው።

[130] ኢሳ 53÷7-8፤ የሐዋ 8÷32-33





ኘውም፤ ይስሐቅ ከበጉ ጋር እንዳል ታረደ ሁሉ መለኮትም ከሥጋ ጋር አልታመመም፤ ነገር ግን ከሥጋ ጋር አንድ ሆኖ ነበር እንጂ፣ ለአንዲትም ሰዓት አልተለየም፣ ለዓይን ጥቅሻ ያህልም ቢሆን ።

መለኮትህ ከሥጋህ ያልተለየ ሆይ፣ እኔን አገልጋይህን ፍሥሐ ክርስቶስን ከንጹሐን በጎችህ መንጋ እንድለይ አታድርገኝ።

(፶፱)ያዕቆብም ኤፍሬምና ምናሴን በባረከ ጊዜ የመስቀልን ምልክት አሳየ፤ ዮሴፍ ምናሴን በግራው ከእሥራኤል በቀኙ አቆመው ኤፍሬምንም በቀኙ፣ በእሥራኤል ግራ አቆመው፤ እሥራኤልም እጆቹን አስተላለፈና ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ፣ ግራ እጁንም በምናሴ ራስ ላይ አደረገ ዮሴፍም እሥራኤልን «የሚበልጠው ይህ ነውና ቀኝ እጅህን በእርሱ ላይ አድርግ» አለው፤ እሥራኤልም «ልጄ ሆይ ዐውቃለሁ፤ ይህ ደግሞ ታላቅ ሕዝብ ይሆናል» አለው[131]። እሥራኤልም በመስቀል ምልክት በረከት እንደሚጸና ዐወቀ፤

(፷)በዚህም ምክንያት እጆቹን በመስቀል አምሳል አደረገ፤ እንደዚሁም ንጉሣችንን ልብነ ድንግልን በቅዱስ መስቀልህ በረከት ባርከው፤ በእርሱ ላይ እሥራኤል የተባለ የያዕቆብ በረከት፣ለእርሱና ለዘሩም የተሰጠው የጸጋ ሀብት ሁሉ ያድርበት ዘንድ የመንግሥትና የክህነት፣ የትንቢትም ዘይት ከእርሱ ዘንድ፤ ከዘሩም ዘንድ፣ ከዘር ማንዘሩም ዘንድ እንዳይጠፋ፤ ለዓለመ ዓለም፣ አሜን።

(፷፩)ለክቡር መስቀል የተሰጠው የጸጋ ሀብት እንደምን የሚያህል ነው!

መስቀልህ በውጊያ ጊዜ የጦር መሣርያ፣ ለወታደሮችህም የመሰኮት ሰይፍ ነው፤

መስቀልህ በጠብ ጊዜ ማዕከሉን የሚመታ፣ ኃጢአትንም ግንብ የሚያፈርስ ነው፤

መስቀልህ ለሙት ልጆች አባት ለባልቴቶችም ዳኛ ነው፤

[131] ዘፍ 48÷3-14

መስቀልህ በባሕር ለሚጨነቁ ጸጥ የሚያደርግ፣ በምድረ በዳ ለሚንከራተቱም ወደብ ነው፤

መስቀልህ ለዕውራን መሪ፣ ለአንካሶችም ምርኩዝ፣ ለድኩማንም ኃይላቸው ነው፤

መስቀልህ ሕፃናት ምእመናንን በቤተ ክርስቲያን ጡቶች የሚያሳድግ ዕፅ ነው፤

መስቀልህ ለነገሥታት አክሊል ነው፤

መስቀልህ ለክርስቶሳውያን ትምክህታቸው ነው፤

መስቀልህ ጠንቋዮችን የሚያጠፋ፣ እናውቃለን ባዮችንም የሚበትን ነው፤

መስቀልህ የካህናት ሰያሚያቸው፣ የዲያቆናትም የተልዕኳቸው ሽልማት ነው፤

መስቀልህ የወደቁትን የሚያነሣቸው፣ደካሞችንም እንደ ዋልያ የሚያሮጣቸው ነው፤

መስቀልህ ለሙሽራህ ለቤተ ክርስቲያን ጥሎሿ፣ በምኩራብ ለፈታሃትም ምልክቷ ነው፤

መስቀልህ በእርሱ ለሚታመኑ የእምነት መሠረት፣ የሃይማኖትም ዓምድ ነው፤

መስቀልህ ጥንቆላን ሁሉ ማርከሻ፣ሙተትንም ሁሉ ማጥፊያ ነው፤

በመስቀልህና በቁጣህ ሰይፍ የመስቀልህን ጠላቶች በትናቸው፤ የመለኮትህንም ወንጌል ሊያጠፉ የሚፈልጉ ሁሉ ከምድረ ገጽ የጠፉ ይሁኑ፤

(፷፪)አቤቱ የአይሁድን ቀንድ አድክም፤

አቤቱ የአረማውያንን ቀንድ ቀጥቅጥ፤

አቤቱ ቁጣህ በላያቸው ላይ ትሁን፣የቅናትህም እሳት በላያቸው ላይ ትንደድ፤

አቤቱ አፍርሳቸው እንጂ አታንጻቸው፤

አቤቱ መብረቆችህን አብርቅና በትናቸው፤





(፷፫)አቤቱ ጋሻና ጦር አንሣ፤ ጠላቴን እንድዋጋው ትረዳኝም ዘንድ ተነሣ፣ መቅሰፍ ትህም ሁል ጊዜ በአንተ በሚያፍሩት ላይ ይሁን፤ የሕያው የእግዚአ ብሔር ልጅ ይሉህ ዘንድ የቁጣህም ሰይፍ የነቢያትን ቃል ሐሰት ነው በሚሉ፣ በሐዋርያትም ትምህርት በማያምኑ ላይ ሁሉ ይሁን እነርሱ በመከ ራቸው ይመካሉ፣ በልባቸው ምኞትም ይታበያሉ፤ ለሰይጣን ፈረሶቹ የሆኑት እነርሱ ናቸው፤ ለአጋንንትም ማደርያ ሆኗቸው በመስቀልህ መታሰቢያቸውን ከምድር አጥፋ፤ ዳግመኛም የአንተ ወዳጅ የሚሆን ንጉሣችን ልብነ ድንግልን ፈጥኖ እንዲያጠፋቸውና መታሰቢያቸውንም እንዲደመስስ አብቃው[132]፤ አቤቱ ንጉሥ ልብነ ድንግል ሀገራቸውን እንዲመዘብር አብቃው፤አቤቱ ንጉሥ ልብነ ድንግል ዐመፀኞቹን ሁሉ ድል እንዲያደርግ አብቃው፤ በሔደበትም ሁሉ የመስቀልህ ኃይል ረዳትና መሠወሪያ ይሁነው፤ መስቀልህ በሥውርም ሆነ በግልጥ ከሚነሣ ጠላት ይታደገው፤መስቀልህ አገልጋይህ ፍሥሐ ክርስ ቶስን የሚጠሉትን በመቅሰፍትና በጥፋት፣ የሚወዱትንም በምሕረትና በቸር ነት ይለያቸው፤ ለዓለመ ዓለም ፣ አሜን፡፡

፳

(፷፬)አቤቱ በመስቀልህ እመካለሁ፣ በእጅ መንሣቱም ብዙ ምርኮን እንዳገኘ ሰው እደሰታለሁ፤

አቤቱ በመስቀልህ እመካለሁ፤በምስክርነቱም ጥሩ ወይን እንዳገኘ ሰው ሐሴት አደርጋለሁ፣

አቤቱ በመስቀልህ ልጅ በአባቱ ክብር እንደሚመካው እመካለሁ፤

አቤቱ አገልጋይ በእመቤቷ ክብር እንደምትመካ እመካለሁ፤

132 ይህ አገላለጥ መጽሐፉ የተገለበጠው ንጉሥ ልብነ ድንግል ከግራኝ ሠዊራት ጋር ወጊያ በጀመረ ባቸው የመጀመርያዎቹ ዓመታት መሆኑን እንድንገምት ያደርገናል፡፡

(፷፭)አቤቱ በመስቀልህ እመካለሁ፤እተማመናለሁም፤የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ ‹ከክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት የለኝም[133]› እንዳለው፤

አቤቱ በመስቀልህ እመካለሁ፣ እንዲህ እያልኩም እታመናለሁ

በመስቀል ችንካሮች ለተቸነከርከው ላንተ ምስጋና ይገባል፣

የመስቀልን ኃፍረት ለታገሥከው ላንተ ምስጋና ይገባል፣

ሕማማተ መስቀልን ለተቀበልከው ላንተ ምስጋና ይገባል፣

ወደ መስቀል መውጣትን እምቢ ላላልከው ላንተ ምስጋና ይገባል፣

ከመስቀል ወደ ሲኦል ለወረድከው፣ ምርኮንም ከጠላት እጅ ለነጠቅከው፣ የመንግሥትህንም ተቃዋሚ ሰለባውን ለሰለብከው፤ትዕቢተኛውን ዲያብሎስንም በመስቀልህ ለጣልከው ላንተ ምስጋና ይገባል፤

በመስቀልህ ትዕቢተኛውን ወደ መሬት ለጣልከው ምስጋና ይገባል፤

በመስቀልህ ሞትን ለዘለፍከው ምስጋና ይገባል፤

በመስቀልህ ጨለማን ለቀጣኸው ምስጋና ይገባል፤

በመስቀልህ ሞትን ለገደልከው ምስጋና ይገባል፤

አቁሳዩን በመስቀልህ ላቆሰልከው ምስጋና ይገባል፤

በመስቀልህ የሲዖል ምርኮዋን ለመዘበርከባት ምስጋና ይገባል፤

የመከራን ግንብ በመስቀልህ ላፈረስከባት ለአንተ ምስጋና ይገባል፤

(፷፮)አቤቱ ትንትናህ ትዕቢተኞችን ጣላቸው የመስቀልህም ኃይል ሲኦልን ደመሰሳት፤ በሞትህ ሙታን ሕያዋን ሆኑ፤ በትንሣኤህም ሰቃዮችህ አፈሩ፤ በእጅህ ችንካር የጠላት ሆድ ተመታ፤ በመስቀልህ ጦር አውሬው ተወጋ፤ በመለኮትህ ሰይፍ የመልአከ ሞት ራሱ ተቆረጠ፤ በበትርህም ኃይል የእባቡ

133 ገላ 6፥14





ራስ ተጠመደ፤ አንተ በመስቀልህ ትልቁን ዘንዶ አሠርከው፤ በጅራቱ የዓለምን ተራሮች ይስብ፣ ጽኑዓንንም ያሸንፍ ነበር፤ በቅንድቦቹም የዮርዳኖስን ወንዝ ይመጥጠው ነበር፣ አይፈስምም ነበር፤ ዓይኑን ከገለጠ በኋላ በሰባት ቀናት ይሰበስብ ነበር፤ በፊቱም ማንም ችሎ መቆም አይችልም ነበር፤ አንተ ግን በመስቀልህ አዋረድከው፤ (ወንዙንም) ሞላኸው፤ አፍንጫውንም እንደ ወፍ አነቆርከው፤ በዚያም ላይ ቀለበት አደረግከበት፤ ለሲኦል ምርኮኞችም ታየሃቸው፤ ለገሃነም ጭፍሮችም ኀፍረትን አላበስካቸው፡፡

(፷፯)የሚያስለቅሱ የነበሩ አለቀሱ፣ እረም አሉ፤ የሚያቆስሉትም ቆሰሉ፤ ያሳምሙ የነበሩ ታመሙ፤ ያለቀሱ ተደሰቱ፣ የተከዙም ፈነጠዙ፤

(፷፰)በመስቀልህ የታሠሩት ተፈቱ፣ ሕመምተኞችም ተፈወሱ፤

በመስቀልህ የአዳም መርገሙ ተሻረ፣ ሔዋንም ነጻ ወጣች፤

በመስቀልህ የጨለማ ሰቅ ተሰነጠቀ፣ የብርሃን ጌጥም ተሰፋ፤

በመስቀልህ የብረት ደጆች ተሰበሩ፣ የብረት መዝጊያዎችም ተቀጠቀጡ፤

በመስቀልህ የገነት በሮች ተከፈቱ፣ ዕረፍትም ተነጠፈ፤

በመስቀልህ የእሪት ቃል ተፈጸመ፤የትንቢቱ ቃልም ታተመ፤

በመስቀልህ የሰላም ዜና ተሰጠ፣ ሐዋርያትም አሕዛብን ለመጥራት ተላኩ፤

በመስቀልህ የመለኮት ወንጌል ተሰበከ፤ምእመናንም አመኑ፤

በመስቀልህ ኢትዮጵያውያን በፊትህ ሰገዱ፤ጠላቶችህም አመድን ይቅማሉ፤[134]

(፷፱)በመስቀልህ ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያው፣ እስከ ሰሜንም ለቅዱስ ስምህ እኩቴትና ምስጋና ይቀርባል፤ እኛም ስለ ቅዱስ መስቀልህ ቡሩክ የሆነውን ስምህን እንባርካለን፤ ቅዱስ ስምህንም እንቀድሳለን፤

በመስቀልህ ልዑል ስምህን ከፍ ከፍ እናደርጋለን፤

134 መዝ 71፥9

በመስቀልህ ክቡር ስምህን እናከብራለን፤

(፷)ስለ መስቀልህ አንተ የአባቶቻችን አምላክ በወዳጅህ በሙሴ አንደበት ለእሥራኤል ልጆች እንዲህ አልካቸው ‹እነርሱም ትውልዶቻቸውም በልብሳቸው ጫፍ ዘርፍ ያደርጉ ዘንድ፣ በዘርፋም ሁሉ ላይ ሰማያዊ ፈትል ያደርጉ ዘንድ፤ ይህም ምልክት ይሁናችሁ[135]› እኛም የተጠመቅን ዕፀ መስቀልህን ምልክት አደረግን፣ ካልተጠመቁት የተለየን እንሆን ዘንድ፤

(፷፩)ማኅየዊ በሚሆን በሕማማተ መስቀልህ ዓለምን ትቤዥ ዘንድ ወንድ ከማታ ውቅ ከቅድስት ድንግል ሰው የሆንክ የእግዚአብሔር ልጅ አንተ ነህ፤

በመስቀልህና በትንሣኤህ ተስፋን የሰጠኸን የእግዚአብሔርና የሰው ልጅ አንተ ነህ፤ ከመስቀልህም በፊት እንዲህ አልክ ‹ሙሴ የነሐሱን እባብ እንደ ሰቀለ እንደዚሁም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀልና ይሞት ዘንድ አለው[136]፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል[137]› ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው የነሐስ እባብ በአንተ ምትክ የተሰቀለ አይደለም፤ በመስቀልህ አምሳል ተሰቀለ እንጂ ሙሴ የመስቀልህን አምሳያ በእንጨት ላይ ባጋደመው የነሐስ እባብ አሳየ፤ በዚህም የተነሣ (ሙሴ) ባቆመው እንጨት ላይ የነሐሱን እባብ አመሳቀለ፣ በዚህም የእሥራኤል ልጆች ከእባብ ጥርስ መርዝ ዳኑ፤ እኔንም በመርዝ ከተሞሉት ከጥቋቁር እባቦች ጥርሶች በመስቀልህ ኃይል አድነኝ፤ እኔ አገልጋይህ፣ የአገልጋይህም ልጅ[138]፣በደምህ የገዛሃት፣ በመጻፋትህም ነጻ ያወጣሃት፣ በሞትህ ያሳመርካት፣ በትንሣኤህም የተገለጥክላት፣ በአባትህ ቀኝ በመቀመጥህም ያስጌጥካት የቤተ ክርስቲያን ልጅ ነኝና ከእኔም ዘንድ ምሕረትህን ከቶ አታርቅ፤ እኔን አገልጋይህን ፍሥሐ ክርስቶስን/ገብረ መስቀልን ርዳኝ፣ በመስቀልህ ኃይልም አድነኝ፤

[135] ዘኍ 15÷38

[136] ዮሐ 3÷14-14

[137] ማቴ 16÷21፤ 17÷23

[138] መዝ 115÷16





(፷፪)ዓለምን ሁሉ ለማማተብ፣አዳምንና ልጆቹንም ለማዳን እጆችህን በመስቀል ላይ የዘረጋኸውን አንተን አቤቱ አመሰግንሃለሁ፡፡

የሞት ሥልጣን በላያቸው እንዳይሠለጥንባቸው ለሚፈሩህ በመስቀልህ ምልክትን የሰጠኻቸውን አንተን አመሰግንሃለሁ፤

መስቀልህን ለእሌኒ ልጅ ቆስጠንጢኖስ አይሁድ በጎልጎታ ከቀበሩት በኋላ የገለጥከውን፣ በጨለማ ማኅተም እንዲታተምም ያልተውከውን አንተን አቤቱ አመሰግንሃለሁ፤ ነገር ግን በመስቀልህ ብርሃን አስጌጥከው፣ እርሱም የቅዱሳን ፀሐይ ነው፤

መስቀልን በመፈለግ የደከመችውን የአገልጋይህ የእሌኒን መሻትዋን የፈጸምክላትን አንተን አቤቱ አመሰግንሃለሁ፤

ቅዱስ መስቀልህን ለማግኘት ምልክት ይሆናት ዘንድ የዕጣኑን ጢስ የሰጠሃትን አንተን አመሰግንሃለሁ፤

(፷፫)ከልመናዋ ፊትህን ያልመለስክ፣የተመኘችውንም ከማግኘት ያላሳፈርካት፣ ብርሃኑንም ለዓለም እንድትገለጥ ያደረግካት አቤቱ አመሰግንሃለሁ፤

በመስቀልህ መገኘት በእፏ እልል እስክትል፣በእጆቿም እስከ ታጨበጭብ፣ በእግሮቿም እስክታሸበሽብ ድረስ በደስታ የመላሃት አቤቱ አንተን አመሰግንሃለሁ፤

በልጇ ፈረስ ልጓም ላይ በተደረገው የችንካርህ ምልክት[139] በጦርነት ጊዜ ጠላቶችን እንበረከካቸው፣የሚያምኑትንም አበረታሃቸው፣ እንደዚሁም በመስቀልህ የማሸነፍን ኃይል ስጠኝ፣ የእኔንም የአገልጋይህን ጠላቶች አስገዛልኝ፤

(፷፬)መስቀልህን ከካዱት ከእሥራኤላውያን ወገን ስላላደረግከኝ አቤቱ አብዝቼ አመሰግንሃለሁ፤ እነርሱ የአባቶቼ የሐዋርያት በሥጋ ዘመዶቻቸው ናቸው፤ በሃይማኖት ረገድ ግን ጠላቶቻቸው ናቸው፤ ቅዱስ ጳውሎስ ‹በወንጌ

[139] ቆስጠንጢኖስ በፈረስ ዕቃው ላይ የመስቀልን ምልክት ማድረጉን እያስታወሰ ነው፡፡

ልሰ በኩል ስለ እናንተ ጠላቶች ናቸው፣ በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው[140]፣ እንዳለ፤

እኔ ግን አቤቱ ከልጅነቴ ጀምሮ አንተን በማምለክ፣ በተስፋ መስቀልህ በመ መካት፣ የተመኘሁትን ስለሰጠኸኝ አመሰግ ንሃለሁ፤ ከአንተም በቀር ሌላ አምላክ የለኝም፤ በመስቀልህ ከማመን በቀርም ሌላ መመኪያ የለኝም፤

(፸፮)አቤቱ ለዐመፃ ያልተገዙ ቅዱሳት እጆችህ፣ በጥፋት መንገዶች ያልተመ ላለሱት ቅዱሳት እግሮችህ የተቸነከረበትን መስቀል ስለገለጥክልኝ አመሰግን ሃለሁ፤ በእርሱም ላይ ሐሞትና ኮምጣጤን ጠጣህ፤ በዚያም ላይ ቅዱስ ጎንህን በጦር ተወጋህ፣ ውኃና ደምንም አወጣህ፤

አቤቱ በላዬ ላይ ስላበዛኸው ጸጋ አመሰግንሃለሁ፤ እርሱም በአንተ ማመንና መስቀ ልህን መቀበል ነው፤

መስቀልህን በማግኘት ነፍሴ ታመሰግንሃለች፤

መስቀልህን ስለማግኘት ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል፤

መስቀልህን ስለማግኘት አጥንቶቼ ያመሰግኑሃል፤

(፸፯)መስቀልህን ስለ ማግኘት መገጣጠሚያዎቼ ያመሰግኑሃል፤

መስቀልህን ስለማግኘት በአንደበቴ እልል እላለሁ፤

መስቀልህን ስለ ማግኘት በጉሮሮዬ እጮኻለሁ፤

መስቀልህን ስለ ማግኘት በእጆቼ አጨበጭባለሁ፤

መስቀልህን ስለማግኘት በእግሮቼ አሸበሽባለሁ፤

(፸፰)ከእንግዲህ በተሠማራሁበት ቦታ ሁሉ፣ በሔድኩትም ቦታ ሁሉ፣ በተጓ ዝኩበትም ሁሉ፣ በገባሁበትም ሀገር ሁሉ መስቀልህ ያብራልኝ፤ በዋል ኩበትም ቀን፣ ባደርኩትም ሌሊት፣ የመስቀልህ ሞገስ ከእኔ አይራቅ፤ አቤቱ

[140] ሮሜ ፲፩÷28





በጠላት ዘንድ ድል ማድረግን አገኝ ዘንድ በመስቀልህ አትመኝ፤ አቤቱ በኃይ ሌም መጠን በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እዘምርልሃለሁ፤የመለኮትህን ሰይፍ እታ ጠቃለሁ፣ እርሱም በቅዱስ መስቀልህ ማመን ነው፤ በቅዱስ መስቀልህ ማመን በጨለማ ውስጥ ላሉት እንዳበራላቸው ሁሉ፣ ለእኔም መለኮታዊ ጥበብህን ያብራልኝ፤ አሜን፡፡

(፸፱)ሰማልያል የተባለውን ሰይጣን የጣለው፣ ሠራዊቶቹንም የበተናቸው መስቀልህ፣ የእኔንም ጠላቴን ይጣልልኝ ሠራዊቱንም ይበትናቸው፤ አቤቱ አምላኬ ተነሥ፣ እጅህም ከፍ ከፍ ትበል፤በመስቀልህ የማያምኑትን ትደመስ ሳቸው ዘንድ፤ በሞትህ የተደሰቱትን ቀኝህ ትዋጋቸው፤

(፹)አቤቱ መስቀልህ በላዩ ላይ የተኛህበት የሕማማትህ አልጋ ነው፤ በስድ ስት ሰዓትም ሰማይን አወከሃት፣ ምድርንም አንቀጠቀጥካት፤ አቤቱ ስለ ሕማ ምህ፣ ስለ መስቀልህም፣ እርሱም የሙሽርነትህ አልጋ የሚሆን፣ በላዩም ላይ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ የተሞሸርክላት፣ ከአንተ በመነጨም ውኃ ያጠብ ካት፣ በቀኝ ጎንህ በፈሰሰው ደምህም ያተምካት ከቀኝህ ሕይወት መነጨ፤ በዚህም ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመኃልየ ሰሎሞን እንዲህ ስትል ትለምንሃለች ‹በቀትር ጊዜ ወዴት ትመሰጋለህ (ትተኛለህ)[141]? ስለምንስ ከባል ንጀሮችህ መንጎች በኋላ እቅበዘበዛለሁ?›[142] ‹በቀትር ጊዜ የት ትመሰጋለህ (ትተ ኛለህ)? ያለችው፤ በቀትር ጊዜ በመስቀልህ ላይ መተኛትህን ነው፡፡ ዳግመ ኛም ‹ወዴት ታሠማራለህ?› ያለችው፤ መንጋውን የሚያሠማራ ሁሉ ወደ ከፍታ ቦታ ስለሚወጣ፣ በጎቹንም ስለሚጠብቅ፣ በበትርም ስለሚቆጣጠራ ቸው ነው፡፡ ዳግመኛም ደግሞ እንዲህ ትላለች ‹ስለምንስ ከባልንጀሮችህ መንጎች በኋላ እቅበዘበዛለሁ?› ይህም ማለት ‹በመስቀልህ እምን ዘንድ አንተ ወደ ተሰቀልክበት ምራኝ፣ የዐመፃን መንጎች የሚጠብቁትን በጎችንም ከተከላ እፍ የማያስጥሉትን ሌሎችን እረኞች እንዳልከተል› ማለቷ ነው፡፡

(፹፩)አቤቱ እኔንም ወደ ጽድቅ መንገድ በሚወስደው በምሕረትህ በትር ጠብቀኝ፣ ዳዊት ‹የመንግሥትህ በትር የጽድቅ በትር ነው፤ ጽድቅን ወደድክ

[141] ግእዙ ሖይቴ ትስክቤ ነው የሚለው

[142] መኃ ፩÷7

ዐመፃንም ጠላህ፤ ስለዚህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ እግዚአብሔር አምላክ የደስታ ዘይትን ቀባህ፣ በልብሶችህ ሁሉ ከርቤና ሽቱ፣ ዝባድም አሉ፤ በከባ ባድ ቀንዶችም ደስ ያሰኙሃል[143]› ብሏል፡፡ ከአሕዛብና ከኢየሩሳሌም ነገሥታት በቀር የከበዱ ቀንዶች እነማን ናቸው? የከበደችው የመንግሥት ሹመት በእነ ርሱ ላይ አረፈች፤ ‹በእነርሱ ደስ ያሰኝሃል› ሲልም ‹እነርሱ በመከራ ውስጥ ሆነው ደስ ሊያሰኙህ አልቻሉም፡፡ አንተ ግን በመከራ ውስጥ ያሉትን በመስ ቀልህ ደስ አሰኘሃቸው› ማለቱ ነው፡፡

(፹፪)አቤቱ አንተ በሁሉም ላይ ጌታ ነህ፣ ሥልጣንህም በሁሉም ላይ ነው፤ ታላቅነትህም ከሁሉም በላይ ነው፤ የሁሉም ጌታ ተባልህ፣ በሁሉም ዘንድም ተጠራህ፤

አንተ ሊቀ ካህናት ነህ፤

አንተ ንጉሠ ነገሥት ነህ፤

አንተ ታላቅ ነቢይ ነህ፤

አንተ የእረኞች አለቃ ነህ፤

አንተ የምትናገር በግ ነህ፤

አንተ ድልብ ሠንጋ ነህ፤

አንተ የአንበሳ ልጅ አንበሳ ነህ፤

አንተ የሕይወት ውኃ ምንጭ ነህ፤

አንተ የመድኃኒት ቀንድ ነህ፤

አንተ የጽድቅና የሕይወት መንገድ ነህ፤

አንተ የጽድቅ ፀሐይ ነህ፤

አንተ የብርሃን ኮከብ ነህ፤

[143] መዝ 19÷6-8





አንተ የሕይወት እንጀራ ነህ፤

አንተ የመድኃኒት ጽዋ ነህ፤

አንተ በር ነህ፤

አንተ የሰው ልጅና የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤

ይህንን ሁሉ ስለ እኛ ፍቅር ስትል ተጠራህበት፡፡

(፹፫)አንተ ሊቀ ካህናት ተብለሃል፣ ዳዊት ‹እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ[144]› እንዳለ፡፡ መልከ ጸዴቅስ አብርሃምን ባገኘው ጊዜ ኅብስቱንና ወይኑን አውጥቶ ሰጠው፤አንተም የስንዴውን ኅብስትና የጽዋው ንም ወይን ወሰድክ፤ ለደቀ መዛሙርትህም እንዲህ ብለህ ሰጠሃቸው ‹ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው፤ ይህ የጽዋዕ ወይንም ደሜ ነው፤ስለ እናንተ ለብዙዎች የተሰጠ[145]› ከመስቀልህ የተሠወረውን ምሥጢር ያሳየኸን አቤቱ አንተ ቡሩክ ነህ፤ አቤቱ አንተ ቡሩክ ነህ፡፡

(፹፬)አንተ ንጉሥ ተባልክ፣ ያዕቆብ ለልጁ ለይሁዳ ስለ አንተ ‹ልብሱን በወይን፣ መጎናጸፊያውንም በወይን ደም የሚያጥብ፤ ውርንጫውን በወይን ግንድ፣ የአህያ ይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ የሚያሥር ንጉሥ ከአንተ ይወጣል[146]› ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ ፡፡

(፹፭)አንተ ነቢይ ተብለሃል፣ ሙሴ ስለ አንተ ‹እግዚአብሔር ከወንድሞ ቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ፣ ከእኔም የሚበልጥ ነቢይን ያስነሣላችኋል፤ ያንን ነቢይ የማትሰማውም ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጥፋ[147]› እንዳ ለው፡፡ ‹እንደ እኔ ያለ› ያለው ለንጹሐን አገልጋዮቹ ስለሰጠኻቸው አዲስ ሕግ ነው፡፡ ‹ሙሴ የብሉይን ሕግ ለእሥራኤል ልጆች ሰጠ› እንዳለው ከአንተና ከሙሴ ብቻ በቀር ሕግ የሰጠ ነቢይ የለም፡፡ ጳውሎስ ‹ሙሴስ ስለሚናገረው

[144] መዝ 110÷4
[145] ማቴ 26÷26-28፤ ሉቃ 22÷19-20
[146] ዘፍ 49÷11
[147] ዘዳ 18÷18-19፤ የሐዋ 7÷37

ነገር ምስክር ሊሆን በቤቱ ሁሉ እንደ ሙሴ የታመነ ነበር፤ ነገር ግን ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል[148]› እንዳለው ሙሴም ‹የዚያን ነቢይ ቃል የማትሰማ ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጥፋ› ያለው ስለ ዐመፁብህ ስለ ሕዝበ አይሁድ ነው፤ በዚህም የተነሣ አይሁድን ‹ሙሴንስ ብታምኑበት ኖሮ በእኔ ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፏልና፤ ሙሴ የጻፈውንም ካላመ ናችሁማ እንዴት በቃሌ ታምናላችሁ[149]› አልካቸው።

(፺፮)አንተ እረኛ ተባልክ፣ ዳዊት ስለ አንተ በመዝሙር ‹ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ የእሥራኤል እረኛ ሆይ አድምጥ[150]› እንዳለው። አንተም በወን ጌልህ ቃል ‹ስለ በጎቼ ነፍሴን አሳልፌ የምሰጥ መልካም እረኛ እኔ ነኝ[151]› አልክ። በመስቀል ላይ ነፍስህን ስለ በጎችህ ቤዛ ስትል አሳልፈህ የሰጠህ በእውነት አንተ እረኛ ነህ።

(፺፯)አንተ በግ ተባልክ፣ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ስለ አንተ ‹የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ እነሆ[152]› ብሎ እንደመሰከረው፤ በእውነትም ለሰዎች ልጆች መድኃኒት ስትል በመስቀል ላይ የታረድክ በግ አንተ ነህ።

(፺፰)አንተ ላሕም ተባልክ፣ ዳዊት ስለአንተ ‹ቀንድና ጥፍር ካበቀለ እምቦሳ ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል[153]› ብሎ እንደ ተናገረ። ስለ ጠፋው ልጅም በወንጌል አባቱ እንደዚህ እንዳለ ተጽፏል ‹የሰባውን ፍሪዳ እረዱ፣ ደስም ይበለን፤ ይህ ልጄ ሞቶ ነበረ፣ ሕያው ሆኗል፤ ጠፍቶም ነበረ ተገኘ ቷል[154]› ለቅዱሳን ምሳ ትሆን ዘንድ በመስቀል ላይ የታረድከው ፍሪዳ አንተ ነህ።

[148] ዕብራ 3፥2-3
[149] ዮሐ 5፥46-47
[150] መዝ 80፥1
[151] ዮሐ 10፥14-15
[152] ዮሐ 1፥29
[153] መዝ 69፥31
[154] ሉቃ 15፥23-24





(፺፱)አንተ አንበሳ ተባልክ፣ ያዕቆብ ለልጁ ለይሁዳ ስለ አንተ ‹ይሁዳ የአን በሳ ደቦል ነው፤ ልጄ ሆይ ከአደንህ ወጣ፤ እንደ አንበሳ አሸመቀ፤ እንደ ሴት አንበሳም አደባ፤ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ የገዥ ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፤ ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ እርሱ ለአሕዛብ ተስፋ ይሆናል[155]› ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ ።

(፻)አንተ ቀንድ ተብለሃል፣ ዳዊት በመዝሙር ‹በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅ ላለሁ፤ ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ[156]› እንዳለው። ዘካርያስም ‹ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተነሡት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረው በብላ ቴናው በዳዊት ቤት የመዳንን ቀንድ አስነሣልን[157]› አለ ዳዊትም ‹ከአንበሳ አፍ አድነኝ፣ ብቻነቴንም አንድ ቀንድ ካላቸው[158]› ዳግመኛም ‹ቀንዴ አንድ ቀንድ እንዳለው ከፍ ከፍ ይላል፤ ሽምግልናዬም በዘይት ይለመልማል[159]›

(፻፩)አንተ ድንጋይ ተብለሃል፣ ዳንኤል ስለ አንተ ‹እጅ ሳይነካው አንድ ድን ጋይ ከረኸርም ተራራ ተፈንቅሎ ወረደ፤ የወርቁንም ሐውልት ሰባበረው[160]› ብሎ ትንቢት ስለ ተናገረልህ። ዳዊትም ስላንተ ‹ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፤ ይህችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፤ ለዓይናችንም ድንቅ ናት[161]› አለ። ለሚያ ምኑብህ የሕይወት ድንጋይ አንተ ነህ፤ ባንተ ለማያምኑብህ፣ በቃልህም ለሚደናቀፉ የዕንቅፋት ድንጋይ አንተ ነህ፤ በመስ ቀልህ ለማይደገፉ የጥርጥር ድንጋይ አንተ ነህ፤ የሕይወት ድንጋይ ሆይ፣ እኔ ግን ባንተ ተደገፍኩ፤ አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ አምና ለሁ፤ እኔን አገልጋይህን እንደ መልካም ጋሻም[162] በመስቀልህ ኃይል ከልለኝ።

[155] ዘፍ 49፥9-10
[156] መዝ 131፥17
[157] ሉቃ 1፥69
[158] መዝ 22፥21
[159] መዝ 92፥10
[160] ዳን 2፥34
[161] መዝ 117፥22
[162] መዝ 5፥12

(፺፩)የሕይወት ውኃ ያለብህ የክብር ጉድጓድ አንተ ነህ፤ የሚሰቅሉትን ሲዘልፋቸው ኢሳይያስ እንዲህ አለ ‹እናንተ ጽድቅን የምትከተሉ እግዚአ ብሔርንም የምትሹ ስሙኝ፣ ከእርሱ የተቆረጣችሁበትን ድንጋይ ከእርሱም የተቆፈራችሁበትን ጉድጓድ ተመልከቱ[163]› ብሎ የተናገረልህ:: አንተም እንጂ በወንጌል ‹እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ አይጠማም[164]› ብለሃል፤ የሕይወት ውኃ ከከንፈሮችህ ይዘንባል::

(፺፪)አንተ የጽድቅና የሕይወት መንገድ ተብለህ ትጠራለህ፣ አንተ በቅዱስ ወንጌል ‹የሕይትና የእውነት መንገድ እኔ ነኝ[165]› ‹በእኔም የሚሔድ አይደናቀፍም፤ የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና[166]› ብለህ እንደ ተናገርከው ::

(፺፫)ፀሐይ ተብለህ ተሰይመሃልና ቤተ ክርስቲያን ስለ አንተ ‹ፀሐይ መልኬን አጥቁሮታልና ጥቁር ስለሆንኩ አትዩኝ[167]› ትላለች:: በመጽሐፈ ኪዳንም ‹ራስህ የማይጠልቅ ፀሐይ፣ የማይጠፋም መብራት፣ ዘወትርም በቅዱሳን ላይ የሚያበራ ፀሐይ ነው[168]› ትላለች::

(፺፬)የብርሃን ኮከብ ተብለህ ተጠርተሃል፤ የሶፎር ልጅ ባላቅ በጠራው ጊዜ በለዓም ትንቢት ሲናገር ‹ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፤ ከእሥራኤልም በትር ይነሣል[169]› አለ:: ለአቡቀለምሲስም ‹ከዳዊት ሥር የተገኘሁ የንጋት ኮከብ እኔ ነኝ[170]› ብለኸዋል::

(፺፭)ከብርሃን የተገኘህ ብርሃንም ተብለሃል፣ አንተ እንጂ ‹እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤[171]› ‹ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ የብርሃን

[163] ኢሳ 51÷1
[164] ዮሐ 4÷14
[165] ዮሐ 14÷6
[166] ዮሐ 11÷9
[167] መኃ 1÷6
[168] መጽሐፈ ኪዳን፣ ዘነግህ
[169] ዘኁ 24÷17
[170] ራእይ 22÷16
[171] ዮሐ 8÷12





ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ[172]›ብለሃልና:: ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድም ‹ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም ሁሉም በእርሱ ያምኑበት ዘንድ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ፣ እርሱ ራሱ ግን ብርሃን አልነበረም፤ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፤ ለሰው ሁሉ የሚያበራ እውነተኛው ብርሃን ግን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር፤ ዓለም ግን አላወቀውም[173]› አለ::

(፺፮)የሕይወት እንጀራም ተብለሃል፣ አንተው እንጂ ‹የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ሥጋዬንም የሚበላ በእኔ የተነሣ የዘለዓለም ሕይወት አለው[174]› ብለሃልና::

(፺፯)ጽዋዕም ተብለሃል፣ አንተው እንጂ ‹ይህ ጽዋዕ ደሜ ነውና እንኩ ጠጡ[175]› አልክ፤ ዳግመኛም ‹ደሜን የሚጠጣ ሞትን አይቀምስም[176]› አልክ::

(፺፰)በርም ተብለሃል፣ አንተም እንጂ ‹እኔ የበጎች በር ነኝ፣ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፣ ይገባልም ይወጣልም፣ መሠማርያም ያገኛል[177]› ብለሃል::

(፺፱)አበባም ተብለሃል፣ ኢሳይያስ ስለ አንተ ‹ከእሴይ ሥር በትር ይወጣል፣ ከግንዱም አበባ ያብባል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል[178]› ብሏል:: ቤተ ክርስቲያንም ስለ አንተ ‹ከንፈሮቹ እንደ አበቦች ናቸው፣ ከርቤንም ያንጠባጥባሉ[179]› ትላለች::

[172] ዮሐ 12÷35፣36
[173] ዮሐ 1÷6-10
[174] ዮሐ 6÷48፣56
[175] ዮሐ 6÷54
[176] ዮሐ 8÷51
[177] ዮሐ 10÷7፣9
[178] ኢሳ 11÷1-2
[179] መኃ 5÷13

(፻)የሰው ልጅም ተብለሃል፤ ከዳዊት ዘር በሥጋ ተወልደሃልና፤ አንተ በሕላዌህ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ እንደዚህ ስትል እንደነገርከን ‹የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ነው[180]› ብለኸናልና፡፡

(፻፩)የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ አንተ የዓለም መድኃኒት፣ ለአዳም ልጆችም የኃጢአታቸውን ዋጋ የምትሰጥ እንደሆንክ አመንኩብህ፤

አቤቱ አንተ የሰውን ልጅ ለማዳን ስትል መስቀልን እንደ ተሸከምክ አመንኩብህ፤

አቤቱ አንተ የብርሃን ልጅ ብርሃን መሆንህን አመንኩብህ፤

አቤቱ አንተ ከንጹሕ ምንጭ የተገኘህ ንጹሕ የሕይወት ምንጭ፣ ከሕይወት የተገኘህ ሕይወት፣ ከአንድ እግዚአብሔር የተገኘህ ወልድ ዋሕድ መሆንህን አመንኩ፤

አቤቱ አንተ ከወለደህ ጋር በመለኮት አንድ እንደሆንክ፣ ከአባትህም ጋር በህላዌ አንድ እንደሆንክ አመንኩ፤

አቤቱ አንተ የሃይማኖት ጽናት እንደሆንክ፣ ከአባትህና ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም በአንድነት በሦስትነት የተፈተልክ የማት በጠስ ፈትል እንደሆንክ አመንኩ፤

አቤቱ አንተ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አክሊል፣ የምእመናንም ጌጥ እንደሆንክ አመንኩ፤

አቤቱ አንተ የሸቱ መዓዛ እንደሆንክ አመንኩ፣ ከአንተም በተቀዳውም ካህናት ተቀቡ፤ ነገሥታት መሲሐውያንም ተቀቡ፣ በአንተም መላእከት ተመሉ፤

(፻፪)ከአንተ ዘንድ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ዘይት ከእኔ አታስወግድ፤ በመስ ቀልህም ሸከም አጠረኝ፤ ነፍሴንም እኔ ረዳትሽ ነኝ በላት፤ ‹በእጆቼ ሥልጣንና በማኅየዊ መስቀሌ አተምኩሽ› በላት፡፡ አጋንንትም ሥጋዬን ይነኩት ዘንድ አታሠልጥናቸው፤ በመስቀልህም ጥላ ሠውረኝ፤ ወፍ ከክንፎቿ

[180] ዮሐ 10+36





በታች ጫጩቶቿን እንደምታቅፍ በክንፎችህም ጥላ እቀፈኝ፣ በአባቶቻችን በአዳምና በሴት፣ በሄኖክም በረከት፤ በኖኅ፣ በሴምና በያፌት በረከት፤ በአብርሃም፣ በይስሐቅና እሥራኤል በተባለ ያዕቆብም በረከት፤በሙሴና በአሮን፣ በነቢያትም ሁሉ በረከት፤በጴጥሮስና በጳውሎስ፣ በሐዋርያትም ሁሉ በረከት፤ ድል ነሺዎች በሆኑ በሰማዕታት በረከት፤ በንጹሐን ደናግል በረከት፤ በተጋዳዮች ጻድቃን በረከት፤ ትጉሃን በሚሆኑ መላእከት በረከት፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፍጹማን ማኅበር በሚሆኑ በረከት፤ አብልጦም ደግሞ በቅድስት፣ ንጽሕትና ቡሩከት ወላዲተ አምላክ በምትሆን በማርያም ምልጃ፤ የጸጋ ማዕተብ፣የመድኃኒትም ምልክት በሚሆን በማኅያዊ ክቡር መስቀልህ በረከት፤ በእኔ በአገልጋይህ በፍሥሐ ክርስቶስ ላይ ብርሃንህ ይሁን ለዓለመ ዓለም፤ አሜን

(፻፫)ሰላም ሰላም፣ ለአንድየ መስቀል ሰላም፤

ቀኙንና ግራውንም እንሳለመዋለን፤

ፊቱንም ኋላውንም፤

የሰላምንም ሀገር እንሳለማለን፤

እርሱም የእግዚአብሔር ቀስት ነው፤

ለሕማሙም አልጋ የሆነው ነው፤

ደሙንም የተቀባ ነው፤

ዝም ባለማለትም ‹ሰላም› እንለዋለን፤

ስሙን እየጠራን፤

እርሱም አውሬውን የሚረታው ነው፤

ፊቱንም ዘነተረው፤

እናቱ ለሆነችው ለወላጁም ሰላም እንላለን፤

በንጽሕና ጽርሐ እርያሙ ተብላ ተጠርታለችና፤

የጸሎቷም ኃይል ጠላታችንን የሚያደክመው ይሁን፤

መታሰቢያዋንም በመተርጎም፣

ለመጨረስም አልቻልኩም፤

እናመልከው ዘንድ ለፈጠረን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤

††††††††††††††††††††††††††††††

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ታላቅ ቦታ የያዘ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ሲሆን፤ዐፄ ዳዊት ደሞ "ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ"ብለዉታል። ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኣባ ጊዮርጊስ(፲፫፻፶፯ እስከ ፲፬፻፲፯ዓ.ም) ነገረ ሃይማኖትን ጠንቅቆ የተረዳና የሚያስረዳ ነበረ። በዘመኑ የተነሡ የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ እርሱ ከሌለ አይሳኩም ነበር። አባ ጊዮርጊስ "ዉዳሴ መስቀል"ን የደረሰበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያዉ ከዐፄ ንዋየ ማርያም ዘመን ጀምሮ በአንዳንድ አካላት ዘንድ የተፈጠረዉ ለመስቀል ክብርና ስግደት አይገባዉም የሚለዉ አስተሳሰብ ነዉ። አባ ጊዮርጊስ ይህንን ሐሳብ የሚቃወምና ለመስቀሉ ሊሰጥ የሚገባዉን ክብርና ምስጋና የሚገልጥ ድርሰት በመድረስ የቤተ ክርስቲያኒቱን አቋም ገልጧል።ሁለተኛዉ፤ መስቀልንና ድንግል ማርያምን በተመለከተ የማን ክብር ይበልጣል? የሚል ክርክር በእርሱ ዘመን ተነሥቶ፤ በመጽሐፈ ምሥጢር ድርሰቱ ላይ፤"ደግሞም ሰዎች ስለ ማርያምና ስለ መስቀል እንደተሳሳቱ በጆሯችን የሚሮጥ ዜና አለ። ከፊሎቹ ደግሞ በሕማመ መስቀሉ የተጠመቀዉ መስቀል ይበልጣል ይላሉ። እኛ ግን ማርያምን ወላዲተ አምላክ እንደሆነች፤ መስቀሉንም በመለኮት ትስብእት በደሙ የተዋጀ የተቀደሰ የብርሃን ምልክት መሆኑን እናምናለን" በማለት አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ አቋሙን የገለጠበት መጽሐፍ ነዉ።

አሣታሚና አከፋፋይ:-
አግዮስጎትመት እና ጠቅላላ ንግድ
ኃ.የተ.የግል ማኅበር

ዋጋ ብር 35.00

Amaneul Printing Press